
# አዲስ ዘመን

ኢፕድ

እሁድ 82ኛ ዓመት ቁጥር 190 መጋቢት 10 ቀን 2015 ዓ.ም ዋጋ 10.00 ብዕራችን ለኢትዮጵያ ህዳሴ ይተጋል!


## “የመደመር ትውልድ የኢትዮጵያን ብልጽግና ያረጋግጣል”

- ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ

# የጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ "የመደመር ትውልድ" መጽሐፍ ተመረቀ

**ጌትነት ምህረቴ**

አዲስ አበባ፡- የመደመር ትውልድ የኢትዮጵያን ብልጽግና ያረጋግጣል ሲሉ የኢፌዴሪ ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር) ገለጹ። ጠቅላይ ሚኒስትሩ የጻፉት “የመደመር ትውልድ መጽሐፍ” ተመርቋል።

በሦስት ቋንቋዎች የተጻፈው የጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ "የመደመር ትውልድ" መጽሐፍ ትናንት በአንድነት ፓርክ ሲመረቅ ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ እንደገለጹት፤ የመደመር ትውልድ በርካታ ችግሮች ቢያጋጥሙትም እነዚህን ፈተናዎች ተሻግሮ የሚያልፍና ኢትዮጵያን ወደ ብልጽግና የሚያሻግር ነው።

የመደመር ትውልድ ብዙ ተስፋ ያለው ትውልድ ነው ያሉት ጠቅላይ ሚኒስትሩ፤ ይህ ትውልድ ለመጪው ትውልድ አሻራውን የሚያስቀምጥና ከተናጠል እውነት ወደ ወል እውነት የሚሸጋገርና የኢትዮጵያን ብልጽግና ማረጋገጥ ይጠበቅበታል ነው ያሉት።

አሻግሮ የሚያይና ፈተናዎችን የሚቋቋም ትውልድ ወደ ብልጽግና መሄዱ እንደማይቀር ገልጸው፤ የመደመር ትውልድ መጽሐፍ የተገለጸው የመደመር ትውልድ ትናንትን በማስተካከል ዛሬን በመገንባትና አሻራ በማስቀመጥ ለሚቀጥለው ትውልድ ዕዳ ሳይሆን ትርፍ የሚተው መሆን እንዳለበት ገልጸዋል።

ትውልዱ ሰፊርተኝነትን የሚጸየፍና የወደፊት ዕድሎቹን አሻግሮ በማየት በአብሮነት ወደ ሀብት መለወጥ እንደሚኖርበትም ጠቁመዋል። ይህ ትውልድ


“የመደመር ትውልድ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል




## ‹‹ኢትዮጵያ የውሃ ሀብቷን በውጤታማነት መጠቀም የምትችለው ግድቦችን ሠርታ ውሃ ማጠራቀም ስትችል ነው››

- ዶክተር በለጠ ብርሃኑ


ገጽ 4


# በድሬዳዋ ከተማ የሃገራዊ ምክክር ተሳታፊዎች ልየታ በቅርቡ ይጀመራል

**መዓዛ ማሞ**

አዲስ አበባ፡- ሃገራዊ የምክክር ኮሚሽን የተሳታፊ ልየታ የተግባር ሥራ በተያዘው መጋቢት ወር በድሬዳዋ ከተማ እንደሚጀምር ተገለጸ።

የሃገራዊ ምክክር ኮሚሽን የኮሙዩኒኬሽንና ሚዲያ ዘርፍ አስተባባሪ ወይዘሮ ቤተልሔም ኪሮስ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ የሃገራዊ ምክክር ኮሚሽኑ ተቋሙን በማስተዋወቅ፣ ከባለድርሻ አካላት ጋር ግንኙነት በመፍጠር እና የአሠራር ሥርዓት ላይ ሰነዶችን በማዘጋጀት የዝግጅት ጊዜውን እያጠናቀቀ በመሆኑ የተሳታፊ ልየታ የተግባር ሥራ በተያዘው የመጋቢት ወር በድሬዳዋ ከተማ ይጀመራል።

የተሳታፊ ልየታው ሥርዓት መዘጋጀቱን የጠቆሙት አስተባባሪዋ፤ በዚህም የተለያዩ የኅብረተሰብ ክፍሎችን የሚወክሉ በሥራቸው፣ በጾታቸው እና በተለያዩ መለያዎች ይለያሉ ብለዋል። በዚህም ከእድሮች፣ የሀገር

የኢትዮጵያ ሀገራዊ ምክክር ኮሚሽን | ETHIOPIAN NATIONAL DIALOGUE COMMISSION

ሽማግሌዎች፣ ከሴቶች፣ ከወጣቶች እንዲሁም ሌሎች ኅብረተሰቡን ሊወክሉ የሚችሉ ሰዎች በተዘጋጀው የአሠራር ሥርዓት መሠረት እንደሚመረጡ ገልጸዋል።

የድሬዳዋው ሲጠናቀቅ በሌሎች ክልሎች የተግባር ልየታ ሥራው እንደሚቀጥል እና ከመጪው ክረምት በፊት


በድሬዳዋ ከተማ ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል


# በሰባት ወራት ከጡረታ መዋጮ ከ31 ቢሊዮን ብር በላይ ተሰብስቧል

## - ተቋሙ አዲስ አበባን ጨምሮ በተለያዩ የክልል ከተሞች ሕንጻዎችን እያስገነባ ነው

**ልጅዓለም ፍቅሬ**

አዲስ አበባ፡- ባለፉት ሰባት ወራት ከጡረታ መዋጮ 31 ቢሊዮን ብር መሰብሰብ መቻሉን የመንግሥት ሠራተኞች ማኅበራዊ ዋስትና አስተዳደር አስታወቀ፡፡ ተቋሙ በሐረር፣ በጅማ፣ በሐዋሳ እና በባህር ዳር ለንግድ ሥራ የሚውሉ ሕንፃዎችን እያስገነባ መሆኑ ተጠቁሟል፡፡

የመንግሥት ሠራተኞች ማኅበራዊ ዋስትና አስተዳደር የለውጥና እቅድ ጥናት ዳይሬክተር አቶ አሰፋ ማናዬ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ አስተዳደሩ ባለፉት ሰባት ወራት ከመንግሥት ሠራተኞች 31 ቢሊዮን


በሰባት ወራት ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል




















## የስማርት ቆጣሪ ተደራሽነት የመጀመሪያው ምዕራፍ ሙሉ ለሙሉ ተጠናቀቀ

**ሳሙኤል ወንደሰን**

አዲስ አበባ፡- በሁለት ምዕራፍ የተከፈለው የስማርት ቆጣሪ መሠረተ ልማት ዝርጋታ ፕሮጀክት የመጀመሪያው ምዕራፍ ሙሉ ለሙሉ መጠናቀቁን የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ አገልግሎት አስታወቀ።

የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ አገልግሎት የኮርፖሬት ኮሙዩኒኬሽን ዳይሬክተር አቶ መላኩ ታዬ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደተናገሩት፤ የስማርት ቆጣሪ መሠረተ ልማት ዝርጋታ ፕሮጀክት በሁለት ምዕራፍ የተከፈለ ሲሆን በፕሮጀክቱ የመጀመሪያ ምዕራፍ አምስት ሺህ ስማርት ቆጣሪዎችን በሙከራ ደረጃ መትከል ተችሏል።

ዘመናዊ ቆጣሪዎቹ ከዚህ ቀደም የነበሩ የንባብ ክፍተቶችን የሚያሻሽሉና ዘመኑ የደረሰበትን ቴክኖሎጂ የሚጠቀሙ መሆናቸው የተናገሩት አቶ መላኩ፤ የቆጣሪ ቅየራው ለከፍተኛ ኃይል ተጠቃሚዎች የተደረገ መሆኑን ተናግረዋል።

ተቋሙ በሃገር አቀፍ ደረጃ ለመትከል ካስቀመጣቸው 50 ሺህ ቆጣሪዎች ውስጥ በፕሮጀክቱ የመጀመሪያ ምዕራፍ አምስት ሺህ ስማርት ቆጣሪዎችን መትከል ተችሏል። 45 ሺህ ቆጣሪዎች ደግሞ የአምስት ሺህ ስማርት ቆጣሪዎች ውጤቱ ከተረጋገጠ በኋላ እንደሚገጠሙ ኮሙዩኒኬሽን ዳይሬክተሩ ተናግረዋል።

የተቀየረው ቆጣሪ ዘመኑን የዋጀና የረቀቀ በመሆኑ ከቆጣሪ መረጃ የሚወሰደው በውስጡ በሚገጠም ሲምካርድ አማካኝነት መሆኑንና ተቋሙ ከሚጠቀመው ሥርዓት ጋር መረጃዎችን በመለዋወጥ ለደንበኛ ቢል በወቅቱ እንደሚያዘጋጅ ገልጸዋል።

ቆጣሪው ሲም ካርድ የሚወስድ መሆኑን የጠቆሙት ዳይሬክተሩ፤ በተሰጠው የሰዓት ልዩነት የፍጆታ ንባቦችን፣ የኃይል መቋረጥና መዋዠቆችን፣ የቆጣሪ መከፈትና የባትሪ አለመስራት መረጃዎችን ወደ ተቋሙ የመረጃ ቋት እንደሚልክም ተናግረዋል።

ደንበኞች የሞባይል መተግበሪያን በመጠቀም የራሳቸውን ወርሐዊ የኃይል ፍጆታ መከታተል ያስችላቸዋል። ቆጣሪው የንባብ ስህተትን እንደሚያስቀር እና በወቅቱ ንባብ ባለመውሰድ የሚፈጠር ውዝፍ እዳ ከመክፈል እንደሚታደግ ገልፀዋል።

በተቋሙ በኩልም ገንዘብ በወቅቱ ለመሰብሰብ ከማስቻሉ በተጨማሪ ቆጣሪ ከተነካካ መረጃ ወደ መቆጣጠሪያ ማዕከል በመላክ የኤሌክትሪክ ኃይል ስርቆትን እንደሚከላከል እና በእጅ የሚሠራ የቆጣሪ ንባብን እንደሚያስቀርም ጠቁመዋል።

ፕሮጀክቱን በታሰበለት ጊዜና ዕቅድ መሠረት ለማጠናቀቅ እነዚህ ከፍተኛ ኃይል የሚጠቀሙ የኢንዱስትሪ ደንበኞች እየተቀየረ የሚገኘውን ስማርት ቆጣሪ ጠቀሜታ ተረድተው ለአፈፃፀሙ ተገቢውን እገዛ ማድረግ እንደሚገባቸው አሳስበዋል።

# በሲዳማ ክልል በበጋ መስኖ ልማት 1ሺህ 626 ሄክታር መሬት በስንዴ ዘር ተሸፍኗል

## - ከ65 ሺህ ኩንታል በላይ ምርት ለማግኘት ታቅዷል

**አመለወርቅ ከበደ**

አዲስ አበባ፡-በሲዳማ ክልል በበጋ መስኖ ልማት 1 ሺህ 626 ሄክታር መሬት በስንዴ ዘር መሸፈኑን የክልሉ እርሻና ተፈጥሮ ሃብት ቢሮ ገለጸ። በበጋ መስኖ ከ65 ሺህ በላይ ኩንታል ምርት ለማግኘት ታቅዷል።

የሲዳማ ክልል እርሻና ተፈጥሮ ቢሮ ኃላፊ አቶ መስፍን ጋሬ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ በክልሉ የበጋ መስኖ ስንዴ ልማት ከአንድ ሄክታር 40 ኩንታል ስንዴ ለማግኘት እየተሠራ ሲሆን በአጠቃላይ ከ65 ሺህ በላይ ኩንታል ምርት ለማግኘት ታቅዷል።

እንደ አቶ መስፍን ገለጻ፤ በዘር የተሸፈነውን መሬት የእንክብካቤ ሥራ እየተከናወነ ይገኛል። በዚህም ማሳውን ውሃ የማጠጣት፣ ማዳበሪያ የመጠቀም፣ የኩትኳቶ እና ሌሎች የግብርና ሥራዎች በተቀናጀ መንገድ እየተሠሩ ነው።



በክልሉ ስንዴ በዋናነት የሚለማው ቆላማ በሆኑ አካባቢዎች ሲሆን በተወሰኑ ወይና ደጋማ አካባቢዎች ላይ የስንዴ ልማቱ እየተተገበረ መሆኑን ጠቁመዋል። ከዚህ በፊት በቆላማ አካባቢዎች ላይ በበጋ ወቅት ምንም አይነት የግብርና ሥራዎች ስለማይሠሩ አርሶ አደሩና መሬቱ ያለሥራ የሚያሳልፉበት ወቅት ነበር። አሁን ላይ በበጋ ወቅትም ማልማት እንደሚቻል ተሞክሮ ተወስዷል ብለዋል።

አርሶ አደሩ አሁን ላይ በበጋ ወቅት አልምቶ ምርት የሚያገኝበትን መንገድ በመፈጠሩ የምግብን ዋስትና ከማረጋገጥ አንጻር ትልቅ ጥቅም አለው ብለዋል፡ ቢሮው የመስኖ ልማት ሥራውን የተሳለጠ ለማድረግ የተለያዩ የድጋፍ ሥራዎችን እያከናወነ ይገኛል ያሉት አቶ መስፍን፤ ለአርሶ አደሩ የምርጥ ዘር፣ ማዳበሪያና የተለያዩ የግብርና ኬሚካሎችን እያቀረቡ መሆኑን ተናግረዋል።

በተጨማሪ በበጋ መስኖ ስንዴ ልማት ሥራ ለወጣቶች የሥራ ዕድል መፍጠር እንደተቻለ የጠቆሙት ኃላፊው፤ የወጣቶችን ተሳትፎ ለማሳደግ የሚረዱ የግንዛቤ ማስጨበጫ ሥራዎች ተጠናክረው እንደሚቀጥሉ ገልጸዋል።

ኃላፊው እንዳስታወቁት፤ የበጋ መስኖ ልማቱ በተሻለ የመነሳሳት ስሜት እየተከናወነ ቢሆንም የውሃ መሠረተ ልማቶችን ቀድሞ ከመሥራት አንጻር መዘግየት በመፈጠሩ በበጋ ወቅት መስኖ ሥራ ላይ የውሃ አቅርቦት እጥረት ተጨማሪ መሬት ለማልማት ተግዳሮት ሆኗል።

በመሆኑም ችግሩን ለመፍታትና የልማት ሥራውን የበለጠ ውጤታማ ለማድረግ ከባለ ድርሻ አካላት ጋር በመሆን ውሃ ለማዳረስ የሚያገለግሉ መሰረተ ልማቶችን ቀድመን ለመስራት አቅደናል ሲሉ ተናግረዋል።

# ለ20/80 እና 40/60

## የቤት ዕድለኞች ካርታ ታትሟል

**ሰሎሞን በየነ**

አዲስ አበባ፡- 11 ሺ 174 የ14ኛ ዙር 20/80 እና 3ኛ ዙር 40/60 የቤት ልማት መርሐ ግብር የጋራ መኖሪያ ቤቶች የቤት እድለኞች የሚጠበቅባቸውን የባንክ ክፍያና ሂደት ማጠናቀቃቸውን ተከትሎ ካርታ እንደታተመላቸው የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ቤቶች ልማት ኮርፖሬሽን አስታወቀ።

የኮርፖሬሽኑ የሕዝብ ግንኙነትና ኮሙዩኒኬሽን ዳይሬክተር አቶ ጋሻው ተፈራ ለአዲስ ዘመን ጋዜጣ እንደገለጹት፤ ከተማ አስተዳደሩ በ14ኛ ዙር የ20/80 የቤት ልማት ፕሮግራም 18 ሺ 930 ቤቶች፣ በ3ኛ ዙር የ40/60 የቤት ልማት መርሐ ግብር ደግሞ 6 ሺ 843 ቤቶች እንዲሁም ተጨማሪ 18 ስቱዲዮ ቤቶች በድምሩ 25 ሺ 791 የጋራ መኖሪያ ቤቶችን ባለፈው ሕዳር ወር 2015 ዓ.ም ዕጣ ማውጣቱ ይታወቃል።

በዚህም ከጥር 1 ቀን 2015 ዓ.ም ጀምሮ መገናኛ በሚገኘው የቦሌ ክፍለ ከተማ አስተዳደር ቅጥር ግቢ ውስጥ በኮርፖሬሽኑ የአንድ ማዕከል አገልግሎት መስጫ የጋራ መኖሪያ ቤት የቤት ባለ ዕድለኞች ውል በመዋዋል ላይ እንደሚገኙ ጠቁመው፤ የ20/80 እና የ40/60 የጋራ መኖሪያ ቤቶች ዕድለኞች እስከ መጋቢት 7/2015 ዓ.ም ድረስ ወደ አንድ ማዕከል ቀርበውና ተመዝግበው ቅፅ 09 የወሰዱት 25 ሺ 412 ናቸው። ከዚህ ውስጥ ቅፅ 09 ወስደው ከቀበሌ አስፈላጊውን ሂደት አጠናቀው ሪፖርት ካደረጉ በኋላ ቅፅ 03 ወስደው ከባንክ ጋር የሚጠበቅባቸውን ሂደት (procedure) ጨርሰው ቅጹን ያመጡ 17 ሺ 114 ናቸው።



**አቶ ጋሻው ተፈራ፤**

ከባንክ ጋር ያለውን የኦዲት ቅጽ 03 ወስደው የሚጠበቅባቸውን የባንክ ሂደትና ክፍያ በመጨረሳቸው 12 ሺ 618 ፋይሎች ካርታ እንዲሠራላቸው ለሚመለከተው አካል ተልኳል። በዚህም ከተላኩ ፋይሎች ውስጥ የ11 ሺ 174 የቤት ዕድለኞች ካርታ እንደታተመላቸው ተናግረዋል።

አቶ ጋሻው፤ ውል ለመዋዋል ከመጡ በኋላ አስፈላጊውን መስፈርት ባለማሟላታቸው የ775 ቤት እድለኞች ፋይላቸው ተመላሽ መደረጉን ጠቅሰው፤ ከዚህ ውስጥ 454 ተዋዋዮች ማስተካከል የሚገባቸውን አስተካክለው በመምጣት ፋይላቸው ተይዞላቸው ውላቸውን እያስፈጸሙ ይገኛሉ። በአንጻሩ ሁለት ሺ 343 የቤት ዕድለኞች የሚጠበቅባቸውን የባንክ ክፍያና ሂደት ባለመፈጸማቸው ባንክ እንዲታገዱ የእግድ ደብዳቤ ለተቋሙ ልኳል። ከዚህ ውስጥ የሚጠበቅባቸውን የባንክ ክፍያ በመፈጸማቸው 761 የቤት ዕድለኞች እግዱ ሲነሳላቸው ቀሪዎቹ አንድ ሺ 582 እግዱ እንዳልተነሳላቸው ገልጸዋል።

በጥቅሉ እስከ መጋቢት 7/2015 ዓ.ም 19 ሺ 570 የቤት እድለኞችን ውል ለማዋዋል መታቀዱን አቶ ጋሻው ጠቁመው፤ በተጠቀሰው ጊዜ ውስጥ በ40/60 የቤት ልማት መርሐ ግብር 162 እንዲሁም በ20/80 የቤት ልማት ፕሮግራም ደግሞ 14 ሺ 267 በድምሩ 14 ሺ 429 የቤት ዕድለኞች ውል ፈጽመዋል።

ይህም የሚያሳየው የቤት ዕድለኞች ቅፅ 09 እና 03 ከወሰዱ በኋላ ወደ አንድ ማዕከል ፈጥነው መጥተው መዋዋል ላይ ክፍተት እንዳለ ነው። ስለዚህ ቅፅ 09 እና 03 የወሰዱ የቤት ዕድለኞች አጠናቀው ወደ አንድ ማዕከል አገልግሎት መስጫ ቀርበው እስከ መጋቢት 26 ቀን 2015 ዓ.ም ድረስ በወጣው ውል የመዋዋያ መርሐግብር መሠረት እንዲዋዋሉ ኮርፖሬሽኑ ጥሪ አቅርቧል።

እድለኞች ቀርበው ውል የማይፈጽሙ ከሆነ ቤቱ ተመላሽ የሚደረግ ሲሆን ጉዳያቸው በፍርድ ቤት የተያዘ እና በህገራዊ ጉዳይ ግዳጅ ላይ ያሉ እድለኞች በሚያቀርቡት ማስረጃ መሠረት እንደሚስተናገዱ አቶ ጋሻው ገልጸዋል።

# ርዕሰ አንቀፅ

## ዲፕሎማሲያዊ ግንኙነቱን ለሳቀ ድል እንጠቀምበት!

ኢትዮጵያ ሉዓላዊት ሀገር ናት። በቅኝ ያልተገዛች ፤ ክብሯን የማታስነካ፤ የሌላውንም የማትፈልግ ፤ ሰላም ፈላጊና ሰላምን የምትሻ ሀገር ናት። ከጎረቤት ሀገራትም ሆነ ከሌሎች ጋር ያላት ግንኙነት በሰላም አብሮ በመኖርና በጋራ ተጠቃሚነት ላይ የተመሠረተ ነው፡፡ በጋራ ጥቅምና መከባበር ላይ መሠረት ያደረገ የውጪ ፖሊሲ ያላትና ይሄንኑም በተግባር የምታረጋግጥ ሀገር ናት።

በዚህም ረጅም ዓመታትን ባስቆጠረ የየሀገራት ዲፕሎማሲያዊ ግንኙነት ከበርካታ ሀገራት ጋር በጋራ ተጠቃሚነት ላይ ትብብር ስታደርግ ቆይታለች። በትምህርት፣ በባህል፣ በቴክኖሎጂ፣ በግብርና በሚሊቴሪ ፣ በኢንቨስትመንት እንዲሁም በሌሎች መስኮች ከብዙ ሀገራት ጋር በጋራ ሠርታለች፤ እየሠራችም ትገኛለች። ለልማቷ የፋይናንስ ድጋፍ፣ ብድርና እርዳታ ከሚያደርጉ ሀገራትና ዓለም አቀፍ ተቋማት ጋር አሁንም ይሄው ግንኙነቷን ቀጥላለች ።

ይሁን እንጂ ሀገራችን አጋጥሟት ከነበረው የሰላም መደፍረስ በተለይ በሰሜኑ የሀገራችን ክፍል በነበረው ጦርነት አንዳንድ ሀገራት በኢትዮጵያ ላይ ተጽዕኖ እንደነበር ይታወሳል። በኢኮኖሚ ዘርፍ ድጋፍና እርዳታን በመቀነስ፣ በአሜሪካ ከቀረጥ ነጻ የገበያ ዕድል(አጎዋ)እንዳትጠቀም እንዲሁም በፖለቲካው በተለያየ መልኩ ተጽዕኖ ለማድረግ ተሞክሯል። በአጠቃላይ ዲፕሎማሲውን ጥያቄ ውስጥ በሚከት መልኩ የተለያየ ጫናዎች ሲደረጉ ነበር። ይሁን እንጂ አሁን በሀገራችን ሰላም ከሰፈነና የሰሜኑ ጦርነት አፍሪካዊ ችግሮችን በአፍሪካዊ መፍትሔ እንዲያገኙ የሰላም ስምምነት ከተደረሰ በኋላ ከአንዳንድ ሀገራት ጋር ሻክሮ የነበረው ዲፕሎማሲያዊ ግንኙነት ወደነበረበት ከፍታ በመመለስ ላይ ይገኛል።

ለዚህም ዋነኛው ማሳያ በቅርቡ ያደጉት ሀገራት በውጭ ጉዳዮቻቸው አማካይነት በኢትዮጵያ ያደረጉት ጉብኝት ነው። ለምሳሌ ያህል የጀርመኑ ውጭ ጉዳይ ሚኒስትር አናሌና ባየርቦክ እና የፈረንሳይ የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር ካትሪ ኮሎናን ከጥር 4 ቀን 2015 ዓ.ም ጀምሮ በኢትዮጵያ የጋራ ይፋዊ የሥራ ጉብኝት አድርገዋል። በኢትዮጵያ ለሚካሄደው የመልሶ ግንባታ ሥራ ድጋፍ እንደሚያደርጉም አስታውቀዋል። ይህም ከሀገራቱ የሁለትዮሽ ግንኙነት ባለፈ በኢትዮጵያ እና የአውሮፓ ኅብረት መካከል መተማመን እና መግባባት በመፍጠር ሁሉም የኅብረቱ አባል አገራትና ኅብረቱ ከኢትዮጵያ ጋር ያለውን ትብብር መልሶ ለማጠናከር የሚያግዝ ሆኗል።

በቅርቡ ደግሞ የቻይና የውጪ ጉዳይ ሚንስትር ቺን ጋንግ የመጀመሪያውን የአፍሪካን ጉብኝታቸውን በኢትዮጵያ አድርገዋል። ይህም ጠንካራውን እና የቆየ ታሪክ ያለውን ግንኙነታቸውን ይበልጥ ወደ ተለያዩ መስኮች በማስፋት በፖለቲካ እና ኢኮኖሚ ዘርፍ ያለውን ግንኙነት ለማሳደግ የሚያግዝ ነው። በግጭቱ ተጎጂ በሆኑ አካባቢዎች ለሚደረገው መልሶ ግንባታ እና ማቋቋሚያ የፋይናንስ ድጋፍ ትብብር እንደሚያደርጉም መግባባት ላይ ደርሰዋል።

ሰሞኑን ደግሞ የአሜሪካው የውጪ ጉዳይ ሚኒስትር አንቶኒ ብሊንከን ጉዟቸውን ወደ ኢትዮጵያ አድርገዋል። ለሰላም ስምምነቱ ተግባራዊነት ድጋፍ እንደሚያደርጉና የሰብዓዊ ድጋፍም ከ133ሚሊዮን ዶላር በላይ መደረጉን አስታውቀዋል። ከሁሉም በላይ ኢትዮጵያና አሜሪካ የቆየውን የሁለትዮሽ ግንኙነት ወደ ላቀ ደረጃ ለማድረስም ተስማምተዋል። ይሄ ከየሀገራቱ ጋር ያለንን የዲፕሎማሲያዊ ግንኙነት እየተጠናከረ መምጣቱን ማሳያ ነው።

ከሀገራቱ ጋር ያለው ዲፕሎማሲያዊ ግንኙነት አሁን ባለው ደረጃ መሻሻል የታየው በመንግሥት በተሠራ ጠንካራ የዲፕሎማሲ እንቅስቃሴ፣ በየሀገራቱ የሚገኙ የኢትዮጵያ አምባሳደሮች የተቀዛቀዘው ዲፕሎማሲያዊ ግንኙነት ወደነበረበት ጠንካራ ግንኙነት ለመመለስ በሠሩት ሰፊ ሥራ ፣የኢትዮጵያን እውነታ ለዓለም አቀፉ ማኅበረሰብ ለማሳወቅና በኢትዮጵያ ላይ ጫና ሊደረግባት አይገባም በሚል የተንቀሳቀሰው ዲያስፖራም ለዚህ ትልቅ አስተዋፅዖ አበርክቷል። በአጠቃላይ ከሃገር ውስጥ እስከውጪ የተሠራው ሥራ አሁን ዲፕሎማሲው በተሻለ ደረጃ ላይ እንዲደርስ አግዟል። ይሄን አሁንም ወደፊትም ተጠናክሮ ሊያዝና ሊቀጥል የሚገባው ነው።

በዲፕሎማሲው ዘርፍ አሁን ያለው እንቅስቃሴ እያደገና እየተጠናከረ መምጣቱ የዲፕሎማሲያዊ ጥረቱ ውጤት ቢሆንም በቀጣይም ከዚህ የበለጠ ሥራ በመሥራት በሁሉም ሀገራት በኩል ያለንን ግንኙነት ይበልጥ ማሳደግ ይገባል። ኢትዮጵያ በኢኮኖሚ ፣በፖለቲካ እና በሌላውም መስክ ተመራጭ፣ተወዳጅና ተጽዕኖ ፈጣሪ ሀገር እንድትሆን መሥራት ይገባል፤ ያስፈልጋልም!


**አዲስ ዘመን**

ኢፕድ

ግንቦት 30 ቀን 1933 ዓ.ም ተቋቋመ

**የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ዋና ስራ አስፈጻሚ**
ስልክ ቁጥር - 011-126-42-22

**ዋና አዘጋጅ**
አንተነህ ኃ/ብርሃን ወ/መድህን

**አድራሻ**
ንፋስ ስልክ ላፍቶ ክ/ከ
ወረዳ 06
የቤት ቁጥር 319
ኢሜይል - anteneh.hailebirhan@press.et
ስልክ ቁጥር - 011-1-26-42-40

**የገበያ ልማትና ፕሮሞሽን ዘርፍ**
ኢሜይል - etpresspromotion@gmail.com
ስልክ - 011-126-43-41
ፋክስ - 011-811-13-15
የዝግጅት ክፍል ፋክስ - 251-011-1-56-98-62

**የአዲስ ዘመን ማኔጂንግ ኤዲተር**
ወንድወሰን ሽመልስ ታደሰ
ስልክ፡- 011 126 4240
Email:- wendweson.shimelis@press.et
wendwesonshimelis@gmail.com

**የአዲስ ዘመን ምክትል ዋና አዘጋጆች**
- ወርቁ ማሩ
- ኃይሉ ሣህለድንግል
- አልማዝ አያሌው
- እስማኤል አረቦ

**የማስታወቂያ መቀበያ ክፍል**
ስልክ ቁጥር - 011-156-98-73
ፋክስ - 011-126-58-12

**የማስታወቂያ ሽያጭ ማስተባበሪያ**
ስልክ - 011-1-26-43-39

**ማከፋፈያ** ፡- ስልክ ቁጥር - 011-157-02-70


# ነፃ ሃሳብ

ይህ አምድ በተለያዩ ፖለቲካዊ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ጉዳዮች ዙሪያ ዜጎች ነፃ ሀሳባቸውን የሚሰጡበት ነው፡፡ በዓምዱ ላይ የሚወጡ ጽሁፎች የዝግጅት ክፍሉን አቋም አያመለክቱም፡፡

## ሃገራችንን ለመታደግ ወገናችንን እንጠብቅ

ሶሎሞን በየነ

**ውብ ሀገሬ፣ ውብ ሀገሬ፣ ውብ ሀገሬ፤**
**ባንች እኮ ነው መከበሬ፣ መከበሬ፤**
**እናት አባት ቢሞት በሀገር ይለቀሳል፤**
**እህት ወንድም ቢሞት በሀገር ይለቀሳል፤**
**ሀገር የሞተ እንደሁ ወዴት ይደረሳል፤**
**.... ውብ ሀገሬ፣ ውብ ሀገሬ ......**

ይሄንን መዝሙር ያኔ ተንኮል ሸር በሌለበት፣ ምቀኝነት ክፋት ባልሰለጠነበት፣ ሴራ ባልተጎነጎነበት ንጹሕ ወረቀት በሆነው የልጅነት አዕምሯችን ዘምረን ያደግን የምናስታውሰው ነው። መዝሙሩ የሚያስረዳው ሰው ያለ ሀገሩ ባዶ እንደሆነና ሀገር ከዕምነት፣ ከቋንቋ፣ ከዘር፣ ከእናት አባት፣ ከወገን ከዘመድ በጥቅሉ ከምንም በላይ መሆኑን ነው። ኃዘን፣ መከራ፣ ችግር፣ ረሀብ፣ መታረዝ፣... ሀገር ካለች ሁሉ በሀገር ላይ ይቻላል። አይደለም ደስታ ልቅሶ በሀገር ያምራል። የሀገሬው ሰው "ሞቴን በሀገሬ አድርገው" ብሎ ፈጣሪውን የሚማጸነው ለዚህ ነው። ስለዚህ ሀገራችን ኢትዮጵያ የሁሉ ነገራችን የመጨረሻዋ ቋጠሮ ብርቱ ክንድ ናት።

ይህቺን የነጻነት ቀንዲል የጥቁር ሕዝቦች ወይም ማኅበረሰብ የነጻነት ዓርማ የሆነች ሀገር ታፍራና ተከብራ ለዛሬ እንድትደርስ የትናንት አባቶቻችን መራራ የሕይወት መስዋዕትነት ከፍለዋል። እንዲህ በዋዛ ዳር ድንበሯ፣ ሕዝቧ፣ መልክዓ ምድሮቿ ተጠብቀው በነጻነት ለዛሬ አልደረሰችም። ይልቁንም በትውልድ ቅብብሎሽ በተከፈለ መራራ መስዋዕትነት የተገነባች የማትደፈር ተራራ ናት።

ታዲያ ሳትደፈር በትውልድ ቅብብሎሽ ዛሬ እኛ ላይ ደርሳለች። እናም ይች ሀገራችንን ዛሬን በአንድነት ተከባብረን ኖረን፣ የራሳችን የታሪክ አሻራ አኑረን፣ ለነገው ትውልድ የማስረከብ ኃላፊነት እያንዳንዳችን አለብን። ምክንያቱም ትናንት ለኛ እንድትደርስ ዋጋ የከፈሉ አባቶች እዳ አለብንና ነው። ይህን ባናደርግ አጥንታቸውን ከስክሰው ደማቸውን አፍሰው ሀገር ነጻነቷ ተጠብቆ ለዛሬ እንድትደርስ ያደረጉ አባቶቻችን አጥንታቸው ይረግመናል።

ነገር ግን ሀገር ነጻነቷ ተጠብቆ ለዛሬ እንድትደርስ የተከፈለውን ዋጋ ዘንግተን አንዴ በሃይማኖት፣ ሌላ ጊዜ በቋንቋ፣ ሻገር ሲልም በብሔርና በዘረኝነት ልክፍት ታውረን እርስ በእርስ ስንጋጭ እንዲሁም በሴራ፣ በአፍቅሮተ ንዋይ፣ በስግብግብነት እርስ በእርስ እየተጠላለፍን . . . ወ.ዘ.ተ ሀገራችንን እጃችን ላይ አጥተናት ማጣፊያው አጥሮብን እንደቃየል ስንቅበዘበዝ ለመኖር እየተሯሯጥን እንገኛለን።

በዚህ ክፉ መንገዳችን ደግሞ ሀገራችን የሞት አፋፍ ላይ ቁማ እያጣጣረች ትገኛለች። ገዳዮቿ ደግሞ ማሯን ልሰን፣ ወተቷን ጠጥተን፣ ሥጋዋን በልተን በጉያዋ አቅፋ ያሳደገችን እንዲሁም አፈርና ውሃዋን ተራጭተን እንደ እንቦሳ ጥጃ ቦርቀን በደጇ ያደግን እኛው ልጆቿ ነን።

ብዙዎች የሚያፈርሷት የውጭ ታሪካዊ ጠላቶቿ ናቸው ይላሉ፡፡ ነገር ግን እኔ "የውጭ ታሪካዊ ጠላቶቿ ሊያፈርሷት ነው" የሚለውን አልቀበልም። "ለምን?" ቢባል ጠላት ሁሌም እንዳለ ይታወቃል። ጠላት የትኛውንም መንገድ ተጠቅሞ ለማሸነፍ ይጥራል። ነገር ግን "ጠላት ለማሸነፍ ወይም ለማጥቃት የሚመጣበትን የትኛውንም መንገድ መመከት ነው" አሸናፊ የሚያደርገው። ነገር ግን "ለሥልጣን አልያም የአፍቅሮተ ነዋይ ጥሙን ለማርካት" ሲባል ሀገርን ለማፍረስ፣ የወገንን አንገት ለማስደፋት ከጠላቶቻችን ጋር የምንተባበረው እኛው በደጇ ቦርቀን ያደግን የእናት ጡት ነካሽ ልጆቿ ነን። ጠራቸውን አዝምተው ለመውረርና ለማፍረስ ያልተሳካላቸው ታሪካዊ ጠላቶቿ በሴራ ሀገሪቱን ለማፍረስ፣ ሕዝቧን ለማዋረድ እኛው ልጆቿን ነው የሴራቸው ማስፈጸሚያ አድርገው እየተጠቀሙብን ያሉት።

ታዲያ "የዚህ የሴራቸው ማስፈጸሚያ ያልሆነ ሰው ማነው?" ብለን ስንጠይቅ ብዙዎቻችን በአንድም በሌላ መንገድ የኢትዮጵያ ታሪካዊ ጠላቶች የሴራ ማስፈጸሚያ ሆነና ባይ ነኝ። ምክንያቱም ማኅበረሰብ እንደ ማኅበረሰብ አንቺ ትብሽ አንተ ትብስ ተባብሎ በአንድ የኢትዮጵያ ጥላ ሥር ተዛዝኖና ተከባብሮ የመኖር ባሕላችን ጠፍቶ አንዴ በብሔር፣ ሌላ ጊዜ በቋንቋ እንዲሁም በኃይማኖት እየተባላን እንገኛለን። የአንድ ሀገር ሰዎች "ከየት መጣህ፣ ከዚህ ውጣ፣ ይሄ የኔ ነው፣ ያ የኔ ነው" እየተባባልን እርስ በእርስ እየተባላን፤ እየተጋደልን እንገኛለን።

ሌላው ነጋዴው፣ ሐኪሙ፣ መምህሩ፣ ጋዜጠኛው፣ መሐንዲሱ፣ በአጠቃላይ ሁሉም አገልግሎት ሰጭ ሠራተኛው የበኩሉን ለሀገር እና ወገኑ የሚጠበቅበትን ኃላፊነት እየተወጣ ነው? ቢባል የአብዛኛው መልስ ምን እንደሆነ ይታወቃል። ነጋዴው በተንሻፈፈ ነጻ ገበያ ስም ኅብረተሰቡን እርቃኑን እስኪቀር ድረስ ያልባል፤ ሐኪሙ ሳይማር ያስተማረውን ድሃውን ማኅበረሰብ ለማከም ተጠይፎ ከበርቴዎችን ምን ይሻላችሁ በሚልበት፣ ፖለቲከኛው በሕዝብ ሕይወት በሚቆምርበት፤ አስተማሪው እውቀትን ሳይሆን ዘረኝነትን በሚሰብክበት፤ ጋዜጠኛው ለሙያው ሥነምግባር ተገዥ ሆኖ ከወገንተኝነት የጸዳ መረጃ በማያደርስበት፤ በየመንግሥት ተቋማት ያለው አገልግሎት ሰጭ ሠራተኛው "ከየት መጣህ? ብሔርህ ማነው?" ሳይልና የእጅ መንሻ ሳይቀበል ለኅብረተሰቡ አገልግሎት በማይሰጥበት፤ ባለስልጣኑ ሥልጣኑን ተገን አድርጎ የሀገር ሀብት በሚዘርፍበት፤ እንዲሁም ሁሉንም በእኩል አይን ማስተዳደር ሲገባው አንዱን ልጅ፣ ሌላኛውን የእንጀራ ልጅ አድርጎ በሚያስተዳድርበት፤ ወጣቱ ኢትዮጵያዊ ባሕልና ወጉን ዘንግቶ በምዕራባውያን መጤ ባሕል ተጠልፎ እየዛከረ በሚገኝበት ... ወ.ዘ.ተ ሁኔታ ሀገር ውጥንቅጧ ጠፍቶ ይገኛል።

እንዲሁም በቅርቡ በሀገሪቱ የሰሜኑ ክፍል በተካሄደው ጦርነት በሰውና በንብረት ላይ ከደረሰው ጥፋት መማር ተስኖን አንደኛው የጦርነት ምዕራፍ በቅጡ ሳይቋጭ ሌላኛውን የጦርነት ምዕራፍ ለማስጀመር ነጋሪት ሲጎሰም ይደመጣል። ዛሬም ከጦርነት አዙሪት አልወጣንም። ሕዝብ ለሕዝብ ተጨካክኗል። አንዱ ባማረ ሕንጻ ውስጥ እየኖረ ሌላኛው ማደሪያ አጥቶ ከጎዳና ወድቋል፡፡ አንዱ ዳቦ መግዣ ተቸግሮ እጁን ለልመና ይዘረጋል፤ ሌላኛው ገንዘብ መጣያው ጠፍቶበታል። አንዱ አራጅ ሌላኛው ታራጅና ተሳዳጅ ሆኗል፤ . . . ስለዚህ ማንም ከደሙ ንጹሕ የለም።

በመሆኑም ዜጎቿ ዛሬ ምን ይመጣብን? ነገ ደግሞ ምን ይከሰት ይሆን? በሚል የሰቀቀን ኑሮ እንደነፍሰጡር ቀን እየቆጠሩ ይገኛሉ። በስደት በሰው ሃገር ከሚባዝኑና ለስደት ወጥተው የአውሬ እራት ሆነው ከቀሩ ዜጎች ባሻገር በሀገራቸው መኖር ተሳቀው የሚንከራተቱት ብዙዎች ናቸው። በጥቅሉ ሀገራችን ከመከራዋ ክብደት እና ብዛት አንጻር ትክሻዋ ዝሎ፣ ወገቧ ጎብጦ፣ ጉልበቷ ተንቀጥቅጦ የሰው ያለህ እያለች ትገኛለች።

ስለዚህ ሳይረፍድ ሁሉም ዜጋ በተሠማራበት የሙያ መስክ የሚጠበቅበትን ኃላፊነት በመወጣት ሀገራችንን ከተጋረጠባት አደጋ ልንታደግና በጽኑ መሠረት ልናቆም ይገባል። ሁሉም ሀገሩን እንደአይኑ ብሌን መጠበቅ አለበት። ወጣት አዛውንት ሳይባል ሁሉም ማኅበረሰብ የሀገሩን ሰላም በማስጠበቅ ለሀገሩ ዘብ በመቆም የበኩሉን ሚና መጫወት አለበት። ምክንያቱም ሀገር የሞተ እንደሁ ወዴት ይደረሳል! ነው ብሂሉም፣ እውነቱም፡፡ እንዴት ቢሉ፣ ንጉስስ በማን ላይ ነግሶ ይፈርዳል? ነጋዴው ያካበተውን ሀብትና ንብረት የት ተቀምጦ ይበላዋል? የሃይማኖት አባቱስ ለማን ይጸልያል? መምህሩስ ማንን ያስተምራል?...፤ እናም አገራችንን እንደ ብሌናችን፤ ወገናችንን እንደ አካላችን ልንጠብቅና ልንወድ ይገባል፡፡

# በደቡብ ጎንደር ከሁለት ሚሊዮን ኩንታል በላይ የሩዝ ምርት ተመርቷል

**ታደሠ ብናልፈው**

አዲስ አበባ፡- በ2014/15 የመኸር ምርት ዘመን ከሁለት ሚሊዮን ኩንታል በላይ የሩዝ ምርት መመረቱን በአማራ ክልል የደቡብ ጎንደር ዞን አስተዳደር አስታወቀ::

የዞኑ ምክትል አስተዳዳሪ አቶ አዲስ ተፈራ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ የሩዝ ምርትና ምርታማነትን ለማሳደግ በተሠራው መጠነ ሰፊ ሥራ በ2014/15 የመኸር ምርት ዘመን ከሁለት ሚሊዮን ኩንታል በላይ የሩዝ ምርት ማግኘት ተችሏል::

በ2014/15 የመኸር ምርት ዘመን በዞኑ 42 ሺህ 500 ሄክታር መሬት በሩዝ መሸፈኑን የገለጹት ምክትል አስተዳዳሪው፤ በዘር ከተሸፈነው መሬት ከሁለት ሚሊዮን ኩንታል በላይ የሩዝ ምርት ተገኝቷል ብለዋል::

አርሶ አደሩ የተሻሻሉ የሩዝ ዝርያዎችን መጠቀም በመቻሉ ከአንድ ሄክታር የሚገኘውን 28 ኩንታል የሩዝ ምርትን ወደ 36 ኩንታል ከፍ ማድረግ መቻሉን አብራርተዋል:: የሩዝ ምርትና ምርታማነትን አስፋፍቶ በጥራት በማምረት በኩል መጠነ ሰፊ ሥራዎች ተሠርተዋል:: ከዚህም በላይ ምርታማነቱን ለማሳደግ ወደፊትም በቅንጅትና በትኩረት ይሠራል ሲሉ ተናግረዋል::

የሩዝ ምርት አቅርቦትን በስፋትና በጥራት ለሀገር ውስጥ ገበያ ተደራሽ ለማድረግም ምርታማነትን የሚያሻሽሉ የምርምር ውጤቶችን አርሶ አደሮቹ እየተጠቀሙ መሆኑንም ገልጸዋል::

በብሔራዊ የሩዝ የምርምር ጣቢያ በጥናትና በምርምር የተሻሻሉ የሩዝ ዝርያዎችን በመጠቀምና በየዓመቱ በሩዝ ሰብል የሚሸፈነውን መሬት በማስፋፋት የሩዝ ምርታማነትን ማሳደግ እንደተቻለ ተናግረዋል::

በተጨማሪም ዞኑ ከክልል የግብርና ቢሮና ከወረዳ የግብርና ባለሙያዎች ጋር በቅንጅት በመሥራት የሩዝን ምርታማነት እያሳደገ እንደሚገኝ ጠቁመዋል:: ለአርሶ አደሮችና ለግብርና ባለሙያዎች የሚያስፈልጉ መሠረታዊ ስልጠናዎችን ከክልሉ ግብርና ቢሮ ጋር በትብብር በመስጠትና ለግብርናው የሚያስፈልጉ የተሻሻሉ ዝርያዎች፣ የማዳበሪያና የተፈጥሮ ግብዓቶችን በማሟላት ከሁለት ሚሊዮን ኩንታል በላይ የሩዝ ምርት ማግኘት ተችሏል ያሉት አቶ አዲስ የሩዝ ምርትና ምርታማነትን ለማሳደግ ዞኑ ትኩረት ሰጥቶ እየሠራ መሆኑን ገልጸዋል::

በዞኑ እየተመረተ ያለው የሩዝ ምርትን በጥራት ለገበያ ተደራሽ ከማድረግ አንጻር የመፈልፈያ ማሽን የጥራትና የተደራሽነት ችግር መኖሩን የጠቀሱት ምክትል አስተዳዳሪው፤ ያለውን ችግር በየጊዜው የመገምገምና ክትትል የማድረግ እንቅስቃሴ በመጀመሩ በተወሰነ መልኩ እየተቀረፈ ነው ሲሉ አብራርተዋል::

በ2015/16 የመኸር ወቅት በዞኑ በሩዝ ምርት የሚሸፈነውን ሄክታር በእጥፍ በማሳደግ ከዘንድሮው የበለጠ የሩዝ ምርት ለማግኘት ከወዲሁ ትኩረት ተሰጥቶ እየተሠራበት መሆኑን አመላክተዋል::

# “የመደመር ትውልድ ...

ከ1ኛው ገጽ የዞረ

የኢትዮጵያን ችግር የሚፈታ፣በሥራ፣በምክንያትና በሳይንስ የሚያምን ይሆናል ብለዋል።

የመደመር መጽሐፍ ሀሳቡ ለትውልድ፤ገቢው ደግሞ ለልማት የሚውል መሆኑን ጠቅላይ ሚኒስትሩ ገልጸዋል።

የመደመር ትውልድ መጽሐፍ 274 ገፆች ያሉት ሲሆን በሦሥት ክፍሎችና በ10 ምዕራፎች የተዋቀረ መሆኑን በምረቃ ሥነ ሥርዓቱ ላይ ተገልጿል። መጽሐፉ በአማርኛ፣ በአፋን ኦሮሞ እና በእንግሊዝኛ ቋንቋዎች የተዘጋጀ ነው።

አዲሱን የመደመር መጽሐፍ ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ ለታዳጊዎች ያበረከቱ ሲሆን፤ ይህ መጽሐፍ ስምንተኛ መጽሐፋቸው መሆኑን ገልጸዋል።

የመደመር ትውልድ መጽሐፍ ትውልዱን በአምስት የሚከፋልና ጥንካሬያቸውንና ድክመቶቻቸውን የሚያትትና ከእነዚህ ትውልዶች ትምህርት በመወሰድ ኢትዮጵያን ወደ ፊት የሚያራምድ ሀገር በቀል ሀሳቦችን የያዘ መሆኑን ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ ገልጸዋል። በሚቀጥለው ዓመትም ሌላ የመደመር መጽሐፍ እንደሚያስመርቁ ነው የጠቆሙት።

የመደመር ትውልድ መጽሐፍ ከያዛቸው አንኳር ነጥቦች መካከልም በአርቲስት ደበበ እሸቱ፥ ደራሲ ሕይወት ተፈራና ሌሎች ምሑራን አማካኝነት በንባብ ለታዳሚው አሰምተዋል።

ሀገራችን ሙሉ አቅምና ብልጽግናዋ ሊረጋገጥ የሚችለው ዘመን ተሻጋሪ ውበትና ሀብትን መፍጠር የሚችል ትውልድ ሲፈጠር ብቻ እንደሆነ በመጽሐፉ ላይ ሰፍሯል።

“ሌላውን እንደራሱ የሚመለከት፤ ብሔሩንና ሀገራዊ ብሔርተኝነትን ያስታረቀ፤ የትናንቱን በጎ ነገር ይዞ የትናንቱን ስህተት የሚያርም፤ ትናንትን ከዛሬና ከነገ ያስማማ፤ በእነዚህ ጉዳዮች የልሂቃንን ስምምነት በማምጣት ሀገራዊ መግባባትና እርቅን የሚያሰፍን ትውልድ ይፈጠርበታል” የሚሉ ጉዳዮች በመጽሐፉ ተቀምጧል።

በአማራ ክልል የሚሸጠው ገቢ በሙሉ ለአጼ ፋሲል ግንብ እድሳት፤ በኦሮሚያ ክልል የሚሸጠው ገቢ ደግሞ ለሶፍ ዑመር ዋሻ ዕድሳት፣ በአፋር ክልል የሚሸጠው ገቢው አይሳኢታ ለሚገኘው የሱልጣን ቤተ መንግሥት ዕድሳትና በሌሎች ክልሎች ከመጽሐፉ ሽያጭ የሚገኘው ገቢም በየክልላቸው ቤተ መጽሐፍት፣ስፖርት ማዘውተሪያና ለሌሎች አስፈላጊ መሠረተ ልማቶች የሚገነቡበት እንደሆነ ለክልል ፕሬዚዳንቶች ኃላፊነቱን ሰጥተዋል።

መጽሐፉ ምክትል ጠቅላይ ሚኒስትርና የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር ደመቀ መኮንን ፥ ቀዳማዊት እመቤት ዝናሽ ታያቸው፣ የፌዴሬሽንና የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት አፈ ጉባኤዎች፣ የክልል ርዕሰ መስተዳድሮች፣ ሚኒስትሮች፣ የተለያዩ የኅብረተሰብ ክፍሎችና ታዳጊዎች በተገኙበት በአንድነት ፓርክ ተመርቋል።

# በድሬዳዋ ከተማ...

ከ1ኛው ገጽ የዞረ

የተግባር ልየታው እንደሚጠናቀቅ የጠቆሙት ወይዘሮ ቤተልሔም፤ ተሳታፊዎች የሚለዩበት ሥርዓት የክልሎቹን ነባራዊ ሁኔታ ያገናዘበ ከክልል ክልል ሊለያይ የሚችል እንደሆነም ገልጸዋል።

ተሳታፊዎች እንዴት ይለዩ የሚለው ሀሳብ የኮሚሽኑ ብቻ ሀሳብ ሳይሆን የማኅበረሰቡ ሀሳብ ጭምር ተወስዶ የአሠራር ሥርዓቱ መዘጋጀቱን የተናገሩት ኃላፊዋ፤ ሁሉም የኅብረተሰብ ክፍል እንዲወከል በጥንቃቄ መሠራቱን ነው የገለጹት።

እንደ ወይዘሮ ቤተልሔም ገለጻ፤ ኮሚሽኑ የሚያካሒደው ምክክር ከሌላ አገር ተሞክሮ ወስዶ የሚደግመው ሳይሆን እንደ ኢትዮጵያ ነባራዊ ሁኔታ ከሌላው ዓለም በተለየ መልኩ ሁሉም የማኅበረሰብ ክፍል የሚወከልበት እና ከታች ጀምሮ ውይይት የሚደረግበት ነው።

የተሳታፊ ልየታ ሥራው ሲጠናቀቅ በቀጣይ የአጀንዳ ልየታ ሥራ እንደሚጀመር ገልጸው በዚህም ሕዝቡ ሊመክርባቸው እና ሊወያይባቸው የሚገቡ አጀንዳዎች ሊመረጡ እንደሚችሉ ተናግረዋል።

ሃገራዊ ምክክሩ ከችግር እና ከግጭት ልንወጣበት የምንችልበት እንደሆነ በብዙ የፖለቲካ ፓርቲዎች እና የማኅበረሰብ ክፍሎች የታመነበት ነው ያሉት ወይዘሮ ቤተልሔም፤ ለስኬቱ ሁሉም ማኅበረሰብ ተሳታፊ እንዲሆን በተለይም የሚዲያ አካላት ስለ ሃገራዊ ምክክሩ በቂ መረጃ በመስጠት ኃላፊነታቸውን እንዲወጡ ጥሪያቸውን አቅርበዋል።

# ‹‹ኢትዮጵያ የውሃ ሀብቷን በውጤታማነት መጠቀም የምትችለው ግድቦችን ሠርታ ውሃ ማጠራቀም ስትችል ነው››

*- ዶክተር በለጠ ብርሃኑ*

**አስቴር ኤልያስ**

አዲስ አበባ፡- ኢትዮጵያ በትክክል የውሃ ሀብቷን መጠቀም የምትችለው በርካታ ግድቦችን ሠርታ ውሃ ማጠራቀም ስትችል ነው ሲሉ በታላቁ የኢትዮጵያ ህዳሴ ግድብ የቴክኒክ ባለሙያ ቡድን አባል ዶክተር በለጠ ብርሃኑ አስታወቁ።

በአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ ቴክኖሎጂ ኢንስቲትዩት በሲቪል ምህንድስና ትምህርት ክፍል መምህር የሆኑትና የዓባይ ግድብ የቴክኒክ ባለሙያ ቡድን አባል ዶክተር በለጠ ብርሃኑ፣ ለአዲስ ዘመን እንዳስታወቁት፤ በዓለማችን ላይ ያሉ ኃያላን የተባሉ ሀገሮች የተቀየሩት በውሃ ሀብት አጠቃቀማቸው ነው። ኢትዮጵያም በትክክል የውሃ ሀብቷን መጠቀም የምትችለው በርካታ ግድቦችን ሠርታ ውሃ ማጠራቀም ስትችል ነው።

ኢትዮጵያ የቀደመ አካሄዷን መቀየር የምትችለው በዝናብ የምታገኘውን ውሃ አጠራቅማ በፈለገችበት ጊዜ መጠቀም ስትችል ነው ያሉት ዶክተር በለጠ፤ እነዚህ የውሃ ማጠራቀሚያዎች ደግሞ ግድቦች ናቸው ብለዋል። ከዚህም የተነሳ በርካታ የውሃ ግድቦችን መሥራት ለኢትዮጵያ ወሳኝ እንደሆነ ተናግረዋል።

እርሳቸው እንደገለጹት፤ በውሃ መስፈርት ሲታይ ትልቅ አቅም ነው የሚባለው የዝናብ ሀብት መኖሩ ብቻ ሳይሆን ውሃ የማጠራቀም አቅም ሲኖር ነው። እስካሁን ዓባይ ግድብ ሳይጨመር ማጠራቀም የተቻለው ወደ 31 ቢሊዮን ሜትር ኪዩብ ውሃ ነው። ይህ በአሁኑ ወቅት አሉ በምንላቸው ግድቦችና በተፈጥሮ ሐይቆች ያጠራቀምነው ሲሆን ይህ በጣም አነስተኛ ቁጥር ነው።

በዓለማችን በዕድገታቸው ላቅ ያሉ ሀገሮች የማደጋቸው ምስጢር ከሆነው አንዱ ውሃ የማጠራቀም ልምዳቸውን በማሻሻላቸው ነው። ለምሳሌ እንደ ኢትዮጵያ ዝናባማ ሀገር የሆነችውን ካናዳን ወደ 860 ቢሊዮን ሜትር ኪዩብ ውሃ ማጠራቀም ችላለች ያሉት ዶክተር በለጠ፣ ይህ በየዓመቱ የሚታደስ ነው ብለዋል። አሜሪካም ልማቷን የቀየረችው ወደ 710 ቢሊዮን ሜትር ኪዩብ ውሃ በማጠራቀሟ ነው። ቻይና እና ሕንድ እኤአ በ1960ዎቹ አካባቢ በጣም ችግር ውስጥ የነበሩ ሀገራት መሆናቸውን አስታውሰው፤ ዛሬ የመጡበት ልማትና ያደጉ ሀገራት ያደረጋቸው ውሃን የማጠራቀም አቅማቸው ነው ሲሉ አስረድተዋል። ቻይና በ15 እና በ20 ዓመት ጊዜ ውስጥ ሕዝቧን ሁሉ አስተባብራ የገነባችው ወደ 80 ያህል ግድብ ነው። ዛሬ ላይ ወደ 660 ቢሊዮን ሜትር ኪዩብ አካባቢ ውሃ አጠራቅማ ይዛለች። ስለዚህ አደጉ የምንላቸው ሀገሮች የእድገታቸው መነሻ ሲታይ ውሃ የማጠራቀሙ ጉዳይ ነው። ሕንድን ደግሞ አረንጓዴው አብዮት (ግሪን ሪቮሉሽን) ብለው እንደ ዘመቻ የሄዱበት ትልቁ እመርታቸው ውሃን አጠራቅመው ወደ ምግብና ኢነርጂ መቀየር ነው። በዛም አቅማቸው ወደ 240 ቢሊዮን ሜትር ኪዩብ ውሃ አካባቢ ማጠራቀም ችለዋል። ይህም ልማታቸውን አፋጥኖታል ብለዋል።

ወደየትኛውም ሀገር ስናማትር እድገትን ማፋጠን የሚቻለው የውሃ ሀብትን ማጠራቀምና መጠቀም ሲቻል ነው ያሉት ዶክተር በለጠ፣ እኛም ውሃ የማጠራቀም አቅማችንን መቀየር ያስፈልገናል ብለዋል። በእኛ ሁኔታ ሲታይ ዓባይ ግድባችንን 74 ቢሊዮን ሜትር ኪዩብ ጨምሮ አሁን ያለው የማጠራቀም አቅማችንን 100 ቢሊዮን ሜትር ኪዩብ አካባቢ ሊወስደው ይችላል በማለትም ገልጸዋል። እንደዛም ሆኖ በኢትዮጵያ የውሃ ሀብት ይጠራቀም ከተባለ ብዙ የማጠራቀሚያ ቋቶች ሊሠሩ እንደሚገባ አስገንዝበዋል።

እንደ አንድ የውሃ ባለሙያ ያለንን ውሃ በበቂ ሁኔታ እየተጠቀምንበት ነው የሚል እምነት የለኝም ሲሉ የገለጹት ዶክተሩ፣ ኢትዮጵያ እስካሁን ባለው አካሄዷ በቂ ዝናብ እያላት በቂ ውሃ ግን የሌላት ሀገር መሆኗን ተናግረዋል። ያላት የዝናብ ውሃ ተይዞ በአግባቡ ወደ ምግብና ኢነርጂ ካልተቀየረ ውሃ ጥቅም እየሰጠ ነው አይባልም። ሃይድሮሎጂ በሚባለው በውሃ ፍሰት ጥናት አኳያ ሲታይ የሁሉም ውሃ ምንጮች ዝናብ ነው እንደሆነ ተናግረው፤ ይህ ዝናብ የሚሰጠን ውሃ ደግሞ የተወሰነው ወደ መሬት የሚሰርግ ነው። ወደ መሬት የሚሰርገው ውሃ የመሬቱ ሁኔታ ካገዘው የከርሰ ምድር ውሃ ሆኖ ይጠራቀማል። ካልሆነ ግን የሚሆነው የገጸ ምድር ውሃ ነው ብለዋል። የገጸ ምድር ውሃ ደግሞ በወንዞቻችን ወጥቶ የሚሄድ ሲሆን፣የእኛ ወንዞች ደግሞ በአብዛኛው በባህሪያቸው ወሰን ተሻጋሪ ናቸው ሲሉ አብራርተዋል።

# በሰባት ወራት...

ከ1ኛው ገጽ የዞረ

ብር የጡረታ መዋጮ መሰብሰብ ችሏል። ይህም ካለፈው ዓመት ተመሳሳይ ወቅት ጋር ሲነጻጸር የአራት ቢሊዮን ብር ብልጫ አለው።

እንደ አቶ አሰፋ ገለጻ፤ የሀገር መከላከያ ሠራዊትና የጸጥታ አካላትን ሳይጨምር በአጠቃላይ ሁለት ነጥብ አምስት ሚሊዮን የመንግስት ሠራተኞች የጡረታ መዋጮ እየከፈሉ ይገኛል። 645 ሺ ዜጎች ደግሞ ጡረታ እየተከፈላቸው ሲሆን ባለፉት ሰባት ወራት ለጡረተኞች ስምንት ቢሊዮን ብር መክፈል ተችሏል።

በ2015 ግማሽ በጀት ዓመት ብቻ ተቋሙ አዳዲስ ጡረታ ተከፋይ የሆኑ 25ሺህ 600 ዜጎችን መመዝገቡንም አቶ አሰፋ ተናግረዋል።

ከመንግሥት ሠራተኞች በጡረታ መዋጮ የሚሰበሰበውን ገንዘብ በትርፋማ መንገድ ለመጠቀም ተቋሙ የተለያዩ የልማት ፕሮጀክቶችን ቀርጾ እየሠራ ይገኛል ያሉት አቶ አሰፋ፤ የተለያዩ አክሲዮኖችን በመግዛት ከሚገኘው ጥቅም ለተሻለ አገልግሎት ለማዋል እየሠራን እንገኛለን ብለዋል።

አስተዳደሩ ሁለት ነጥብ አምስት ቢሊዮን ብር በላይ እያስገነባ የሚገኘው ሕንፃ በቅርቡ ተመርቆ አገልግሎት እንደሚሰጥ ጠቁመው፤ ከማዕከል ባለፈ በተለያዩ የሀገሪቱ ክፍሎች አዳዲስ የንግድ ሕንጻዎችን እያስገነባ መሆኑን አስታውቀዋል።

በሐረር፣ በጅማ፣ በሐዋሳ እና በባሕር ዳር ለንግድ ሥራ የሚውሉ የተለያዩ የሕንፃ ግንባታዎችን እያከናወነ ይገኛል። ይህም ድርጅቱን አትራፊ ከማድረግ በተጨማሪ ለሀገሪቱ ኢኮኖሚ ዕድገትና ለሥራ እድል ፈጠራ ትልቅ ሚና ይጫወታል ብለዋል።

በኅዳር ወር 2015 ዓ.ም አስተዳደሩ በሲቪል ሰርቪስ ከመተዳደር ወጥቶ ራሱን እንዲችል በመደረጉ የተለያዩ ፕሮጀክቶችን በመንደፍ ለሚያከናውናቸው የልማት ሥራዎች ውጤታማነት ምቹ ሁኔታ እንደሚፈጥር ገልጸዋል።

መሥሪያ ቤቱ አሠራሩን ቀልጣፋና የተሟላ አገልግሎት እንዲሰጥ ለማድረግ የሚረዳ የሶፍትዌር ሲስተም ገዝቶ ለመጠቀም በዝግጅት ላይ መሆኑን ዳይሬክተሩ አስረድተዋል።

ዘመናዊና ቀልጣፋ አገልግሎት ለመስጠት ከሚደረገው ጥረት ባሻገር በተለያዩ ተቋማት በኩል ተገቢውን የሠራተኞች መረጃ ያለመስጠትና ትክክለኛ ማስረጃ ያለማቅረብ ችግሮች ለተቋሙ ዕድገት መሆናቸውን ጠቁመዋል።

የጡረታ መዋጮ በአግባቡ አለመሰብሰቡ ገንዘቡን መልሶ ለኢንቨስትመንት ለማዋልና ትርፋማ ለመሆን የሚደረገውን ጥረት የሚያደናቅፍ በመሆኑ የሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት ይህንን ተረድተው በወቅቱ የጡረታ መዋጮ ገንዘብን ለተቋሙ ገቢ እንዲያደርጉ ጥሪ አቅርበዋል።

# የኢትዮጵያ ሚዛን በኃያላኑ ዘንድ

**እስማኤል አረቦ**

ኢትዮጵያ ጥንታዊ ሥልጣኔና ረጅም የመንግሥት ታሪክ ካላቸው ጥቂት ሀገራት አንዷ ናት። ኢትዮጵያ በተባበሩት መንግሥታት ድርጅት የተተካውን ሊግ ኦፍ ኔሺን ከመሰሩት ሃምሳ የሚጠጉ ሀገራትም አንዷ የሆነች፤ እና በዓለም ላይ በሰላም አስከባሪነት እየተመረጠች ሰላምና መረጋጋትን ስታሰፍን የቆየች ስመ ጥር ሀገር ነች።

በርካታ የዓለምም ሆነ የአፍሪካ ሀገራት እንደ ሀገር ከመታወቃቸውና ከመቆማቸው በፊት ኢትዮጵያ ሩቅ ምስራቅ፤ አውሮፓና አሜሪካ ድረስ በመዝለቅ የመንግሥት ለመንግሥት ግንኙነት የመሰረተችና ዝናዋና ቀደምትነቷም በአራቱም የዓለም ማዕዘናት የናኘ ነው። ወደ ቅርብ ጊዜ ታሪኳ ብንመጣ እንኳን በዓድዋ ተራሮች ቅኝ ገዚዎችን አሳፍራ የመለሰችና የነጻነት አኩሪ ኮከብ ሆና እስከ ዛሬ የዘለቀች ሀገር ነች፡፡

ይህ አኩሪ ተጋድሎዋም በአፍሪካውያን ዘንድ የነጻነት አርማ ተደርጋ የምትወሰድ ብቻ ሳትሆን፤ ለአፍሪካውያን የላቀ ነጻነት እውን እንዲሆን በብርቱ ለተደከመበት ለቀድሞው አፍሪካ አንድነት ለአሁኑ አፍሪካ ህብረት ድርጅት መመስረት እርሾ ሆኖ አገልግሏል። ከዚህ ባሻገርም ኢትዮጵያ ቀጣናዊ ትስስሮችን የሚያጠናክሩ ታላላቅ ተቋማትን በመመሥረት ጭምር በዓለም ዲፕሎማሲ መድረክ ጉልህ ሚና ስትጫወት የቆየች አገር ናት፡፡

ከተባበሩት መንግሥታት ድርጅት እስከ ኢጋድ ድረስ የዲፕሎማሲ አሻራዋን ያሳረፈችባቸው ተቋማት በርካታ ናቸው። ለዓለምና ቀጣናዊ ሰላም መስፈን ጦር ማሰማራትን ከማንም ቀድማ የጀመረችው ኢትዮጵያ፣ እንደ ጎረቤት ሶማሊያ ያሉ አገሮች በእግራቸው እንዲቆሙ ለማስቻል ብዙ መስዋዕትነትም የከፈለች ሀገር ነች። የዓለም ሰላም ስጋት የሆነውን ሽብርተኝነት በመዋጋት ረገድም ግንባር ቀደም ሚና ትጫወታለች፡፡

ከዚሁ ጎን ለጎንም ኢትዮጵያ በምስራቅ አፍሪካ ያላት አቀማመጥ፤ የሕዝብ ብዛት፤ እያደገ ያለ ኢኮኖሚ ባለቤት መሆኗ፣ እንዲሁ በቀጣናው ያላት ተጽዕኖ ፈጣሪነትና ተደማጭነት በዓለም አቀፍ ፀጥታና ደኅንነት ጂኦ ስትራቴጂካዊ ተፈላጊነት ያላት አገር ያደርጋታል። ኢትዮጵያ ቀጣናዊ የመሰረተ ልማት ትስስር በሚፈጥሩ የጋራ በሆኑ የባቡር፣ የመንገድና የወደብ ፕሮጀክቶች ግንባታ ላይ የነቃ ተሳትፎ ከማድረግ በተጨማሪ፣ ለቀጣናው የኃይል አቅርቦት ዋና ምንጭ በመሆን ትልቅ አስተዋጽኦ እያደረገች ነው። የአፍሪካ ሀገራት ከስንዴ ጠባቂነት እንዲላቀቁና በራሳቸው እንዲቆሙ ስንዴን አምርታ ለጎረቤት ሀገራት ጭምር ገበያን የከፈተች ሀገር ነች፡፡

እነዚህ ሁሉ ኢትዮጵያን በአፍሪካ ግንባር ቀደም ሀገር የሚያደርጓት ናቸው። ትናንት በደም እና በአጥንት ከራሷ አልፎ ለሌሎችም ነጻነት ዘብ እንደቆመች ሁሉ ዛሬም በልማቱ ዘርፍ ከፊት ቀድማ ተገኝታለች። ታዲያ በዚህ ሁሉ ጉዞዋ ውስጥ ያላትን ተጽዕኖ ፈጣሪነትና ተደማጭነት ከግምት ውስጥ በማስገባትም ኢትዮጵያን የአፍሪካ መግቢያ በር አድርገው የሚወስዱም በርካቶች ናቸው። አፍሪካ ምን እንደምትፈልግ ለማወቅ ኢትዮጵያን ጠይቅ ሲሉም ይደመጣሉ፡፡

እነዚህ ሁሉ ሲደማመሩ ኢትዮጵያ ከምስራቅ አፍሪካ ቀጣና አልፋ በአፍሪካ ተደማጭ ሀገርና በኃያላኑ ሀገራትም ዘንድ ከፍ ያለ ግምት የሚሰጣት እና የአፍሪካ ዲፕሎማሲ የስበት ማዕከል እንድትሆንም አስችሏታል። የቅርብ ጊዜውን እንኳን ብንመለከት ኢትዮጵያ የበርካታ ኃያላን ሀገራትን ቀልብ መሳቧን በቀላሉ መገንዘብ ይቻላል። ቻይና፤ ራሽያ፤ አሜሪካ እና የተባበሩት መንግሥታት ሳይቀር ኢትዮጵያን ደጋግመው ሲገበኙ ተስተውለዋል።

ኢትዮጵያ በማንም አገር የውስጥ ጉዳይ ጣልቃ ያለ መግባትና ለዓለም አቀፋዊ ሰላምና ደኅንነት በጋራ የመቆም የጥንት የውጪ ግንኙነት ፖሊሲዋን በማስቀደም ዲፕሎማሲዋን ስትመራ የቆየች ሀገር ነች።

ቻይና በየካቲት 2014 ዓ.ም. አንጋፋ የተባሉትን ዲፕሎማት ዡ ቢንግን የአፍሪካ ቀንድ ልዩ መልዕክተኛ አድርጋ ከሾመች በኋላ፣ ከሰኔ 20 እስከ 21 2014 ዓ.ም. ለመጀመሪያ ጊዜ የአፍሪካ ቀንድ የሰላም ኮንፈረንስ በአዲስ አበባ ማዘጋጀቷ ይታወሳል። ዡ ቢንግ መጋቢት 2014 ዓ.ም. ኢትዮጵያን በጎበኙበት ወቅት ቻይና የአፍሪካ ቀንድ አገሮችን የደኅንነት፣ የልማትና የአስተዳደር ችግሮችን ለመፍታትና አንድነትን ለማጎልበት አብራ እንደምትሠራ መግለጻቸውንና ኢትዮጵያ በአፍሪካ ቀንድ የቀጣናው ወሳኝ አገር መሆኗን መናገራቸውን በወቅቱ ተዘግቦ ያለፈ ጉዳይ ነው፡፡

> **ኢትዮጵያ በየዘመናቱ የሚያጋጥሟትን ሰው ሰራሽና የተፈጥሮ አደጋዎችን ለመሻገር የምታደርገውን ጥረት በማገዝ ቻይና የበኩሏን እገዛ ስታደርግ ቆይታለች። ለአብነትም ዓለም አቀፍ ወረርሽኝ የሆነውን ኮቪድ 19 በመከላከሉ ረገድ ቻይና ያደረገችው ድጋፍ የሚዘነጋ አይደለም**

ቻይና ከኢትዮጵያ ጋር ያላት ዲፕሎማሲያዊ ግንኙነት የጠነከረና ከየትኛውም ሀገር ቅድሚያ የምትሰጠው መሆኑን ያረጋገጠቸው በቅርቡ የቻይና የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር ሆነው የተሾሙት ቺን ጋንግ በሥልጣን ዘመናቸው የመጀመሪያ የሆነውን ይፋዊ የሥራ ጉብኝት በኢትዮጵያ ካደረጉ በኋላ ነው፡፡

የኢትዮጵያና የቻይና ግንኙነት ከግማሽ ክፍለ ዘመናት በላይ የተሻገረ ነው። በእነዚህ ዓመታትም ሁለቱ ሀገራት የሕዝቦቻቸውን ጥቅም የሚያስከብሩ ተግባራት ከማከናወናቸውም ባሻገር የእርስ በእርስ መተሳሰብንና መተማመንን በማስቀደም ተምሳሌታዊ ግንኙነት መፍጠር ችለዋል፡፡

ኢትዮጵያ በየዘመናቱ የሚያጋጥሟትን ሰው ሰራሽና የተፈጥሮ አደጋዎችን ለመሻገር የምታደርገውን ጥረት በማገዝ ቻይና የበኩሏን እገዛ ስታደርግ ቆይታለች። ለአብነትም ዓለም አቀፍ ወረርሽኝ የሆነውን ኮቪድ 19 በመከላከሉ ረገድ ቻይና ያደረገችው ድጋፍ የሚዘነጋ አይደለም። እንደ አብነት ለማንሳት፣ የቻይና መንግሥት ኢትዮጵያ እያካሄደች ላለችው የጸረ ኮቪድ 19 ዘመቻ ከ 12 ነጥብ 2 ሚሊዮን ዶዝ በላይ መድሃኒት በመለገስ ለኢትዮጵያ ሕዝብ ያለውን ወገንተኝነት ማሳየት ችሏል፡፡

የኢትዮጵያ መንግሥት በበኩሉ ቻይና በኮቪድ ወረርሽኝ በተጠቃችበትና በዚሁ ምክንያትም መላው ዓለም ወደ ቻይና በረራ በሰረዘበት ወቅት በብቸኝነት በረራ በማድረግ በችግር ጊዜም ቢሆን የቻይናና ኢትዮጵያ ሕዝብ እንደማይለያዩ ያስመሰከረበት ታሪካዊ ሁነት መቼም የሚረሳ አይደለም። በወቅቱም የዓለም ሀገራት ወደ ቻይና በረራ ባቆሙበት ወቅት የኢትዮጵያ መንግሥት በብቸኝነት የወሰደው እርምጃ ከቻይና መንግሥትና ሕዝብ አድናቆት የተቸረው እንደነበር የሚታወስ ነው፡፡

ኢትጵዮጵያ በየጊዜው የሚያጋጥሟትን ሰብአዊ ቀውሶች በማቃለል ረገድም የቻይና መንግሥት ድጋፍ የማይነጥፍ ነው። በተለይም በሰሜኑ የሀገሪቱ ክፍል በነበረው ጦርነት ለተጎዱ ዜጎች የቻይና መንግሥት ከ30 ሚሊዮን የቻይና ዩዋን በላይ ድጋፍ አድርጓል። ከዚሁ ጎን ለጎንም ኢትዮጵያ ለምታከናውናቸው የተለያዩ ልማቶችንም በመደገፍ የቻይና መንግሥት ተኪ የሌለው ተግባር በመፈጸም ከፍ ያለ ድጋፍና አጋርነቱን ማረጋገጥ ችሏል፡፡

የቅርቡን እንኳን ብንመለከት በአዲስ አበባ እየተከናወኑ የሚገኙትን የአረንጓዴ ልማትና አካባቢ ማስዋብ ስራዎችን በመደገፍ ረገድ የቻይና መንግሥት የማይተካ ሚና እየተጫወተ ይገኛል። ግዙፉ የንግድ ባንክ ህንጻና የሳይንስ ሙዚም ግንባታዎች የቻይና መንግሥት አሻራ ያረፈባቸው ድንቅ የልማት ውጤቶች ናቸው። በአዲስ አበባ ከተማ 90 ሺህ ሜትር ስኩዌር የሚሸፍን ቦታ ላይ ዘመናዊ የሆነ የአፍሪካ የበሽታ መቆጣጠሪያ ማዕከል ዋና መስሪያ ቤት እየገነባ የሚገኘውም በቻይና ድጋፍ ነው።

ኢትዮጵያ በለውጥ ጎዳና ውስጥ በገባችባቸው ባለፉት አራት ዓመታት ውስጥም ዘመናዊ ቴክኖሎጂ መሰረት እንዲጥልና የህዋ ምርምር እንዲዳብር ቻይና ያልተቆጠበ ድጋፍ አድርጋለች። የቻይና መንግሥት ከ250 ሚሊዮን ብር በላይ ድጋፍ በማድረግ ETRSS-1 እና ET-Smart-RSS የተሰኙ ሳተላይቶችን ኢትዮጵያ እንድታመጥቅ በማድረግ አጋርነቱን አሳይቷል፡፡

እንደ ቻይና ሁሉ ከኢትዮጵያ ጋር ጠንካራ የዲፕሎማሲ ግንኙነት ካላቸው ሀገራት አንዷ ራሺያ ናት። የፖለቲካ ማዕቀብ ውጥኖችን አመክንዮያዊ በሆነ አካሄዷ በመቃወምና ሁልጊዜም ቢሆን ከኢትዮጵያ ጎን በመቆም የምትታወቀው ሩሲያ አንጋፋውን የውጭ ጉዳይ ሚኒስትሯን ሰርጌይ ላቭሮቭን ጨምሮ የተለያዩ ባለሥልጣኖቿን ወደ ኢትዮጵያ ደጋግማ በመላክ ትታወቃለች። ሩስያ በሁለተኛው የዓለም ጦርነት ጭምር ከኢትዮጵያ ጎን ስትሰለፍ የቆየች ሀገር ከመሆኗም ባሻገር በህዳሴ ግድብ ግንባታ ሒደት ላይ የሚስተዋሉ አለመግባባቶች መፈታት ያለባቸው፣ በመነጋገርና በአፍሪካ ኅብረት አደራዳሪነት ብቻ መሆኑን ያለማመንታት ሃሳቧን በመግለጽ ትታወቃለች። በእነዚህና ሌሎችም ማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊ እና ዲፕሎማሲያዊ መስኮች ከፍ ያለ ግንኙነትና አጋርነቷን ሲትገልጽ፤ ያልተቋረጠ ድጋፏንም ስታደርግ የቆየች አጋር አገር ናት፡፡

እንደ ቻይናና ራሺያ ሁሉ፣ የኢትዮጵያና የአሜሪካ ግንኙነትም ዘመናትን የተሻገረ ነው። መረጃዎች እንደሚያሳዩትም የሁለቱ ሀገራት ግንኙነት ከ አንድ መቶ ዓመታት በላይ አስቆጥሯል። በአንድ ወቅትም አሜሪካ በዓለም ላይ ካሏት ጠንካራ አጋሮች መካከል ኢትዮጵያ በሶስተኛ ደረጃ ተቀምጣ እንደነበር መረጃዎች ይጠቁማሉ። በተለይም በንጉሱ ዘመን ኢትዮጵያ እንደ ዋነኛ የአሜሪካ አጋር የምትወሰድና በዚሁ ምክንያትም በተለይ በሚሊቴሪው ዘርፍ አሜሪካ ጠንካራ ድጋፍ ስትሰጥ ቆይታለች፡፡

ቀጥሎ የመጣው የደርግ መንግሥት ይከተለከው በነበረው ርዕዮተ ዓለም የሁለቱ ሀገራት ግንኙነት ተቋርጦ የቆየ ቢሆንም የኢህአዴግ መንግሥት ሥልጣን ከያዘ በኋላ ግንኙነቱ እንደገና ታድሶ የተሻለ ደረጃ ላይ ደርሶ ነበር። በሰሜኑ የኢትዮጵያ ክፍል የነበረውን ግጭት ተከትሎ ግን የኢትዮጵያ እና የአሜሪካ መንግሥታት ግንኙነት ዳግም መሻከር የታየበትና የአፍሪካ ሀገራት ከቀረጥ ነጻ በሆነ መልኩ ሸቀጦቻቸውን እንዲያስገቡ ከፈቀደችው የንግድ ዕድል ኢትዮጵያ እንድትሰረዝ እስከማድረግ የደረሰ ነበር።

ሆኖም ኢትዮጵያ በማንም አገር የውስጥ ጉዳይ ጣልቃ ያለ መግባትና ለዓለም አቀፋዊ ሰላምና ደኅንነት በጋራ የመቆም የጥንት የውጪ ግንኙነት ፖሊሲ ላይ በመመስረትም በጦርነቱ ወቅት ጭምር ከአሜሪካ ጋር ያላት ዲፕሎማሲያዊ ግንኙነቱ እንዳይበላሽ በብዙ ስትጥር ቆይታለች፡፡

ይህም ጥረቷ ፍሬ አፍርቶ ጥቅምት 23 ቀን 2015 በኢትዮጵያ መንግሥትና በሕወሓት መካከል በፕሪቶሪያ የሰላም ስምነት ከተደረሰ በኋላ የሁለቱ ሀገራት ግንኙነት መጠነኛ ለውጥ አሳይቷል። በሂደትም የኢትዮጵያ መንግሥት የሰላም ስምምነቱን ለመተግባርና የሰብአዊ ድጋፍ አገልግሎቱ በአግባቡ እንዲዳረስ እያደረገው ያለው ድጋፍ በአሜሪካውያኑ ዘንድ በጎ ምላሽ አስገኝቷል። ይህ ደግሞ የአሜሪካ የውጭ ጉዳይ ቢሮ ኃላፊ አንቶኒ ብሊንከን ለይፋዊ የሥራ ጉብኝት ሰሞኑን አዲስ አበባ እንዲገኙ አድርጓቸዋል። የብሊንከን ጉብኝት ከጦርነቱ መቆም በኋላ በከፍተኛ የአሜሪካ መንግሥት ባለሥልጣን የተደረገ የመጀመሪያው ጉብኝት ነው።

የኢትዮጵያ መንግስት የሰሜኑ ጦርነት እንዲቋጭና ይህንኑ ተከትሎም የሰብአዊ ዕርዳታ በአግባቡ እንዲዳረስ፤ የተቋረጡ መሰረተ ልማቶች መልሰው አገልግሎት መስጠት እንዲጀምሩ እና የሕዝብ ለሕዝብ ግንኙነት ወደ ነበረበት እንዲመለስ በማድረግ ረገድ ዘርፈ ብዙ ተግባራትን አከናውኗል። በሌላም በኩል በሁሉም ወገን የተፈጸሙ በደሎች ለመካስ የሚያስችል የሽግግር ፍትህ ለመተግበር በሂደት ላይ ነው። ይህ ደግሞ በአጠቃላይ ለሰላም ያለውን ቁርጠኝነት የሚያመላክት በመሆኑ በጦርነቱ ምክንያት ተበላሽቶ የነበረው የአሜሪካ እና የኢትዮጵያ መንግሥታት ግንኙነት ወደ ቀድሞው ቦታው እንዲመለስ የሚያስችል ነው፡፡

ኢትዮጵያ በምስራቅ አፍሪካ የአሜሪካ ዋና አጋር ሆና ዘመናትን ዘልቃለች። በዚህም ሁለቱ ሀገራት የጋራ ተጠቃሚነትን ባማከለ መልኩ ዲፕሎማሲያዊ ግንኙነታቸውን ሲመሩ ቆይተዋል። በተለይም በምስራቅ አፍሪካ ዋነኛ ስጋት የሆነውን ሽብርተኝነትን በመዋጋት ረገድ ሁለቱ ሀገራት ለዓመታት ያህል ተጨባጭ ስራ ሲሰሩ ቆይተዋል። ምስራቅ አፍሪካ የሽብርተኞች መናኸርያ እንዳይሆን ኢትዮጵያ እየተጫወተችው ያለው ሚና አካባቢውን በትኩረት ለምትከታተለው አሜሪካ ትልቅ ትርጉም ያለው ነው። በሌላም በኩል ኢትዮጵያ ወደ ተለያዩ ሀገራት ሰላም አስከባሪ ሠራዊቷን በመላክ በአፍሪካ ብሎም በዓለም ሰላም እንዲሰፍን የበኩሏን ሚና የምትጫወት ሀገር ነች፡፡

ሆኖም ኢትዮጵያ በሁለንተናዊ መልኩ ያላትን ሚና በአግባቡ እንድትወጣ ደግሞ የተረጋጋ ሰላምና የተጠናከረ ኢኮኖሚ ያስፈልጋታል። ለዚህ ደግሞ አንቶኒዮ ብሊንከን አዲስ አበባ ተገኝተው ካበረከቱት 331 ሚሊዮን ዶላር የሰብዓዊ ድጋፍ በተጨማሪ ከዓለም አቀፍ ተቋማት ብድርን ማመቻቸት፣ ያለባትን የዕዳ ክፍያ ጊዜ ማሸጋሸግ፣ በጦርነቱ መዘዝ የተነፈገቻቸውን እርዳታዎች እና የበጀት ድጎማዎችን እንዲሁም ወደ አጎዋ የቀረጥ እና ታሪፍ ነጻ ንግድ መመለስ ከአሜሪካ የሚጠበቁ የቤት ስራዎች ናቸው፡፡

ምክንያቱም ኢትዮጵያ፣ በምሥራቅ አፍሪካ የመልክዓ ምድራዊ አቀማመጧና ካላት ተደማጭትና ትልቅ ቀጣናዊ ተዋናይነትና የአፍሪካ መግቢያ ተብላ የምትጠራ ከመሆኗ አኳያ በአሜሪካ፣ በቻይና፣ በሩሲያ እንዲሁም በአረብና በገልፍ ሀገራት ጭምር በከፍታ የምትታይ ሀገር ነች። እያደገ ያለው ኢኮኖሚዋና የሕዝብ ቁጥሯ እንዲሁም ጂኦፖለቲካ አቀማመጧ ሀገሪቱን በቀጣይም ቢሆን ተመራጭ ያደርጋታል። ይህ ደግሞ በኢኮኖሚም ሆነ በፖለቲካ ረገድ የአካባቢው ኃያል ሀገር ሆና እንድትወጣ በር ይከፍታል፡፡

ሆኖም እኛ ኢትዮጵያውያን የሀገራችንን ዋጋ የተረዳነው አይመስልም። በጎሳ፣ በብሄርና በኃይማኖት በመከፋፈል ከከፍታዋ አውርደን ልናሳንሳት ስንሞክር እንታያለን። ሌሎች ያከበሯትን እኛ ልጆቿ ልናዋርዳት እየጣርን ነው። ሌሎች ወደ ኢትዮጵያ መጥተው በነጻነቷ ሀገር ለመኖር ሲመኙ እኛ እርስ በእራሳችን በምናደርገው ግብግብ ለሁላችንም የማትሆን ሀገርን ለመፍጠር እሽቅድድም ከጀመርን ውለን አድረናል። ስለሆነም የሀገራችንን ዋጋ እንገንዘብ። ኢትዮጵያ ብዙዎች የሚመኙዋት፤ ብዙዎች ከፍታዋን የተረዱት ፤ ብዙዎች መስዋዕት የሚከፍሉላት ሀገር ነችና የሀገራችንን ዋጋ እንረዳ፡፡

ማህበራዊ

# የሕይወት ገጽታ

# ከብሄራዊ ባንክ ገዢነት እስከ ጠቅላይ ሚኒስትር አማካሪነት

**እፀገነት አክሊሉ**

ትናንት በጉርምስናና ጉልምስና እድሜያቸው ላይ አገራቸውን በብዙ ያገለገሉ ጀግኖች ዛሬ ላይ ቀን ዘምበል ሲልባቸው ፤ ጎንበስ ቀና ይሉላቸው የነበሩ ሁሉ የት እንዳሉ እንኳን በውል እያወቋቸው አይደለም። ጊዜ እራሱ አድሎ የሚፈጽም እስከሚመስል ድረስ ለአገር ለወገን ብዙ የዋሉ ሰዎች ሳይታዩ ሳይከበሩ መከበሩ ቀርቶ ለኑሯቸው እንኳን አስፈላጊ ነገር ሳይሟላላቸው በአሳዛኝ ሁኔታ እድሜያቸውን እንዲጨርሱ በለፉባት አገርና ሕዝብ ዘንድ ዋጋ ቢስ ሆነው ተስፋ ሲቆርጡ መመልከት የተለመደ እየሆነ ነው፡፡

የዛሬ የሕይወት ገጽታ ዓምዳችን ባለታሪካችን በእውቀት የገፉ ለትልልቅ አገራዊ ሃላፊነቶች ታጭተው በብቃት የተወጡ ናቸው። ሮጠው መስራት በስራቸው ያሉትንም በሚገባ መምራት በሚችሉበት ቁመናና የጤና ሁኔታ ላይ ሆነውም አገራቸውን በብዙ ያገለገሉ ጀግና ናቸው። ምን ዋጋ አለው ፤ ሰርተው ሳይጠግቡ ያስተማረቻቸው አገርም በቅጡ ሳትጠቀምባቸው ጤና ይሉት ገበያ ዘንበል ብሎባቸው ቤት ከዋሉ ዓመታት ተቆጥረዋል፡፡

ትውልዳቸው በ1951 ዓ.ም ጥቅምት 1 ቀን በምዕራብ ወለጋ ጊምቢ ገንጂ ወረዳ ሲሆን እድገታቸውም እዛው አካባቢያቸው ላይ ነው። እድሜያቸው ለትምህርት ሲደርስም በአቅራቢያቸው ባለ አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ትምህርታቸውን ተምረዋል፡፡

"......አባቴ ባይማርም ለትምህርት ልዩ ፍቅር ስለነበረው ደጋግሞ ተማር ብታጣ እንኳን እንደ ቆሎ ተማሪ ለምነህ ተማር ፤ ኋላ እዚህ ገጠር ነው የምትቀረው" ብሎኝ ነበር የሞተው። በማለትም መለስ ብለው የልጅነት ጊዜያቸውን አልፎ ተርፎም አባታቸው ለእሳቸው በእውቀት መጎልመስ ብሎም እውቀታቸውን ለአገራቸው እድገት እንዲያውሉ ያሳዩዋቸውን መንገድ ይናገራሉ። ይህ ምክር ደግሞ መሬት አልወደቀም ፤ ይልቁንም የመማር ፍላጎታቸውን በከፍተኛ ሁኔታ ጨመረው እንጂ።

ምንም እንኳን መብራት እንዲሁም መንገድ በሌለባት ጊምቢ ወረዳ ቢወለዱም ትምህርት የሁሉ ነገር ብርሃን ነው ብለው በማመን በሳምንት አርብ አርብ ስንቅ ከቤተሰቦቻቸው ለማምጣት 61 ኪሎ ሜትር በእግራቸው ተጉዘው ገንጂ ወረዳ እየሄዱ ተምረዋል። ይህ የእውቀት ፍላጎታቸውም ሳያሳፍራቸው እስከ ጠቅላይ ሚኒስቴር አማካሪነት ድረስ የደረሱ ጀግና ኢትዮጵያዊ ናቸው አቶ ዱባለ ጃሌ፡፡

"...61 ኪሎ ሜትር የምንጓዘው ከጓደኞቼ ጋር ነበር። ስንሄድ እንዲሁ ዋዛ ፈዛዛ እያወራን የምንሄድ እንዳይመስልሽ ፤ ይልቁንም ትምህርታችንን እያጠናን ጥያቄ እየተጠያየቅን ፤ በመካከልም እየሳቅን እየተጫወትን ብቻ ያ ሁሉ መንገድ ምንም ሳይመስለን በአጭር ሰዓት ውስጥ ነበር ተጉዘን የምንገባው" በማለት በትዝታ ተጉዘው ይናገራሉ፡፡

በትምህርታቸው እጅግ በጣም ጎበዝ ተማሪ የነበሩት አቶ ዱባለ በወቅቱ አብረዋቸው ይማሩ የነበሩ ሰዎች ዛሬም ድረስ ይጠያየቃሉ። ብዙዎቹም እንደሳቸው በጣም ጎበዝ ተማሪ ስለነበሩ በትልልቅ የመንግሥት የስራ ሃላፊነት ላይ የሚገኙም ስለመሆናቸው አቶ ዱባለ ይናገራሉ፡፡

"...ሂሳብ ትምህርትን በፍቅር ነበር የምወደው፤ አልጄብራው ኧረ ምኑን ልንገርሽ በጣም እወድ ነበር፤ በነገራችን ላይ ሂሳብና እንግሊዝኛ የማይችል ሰው ሌላውንም ትምህርት አይችልም የሚል የራሴ የሆነ ድምዳሜም አለኝ፤ ብቻ በአጠቃላይ የሂሳብ ትምህርት በጣም እወድ ነበር፤ ኋላም እንጀራዬ ሆነ" ይላሉ፡፡

አቶ ዱባለ ጃሌ ከዚህ ሁሉ ውጣ ውረድ የተሞላበት የአንደኛና ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት በኋላ 12ኛ ክፍል ማትሪክ ተፈትነው 3 ነጥብ 8 በማምጣት አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የመግባት እድልን አገኙ። የደሃው ልጅ አቶ ዱባለ ቀድሞም ቢሆን ራሳቸውን ያውቁ ነበርና በተለይም ከፍተኛ ትምህርት ተቋም እንደሚገቡም እርግጠኛ ስለነበሩ ፈተናውን ወስደው በነበረቻቸው ትርፍ ጊዜ በቆሎ ዘርተው አሳድገው በመሸጥ አስፈላጊ ግብዓቶቻቸውን አሟልተው እናታቸውን ሳያስቸግሩ ነው የመጀመሪያ መንፈቅ ዓመት የዩኒቨርሲቲ ትምህርታቸውን ለመከታተል አዲስ አበባ የገቡት፡፡

አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ መግባታቸው አቶ ዱባለ ዛሬ ላይ ሆነው ሲገልጹት ሎተሪ ነው ይላሉ፡፡"..... በወቅቱ አባት የለኝ፤ እናቴ ብቸኛ ናት፤ ሌሎች እህት ወንድሞቼም አሉ፤ በጠቅላላው እኔን እንደ ልቤ ሊያኖረኝ ወይም ሊያስተምረኝ የሚችል አቅም ያልነበረ በመሆኑ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ መግባቴ እንደ ሎተሪ የሚቆጠር ነው። ምግብ መኝታ እዛው ነው። ስለምንም የማስበው ወጪ የለብኝም እኔ የሌሊት ልብስና ደብተሬን ነው ይዤ የሄድኩት ፤ ከዚህ በላይ እድለኝነት ከየት ይመጣል፤" በማለት ሁኔታውን ይገልጻሉ።

አቶ ዱባለና ጓደኞቻቸው ዩኒቨርሲቲ ሲገቡ እሳቸውም እንዳሉት ብዙ ሃሳብ ተቃለለላቸው። ምን ልብላ ?ቤት ኪራይ ከየት አመጥቼ ነው የምከፍለው? ይሉት አይነት ሃሳብ የለባቸውም። ይህ ደግሞ በትምህርታቸው ላይ ይበልጥ እንዲያተኩሩ ከልጅነት ከታችኛው ክፍል ይዘውት የመጡትን የማንበብና የማጥናት ልምዳቸውን በአግባቡና በተገቢው ሁኔታ እንዲጠቀሙበት አደረጋቸው፤ ላቅ ወዳለ ውጤትም አደረሳቸው፡፡

የመጀመሪያ ዲግሪያቸውንም በኢኮኖሚክስ የትምህርት መስክ ያደረጉት አቶ ዱባለ ዛሬም ድረስ በአገሪቱ ትልልቅ የፋይናንስ አመራርነት ላይ የሚገኙት እንደ አቶ ግርማ ብሩ ፣ ሶፊያን አህመድና ሌሎችም ጓደኞቻቸው እንደነበሩ ይናገራሉ።

በ1975 ዓ.ም ከአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ በኢኮኖሚክስ የትምህርት መስክ የመጀመሪያ ዲግሪያቸውን ያገኙት አቶ ዱባለ የሁለተኛ ዲግሪያቸውን በፕላኒንግ የትምህርት መስክ ከዚሁ ዩኒቨርሲቲ አግኝተዋል፡፡

የስራ ዓለምን "ሀ" ብለው የተቀላቀሉት በትራንስፖርት ሚኒስቴር ሲሆን ለአንድ ዓመት ያህል ካገለገሉ በኋላ በ 1975 ዓ.ም ወደ ኮንስትራክሽን ሚኒስቴር በመሄድ ለስምንት ዓመታት ያህልም ሰርተዋል። ከዚህ በኋላ የስራ መዳረሻቸውን ያደረጉት የቀድሞ ጠቅላይ ሚኒስትር መለስ ዜናዊ ቢሮ ነበር። እዛም በአማካሪነት እና በመምሪያ ሃላፊነት የስራ መደቦች ላይ ለአንድ ዓመት ያህል አገልግለዋል፡፡

የአቶ ዱባለ የስራ ትጋትና ፍላጎት እዚህ ላይ የሚያበቃ አይደለም፤ ከጠቅላይ ሚኒስትር ቢሮ እንደወጡ በቀጥታ ያመሩት የልማት ተቋማት ላይ ነበር፡፡"... ከጠቅላይ ሚኒስትር ቢሮ ከለቀቅኩ በኋላ ወደ ልማት ማህበራት ሄድኩ፤ ዋል ኮ አነስተኛ የብድር ተቋም የመጀመሪያ መግቢያዬ ሲሆን በመቀጠልም ፤አሾ ፣ አልማ ቱምሳና ሌሎችንም ወደማቋቋምና ወደ መመስረት ተግባር ውስጥ ገባሁ" ይላሉ፡፡

እነዚህን ተቋም በመመስረት አባላት እንዲኖሯቸው በማድረግና በሁለት እግራቸው ቆመው ህብረተሰቡን እንዲያገለግሉ ካስቻሉ በኋላ አቶ ዱባለ ለከፍተኛ ሃላፊነት ተጠሩ፤ እሱም የብሔራዊ ባንክ ገዢነት ነበር፡፡

አቶ ዱባለ የብሔራዊ ባንክ ገዢ በመሆን ከ1989 እስከ 1994 ዓ.ም ድረስ አገራቸውን አገልግለዋል፡፡

".....የብሄራዊ ባንክ ገዢ ሆኜ የቆየሁበት ጊዜ አስገራሚም አስደሳችም ነበር፤ አስገራሚው ነገር ብሔራዊ ባንክን የሚያክል ግዙፍ ሀብት የሚንቀሳቀስበት ድርጅት ላይ ሰርተህ አሁን ገንዘብ ቸገረኝ ትላለህ ወይ የሚሉኝ አሉ፤ እኔ ደግሞ በዚህ አልስማማም። ምክንያቱም ብሔራዊ ባንክ አጭቆ የያዘው ገንዘብ የሕዝብ እንጂ እኔም ሆንኩ ሌሎች ግለሰቦች እንደፈለጉ የሚፈነጩበት አይደለም። አስደሳቹ ነገር ደግሞ ብሔራዊ ባንክ መስራት ከምንም በላይ ሙያዊ የሆነ ቤት መሆኑ ነው፡፡" በማለት ይናገራሉ፡፡

በተለይም የብሔራዊ ባንክ ገዢ ሆነው በአገለገሉባቸው ዓመታት ዓለም አቀፉን የገንዘብ ድርጅት ጨምሮ በርካታ ለኢትዮጵያ ብድር የሰጡ የዓለም አገሮች ዘንድ በመቅረብ በብድር ቅነሳና ስረዛ ዙሪያ ድርድሮችን ውይይቶችን ስምምነቶችን አድርገዋል። አብዛኞቹንም አሳክተው ተመልሰዋል፡፡

ኢትዮጵያና ኤርትራ መጣላታቸውን ተከትሎ የነበረውን የገንዘብ ለውጥ የቀድሞ ጠቅላይ ሚኒስትር አቶ መለስ ዜናዊ በቢሯቸው ጠርተው የቅያሪውን ሚስጥራዊ ሂደት አማክረዋቸዋል። አቶ ዱባለም የአገራቸውን ምስጢር በልባቸው ይዘው በተባለው መንገድ ስራዎች እንዲሰሩ አድርገው በሚፈለገው ልክ አሳትመው ይፋ መሆን በሚገባው ጊዜ ይፋ በማድረግ ህብረተሰቡ ጋር ያደረሱም ጀግና የአገር ባለውለታ ናቸው።

"...በወቅቱ የነበሩት ሟቹ ጠቅላይ ሚኒስትር መለስ ዜናዊ የሁለቱን አገራት መለያየታቸውን ተከትሎ የኢትዮጵያ ካርታ የቅርጽ ለውጥ በማምጣቱና ገንዘቡ ላይ ያለውም ካርታ እንደወቅቱ መሆን ስለነበረበት ገንዘብ እንዲቀየር አዘዙ ፤ ሌላው ደግሞ ገንዘቦችን አስመስሎ የመስራት ቴክኖሎጂው እንደ አገር ስር እየሰደደ ስለመጣ እሱንም መከላከል በማስፈለጉ ገንዘቡ እንዲለወጥ ታዘዘ፤ ብሔራዊ ባንክም በአዋጅ የተሰጠው ግዴታው ነውና ሃላፊነቱን ተቀበልኩ፤ ካዛም በተባለው መንገድ ምስጢራዊነቱን ጠብቄ ገንዘቡ እንዲለወጥ ኋላም ለህብረተሰቡ እንዲሰራጭ አደረኩ፤ " በማለት የተጣለባቸውን ትልቅ አገራዊ ሃላፊነት በብቃት ስለመወጣታቸው ይናገራሉ፡፡

አቶ ዱባለ የዓለም ባንክና የዓለም አቀፉን የገንዘብ ድርጅት ጨምሮ ሌሎች በፋይናንስ ዙሪያ የሚሰሩ አካላት የተካተቱባቸው በርካታ ጉባኤዎችን ተሳትፈዋል፤ መሳተፍም ብቻ ሳይሆን በድህነት ቅነሳ በስራ እድል ፈጠራ እንዲሁም በሌሎች ጠቃሚ ጉዳዮች ዙሪያ ውይይቶችን አድርገው ለአገራቸው ፍሬያማ የሚባል ውጤትን አምጥተዋል። አገር ያለባት የእዳ ጫናም ይሰረዝ ዘንድ አቶ ዱባለ ወደ ራሺያ ፤ፓሪስ እንዲሁም ሌሎች አበዳሪ አካላት ዘንድ እየተመላለሱ የተወሰኑ ውጤቶችን ማምጣትም ስለመቻላቸው በአንደበታቸው ይናገራሉ፡፡

አቶ ዱባለ ይህንን ሁሉ ለአገር የሚጠቅም ስራ በመስራት የተጣለባቸውን ሃላፊነት በታማኝነት ቢወጡም ይህ ጉዟቸው በተለይም ታማኝነታቸው የጎረበጣቸው አንዳንዶች ደግሞ ከቦታው እንዲነሱ የራሳቸውን ጥረት ማድረግ ጀመሩ። "...በወቅቱ እኔ ከብሔራዊ ባንክ ለመነሳቴ ብዙ ምክንያቶች ቢኖሩም ዋናው ነገር ግን በተለይም ለበላተኞች ምቹ አለመሆኔ ነው። ብዙ ሰዎች ብሔራዊ ባንክ ተከማችቶ የሚገኘው ገንዘብ ባለቤት የሌለው ይመስላቸዋል፤ ከዚህ አንጻርም እንዳሻቸው ለማድረግ ይፈልጋሉ፤ እኔ ደግሞ በዚህ አልስማማም ምክንያቱም ገንዘቡ ባለቤት አለው። ነገር ግን የገንዘቡ ባለቤት ወደጎን ተገፍቶ የተወሰኑ ሰዎች ለድርጅታቸው ላቋቋሙት ተቋም ለክልላቸው ብቻ ገንዘብ ለሚፈልግ እንቅስቃሴዎች ሁሉ ብር አምጣ የምባልበት ደረጃ ላይ ተደረሰ። የገንዘቡ ምንጭም እኔን አደረጉኝ እኔ ደግሞ ለተሰጠኝ ሃላፊነት ታማኝ መሆን ስለነበረብኝ አሻፈረኝ አልችልም የሕዝብ ገንዘብ መዝረፍ የሚፈልግ ሰው ሌሎች አማራጮችን ይፈልግ እንጂ እኔ በዚህ ውስጥ አልገባም ብዬ እምቢ አልኩ፤ እነሱም ተመካክረው ይህ ሰው አጋር አይሆነንም ብለው አስወጡኝ " በማለት ስለሁኔታው ያብራራሉ፡፡



ፎቶ:አሸናፊ ጉደታ

አቶ ዱባለ ጃሌ

**"...በነገራችን ላይ ብሔራዊ ባንክ የሰራሁት በምን ያህል ደመወዝ እንደሆነ ታውቂያለሽ? በ 2ሺ500 ብር ነው። 1 ሺ 900 ብር እጄ ይገባል፤ በዚህ ደመወዝ ቤተሰብ አስተዳድሬ ልጆቼን አስተምሬ ነው የኖርኩት**

ማህበራዊ

# የሕይወት ገጽታ



የአምስት ዓመት የባንክ ገዢነት ስራቸውም በዚህ መልኩ ከተጠናቀቀ በኋላ አቶ ዱባለ ዝም ብለው አልተቀመጡም፤ ይልቁንም በተከበረው ሙያቸው ሰርተው ማግኘት እንደሚችሉ በማመን ሌሎች አማራጮችን ለማየት ወሰኑ።

“...በነገራችን ላይ ብሔራዊ ባንክ የሰራሁት በምን ያህል ደመወዝ እንደሆነ ታውቂያለሽ? በ 2ሺ500 ብር ነው። 1 ሺ 900 ብር እጄ ይገባል፤ በዚህ ደመወዝ ቤተሰብ አስተዳድሬ ልጆቼን አስተምሬ ነው የኖርኩት። የሚያውቁኝና አንዳንድ ሰዎች አንተ ምን ነክቶህ ነው ለራስህ የሚሆን ጥሪት ያዝ እንጂ ሁሉ ሰው እየሰረቀ አይደለም እንዴ ውሰድ ይሉኝ ነበር። ነገር ግን የሰረቀ ይስረቅ እኔ ግን አላደርገውም ስርቆት ውስጥ አልገባም ባለመስረቄ ምድራዊ ችግር ቢገጥመኝም የሰማዩን ቤቴን ግን አሳምርበታለሁ፤ እምቢ አልኩ፤” በማለት ታማኝነት ለራስ መሆኑን ያስረዳሉ፡፡

አቶ ዱባለ ከብሔራዊ ባንክ ባዶጃቸውን በሚባል ደረጃ ከተሸኙ በኋላ ያደረጉት ነገር ቢኖር መጀመሪያ የስራን ዓለም ሲቀላቀሉ ወዳቋቋሟቸው የልማት ማህበራት በመሄድ ስራን ጀመሩ። ታማኝነት ራሱ ይከፍላልና ብዙም ሳይቆዩ የኦሮሚያ ክልል ፕሬዝደንት ወደነበሩት አቶ አባዱላ ገመዳ ዘንድ በአማካሪነት ተመድበው ዳግም የመንግሥት የስራ ሃላፊነታቸውን ጀመሩ፡፡

አቶ ዱባለ የአማካሪነት ጊዜ የስራ ቆይታቸውን ሲገልጹም “... አቶ አባዱላ ማለት እጅግ በጣም ጥሩ ሰው፣ እውነትን የሚያውቅ፣ ሰው የሚረዳ ነው። አሁን ባለኝ ሕይወትም የት ወደክ? ምን ሆንክ? ብሎ የሚያየኝ እሱ ነው” በማለት ይናገራሉ።

ከዚህ ሁሉ የስራና የአገልግሎት ዘመን በኋላ ያለው የአቶ ዱባለ ኑሮ በእውነት አንገት ያስደፋል፤ ልብ ያደማል፤ በኀዘን ጭብጥ ኩርምት ያደርጋል። “....አትመመኝ ማለት ባይቻልም ግን ደግሞ መታከሚያ ገንዘብ አትንፈገኝ ማለት ግን ይገባል”። አቶ ዱባለ መጀመሪያ ከስራ ውለው ቤታቸው እረፍት እያደረጉ ባሉበት ጊዜ ነበር በጭንቅላት ደም መፍሰስ (ስትሮክ) የተመቱት። እሱን እንደምን ማገገም ቢችሉም ኩላሊታቸው በመድከሙ ምክንያት ዛሬ ላይ በሳምንት ሶስት ጊዜ የኩላሊት እጥበት ዲያሊሲስ የሚፈልጉ ህመምተኛ ሆነዋል፡፡

“....ዛሬ እንዲህ ሆንኩ እንጂ ድሮማ ለረሃብም ለጥጋብም የማልበገር ፤ ሰርቼ የማይደክመኝ፤ የሰው ሀቅ የማልፈልግ ፤ አገሬ በምትፈልገኝ ቦታ ሁሉ በአቅሜ በታማኝነት ያገለገልኩ፤ አዲስ አበባ ተቀምጬ ገጠር ያሉ ወገኖቼን የምደግፍ፤ ለልጆቼ አባት ለሚስቴም አባወራ ነበርኩ። ምን ያደርጋል ዛሬ አልሆነም “ ይላሉ አንገታቸውን ስብር አድርገው። በሽታ ክፉ ነው በሰው እጅ መውደቅ ደግሞ ሞት። እኛ ጠንካራና ቆፍጣና በርካታ አገራዊ ሃላፊነቶች ላይ ግንባር ቀደም የነበሩት ሰው ዛሬ ተንቀሳቃሽ ወንበራቸው (ዊልቸራቸው) ላይ ቁጭ ብለው የልጆቻቸውን በተለይም የካሊድን ድጋፍ መፈለግ የእለት ተዕለት የኑሮ ሂደታቸው ከሆነ 13 ዓመታት እንደዋዛ ተቆጥረዋል፡፡

ዛሬ አቶ ዱባለ በሳምንት ሶስት ጊዜ እንዲያደርጉ ለሚጠበቅባቸው ዲያሊሲስ እጅ ሰጥተዋል። ለህክምናው እጅ ቢሰጡም ከፍሎ መታከሚያው ደግሞ የሞት ያህል ገዝፏል። አስራ ሶስት ዓመት ሙሉ በተለያዩ ህመሞች ሲሰቃዩ የቆዩት አቶ ዱባለ ዛሬም ድረስ አብሯቸው ለቀጠሉት ህመሞች የሚሆን መታከሚያ ያስፈልጋቸዋል። ዛሬ ቤተሰቦቻቸው የኩላሊት ንቅለ ተከላ እንዲደረግላቸው ቢያስቡም (ቢመኙም) ለእሱ የሚሆን ገንዘብ ግን የላቸውም። እኚህን የአገር ባለውለታ ዞር ብሎ ያያቸውም የለም። ከህመማቸው ጋር ችግር ተደምሮ ቁጭ ብሎ ቀን ከመቁጠር የዘለለ አቅም አሳጥቷቸዋል፡፡

አቶ ዱባለ በወጣትነታቸው ስራ መስራት ባገኙት ነገር ቤታቸውንና ቤተሰባቸውን መደገፍ ነበር የቀን ከሌሊት ህልማቸው። የብሔራዊ ባንክ ገዢ ሆነው በ 2ሺ 500 ብር ደመወዝ ይስሩ እንጂ ከሃቃቸው ውጪ አንዲትም ነገር ለመጠቀም አስበው አያውቁም። አስር ብር ኪሳቸው ሳይኖር ስለመውጣታቸውም ደጋግመው ይናገራሉ። በወቅቱ ደመወዛቸውን ቆጥበው የሰሩትን ቤትም በኩላሊት ህመማቸው ምክንያት ለመታከሚያ ይሆን ዘንድ ሸጠውታል። ከዛም በመንግሥት አንድ ክፍል ቤት ውስጥ ቤተሰባቸውን ይዘው ለመኖር ተገደውም ነበር። አንዳንዴ ስራ ዋጋ ይከፍላልና ዛሬ ላይ አብረዋቸው በሰሩ ስለ ጉብዝናቸው ስለአገልግሎታቸው እንዲሁም ታማኝነታቸው የሚያውቁ የቀድሞ የስራ ባልደረቦቻቸው አቶ አባዱላ ገመዳ ባደረጉላቸው ጥረት የመንግሥት ቤቶች ኤጀንሲ ማረፊያ ይሆናቸው ዘንድ አንድ ቤት ሰጥቷቸዋል።

ይህንን ላደረጉላቸው አካላትም ላቅ ያለ ምስጋናን ያቀርባሉ ግን ደግሞ አሁን የአቶ ዱባለ ችግር የህክምና ወጪያቸው ነው። በጡረታ የሚያገኟት ገንዘብ አሁን ላይ እሳቸው የሚያስፈልጋቸውን ህክምና ለማድረግ ቀርቶ ቀለብ ለመሸመት አትበቃም። እራሱን ችሎ እሳቸውን ለመደገፍ አቅም ያለውም ልጅ የላቸውም ፤ብቻ ሁኔታቸው ልብ ይነካል ፤ተገቢውን ህክምና ቢያገኙ በቀላሉ የሚያገግሙ መሆናቸው ሲታይ ደግሞ ይቆጫሉም፡፡

“...በስራ ላይ ሆኜ በተለይም ብሔራዊ ባንክ ስሰራ ጠዋት 2 ሰዓት የገባሁ ከሌሊቱ ስምንት ሰዓት ነበር ቤቴ የምገባው። ስለ ፕሮጀክቶች ስለ መንገድ ስለሌላውም ሌላውም ስንሰበሰብ ፤ ስንወያይ ውሳኔ ሲሰጥ አድሮ የመምጣት ያህል ነበር ቤቴ የምገባው፤ አንዳንድ ጊዜ ለወር ያህል ልጆቼን ላላያቸው እችላለሁ። ይህንን ሁሉ ዋጋ የከፈልኩት ደግሞ ለሕዝቤና ለአገሬ ነው። በአጭሩ ግን በተሰሩ ስራዎች ውስጥ ሁሉ ድርሻ አለኝ። ድርሻዬን ደግሞ በንጽህና ስለመወጣቴ ባለሥልጣናቱም እንዲሁም ሕዝቡም የሚያውቀው ሃቅ ነው፡፡” በማለት ይናገራሉ።

አቶ ዱባለ ዛሬ ላይ ከፍ ባለ የጤና ችግር ውስጥ ያሉ ቢሆኑም ተስፋ መቁረጥ ግን አይነበብባቸውም ፤ ኢትዮጵያውያን ያግዙኛል ያድኑኛል ይላሉ፤ “ ...ከዚህ ቀደም ጠቅላይ ሚኒስትር ዶክተር አቢይ አሕመድን አግኝቻቸው ነበር ፤አይተውኝ አዝነው ለህክምናም እንዳታስብ ያገለገልካት አገር ታሳክምሃለች ብለውም መጽሀፍ ሰተውኝ ቃል ተገባብተን ነበር የተለያየነው፤ ነገር ግን ሃላፊነቶችም ሲበዙባቸው ዳግም መገናኘት አልቻልንም” ይላሉ።

ዛሬ ላይ የአቶ ዱባለ ህመም ኩላሊትና ስትሮክ ዋናዎቹ ይሁኑ እንጂ ሌሎች ተጨማሪ ነርቭ እግራቸው እንዳይንቀሳቀስ አደረገው ፤ እጃቸውም እንደልብ አይሰራም፤ ጆሯቸውም የህመሞቹ ተጽዕኖ እንዳይሰማ እየተጋፋው ነው፤ ከምንም በላይ ደግሞ ያሳሰባቸው የዓይናቸው አቅም መቀነስ ነው፤ እነዚህ ሁሉ ነገሮች ተደራርበውባቸው ሕይወት የምርጊት ያህል ከባድ ሆኖባቸዋል፡፡

**“.....እጄን፣ እግሬን፣ አይኔን ብቻ መላ ሰውነቴን ያመኛል ፤ እዚህ ቦታ ሰላም ነኝ የምለውም የለኝም፤ ያለሁት ከፍተኛ ስቃይ ላይ ነው። የምታከምበት ማጣቴ የእኔ ስንፍና አይደለም፤ ሰነፍም አልነበርኩም ፤ ለሀገሬ ታማኝ ለመሆን ስል ነው ይህን ሁሉ መከራ የምከፍለው። ነገር ግን ታማኝነት እራሱ የሚከፍል ቢሆንም ዛሬ ላይ ግን እኔን ስቃይ ውስጥ ከቶኛል ያም ቢሆን ግን ከነክብሬ ደሃ ሆኜ መኖሬን መርጫለሁ፤**

“.....እጄን፣ እግሬን፣ አይኔን ብቻ መላ ሰውነቴን ያመኛል ፤ እዚህ ቦታ ሰላም ነኝ የምለውም የለኝም፤ ያለሁት ከፍተኛ ስቃይ ላይ ነው። የምታከምበት ማጣቴ የእኔ ስንፍና አይደለም፤ ሰነፍም አልነበርኩም ፤ ለሀገሬ ታማኝ ለመሆን ስል ነው ይህን ሁሉ መከራ የምከፍለው። ነገር ግን ታማኝነት እራሱ የሚከፍል ቢሆንም ዛሬ ላይ ግን እኔን ስቃይ ውስጥ ከቶኛል ያም ቢሆን ግን ከነክብሬ ደሃ ሆኜ መኖሬን መርጫለሁ፤ ይህንን ደግሞ በልጆቼ ላይም አስርጬዋለሁ በዚህም በጣም ደስተኛ ነኝ” በማለት ይናገራሉ።

እስከ አሁንም ጓደኞቻቸው ኦሮሚያ ላይ የሰሩባቸው መስሪያ ቤቶች እንዲረዷቸው አደረጉ በዚህም አንድ ዓመት ኩላሊታቸውን መታጠብ ቻሉ፤ ከዚህ በኋላ ያሉትን ጊዜያት ግን ተራራ የመቧጠጥ ያህል ከባድ ጊዜዎችን በማሳለፍ ልጃቸው አይገቡ እየገባ የሰው ፊት እየገረፈው ለምኖ ስለማሳከሙ አቶ ዱባለ ይናገራሉ፡፡

“...በአገለገልኩበት አገር ላይ ተረስቻለሁ ፤ እባካችሁ ለሩጫ የሚያበቃኝን ድጋፍ አድርጉልኝ፤ ሌላውና ዋናው ነገር ግን የኩላሊት ንቅለ ተከላ ነው። አሁን ላይ ኩላሊቱን የሚሰጠኝ ቤተሰብ አግኝቻለሁ ፤ ለንቅለ ተከላውም ብቁ መሆኔን ሀኪሞች አረጋግጠውልኛል። ነገር ግን ገንዘብ በማጣቴ ምክንያት ህክምናውን አግኝቼ አገሬን በቀሪው እድሜዬ እንዳላገለግል ሆኛለሁና የኢትዮጵያ ሕዝብ እጁን ይዘርጋልኝ” ይላሉ፡፡

አቶ ዱባለ ዛሬ ላይ ንቅለ ተከላውን አግኝተው የነርቭ ህክምናቸውን በአግባቡ ተሰጥቷቸው አገራቸውን ለማገልገል ቤተሰባቸውን በተሻለ ሁኔታ ጥሩ ደረጃ ላይ ለማድረስ ይጓጓሉ። ነገር ግን ይህ እስከሚሆን ድረስ እስትንፋሳቸውን ለማስቀጠል ብዙ መድሃኒቶች ብሎም የዲያሊሲስ ህክምናው ያስፈልጋቸዋል ። ለዚህ ደግሞ ነገ ሳይሆን ዛሬ ገንዘብ ለእሳቸው የግድ ነው።

“...ዛሬ ገንዘብ እጄ ላይ ስለሌለ ጠዋት ተነስቼ ጸሀይ መሞቅ ነው ስራዬ” በማለት እጅግ በጣም በተከፋ ስሜትና ልብ በሚሰብር ኀዘን ያለባቸውን ችግር ይናገራሉ።

የእኔ አባት የሚሉት ልጃቸው ካሊድ ዱባለ ከጎናቸው አይለይም፤ ይህንን ቃለ ምልልስ እያደረግን እንኳን ደጋግመው ይጠሩታል። እሱም ለእሳቸው ሲል ስራና ኑሮውን ትቶ አባቱ ስር ነው ያለው፤ “....አባቴ አገሩን በታማኝነት ያገለገለ ነው፤ ዛሬ ላይ ግን ጤናው ተዛብቶ የሰው እጅ ላይ ወድቋል “ ይላል፡፡

ካሊድ አባቱ የዲያሊሲስ ህክምናቸውን በገንዘብ ችግር ምክንያት እንዳያስተጓጉሉ ብዙ ጥረት ያደርጋል፤ ቀድሞ የሰሩባቸው መስሪያ ቤቶች እየሄደ እርዳታ ይጠይቃል ፤ የሚያውቁትን እሳቸውን የሚያውቋቸውን ሰዎች ሁሉ አስቸግሯል ግን ደግሞ ዘላቂ መፍትሔን ማግኘት ግን አልቻለም፡፡

“....አባቴ ታሞ አልጋ ከያዘ 13 ዓመታት ተቆጥረዋል። በእነዚህ ዓመታት ቤታችንን ሸጠናል የሚያውቁንም የማያውቁንም ብዙ አድርገውልናል ፤ አሁን አባቴ የሚያስፈልገው የኩላሊት ንቅለ ተከላው በመሆኑ እሱን በገንዘብ የሚደግፈን ኢትዮጵያዊ እንፈልጋለን” በማለት እያሳለፉ ያሉትን ከባድ ጊዜ ይናገራል።

35 ዓመታት አብረዋቸው ከኖሩት ባለቤታቸው አራት ልጆችን አፍርተዋል። ‹‹ባለቤቴ በዚህ ሁኔታዬ ውስጥ ከጎኔ ቆማ ያለችው እሷ ናት። ልብሴን አጥባ ምግቤን ሰርታ አቅርባ ታበረታታኛለች። “አመመኝ “ እንኳን ስል “ አንተ ብቻ ነህ እንዴ የምትታመመው በል በርታ “ ብላ ሁሌም የሞራል ድጋፍ ትሰጠኛለች፡፡›› ይላሉ የባለቤታቸውን ውለታ ሲገልጹ።

በዚህ ዘመን ሙስና ገነገነ ፤ አስቸገረ ፤ ትልቁም ትንሹም ሙሰኛ ሆነ ፤ አገር ተበዘበዘች እየተባለ ኮሚቴ እስከማዋቀር የደረሰ ዘመቻ ላይ ነን። እንደዚህ ደግሞ አገራቸውን በታማኝነት ያገለገሉ ለእኔ ሳይሉ የኖሩ በዚህ መልኩ ችግር ሲገጥማቸው እንደ አገርም ሆነ ሕዝብ ውለታቸውን በአለሁ ባይነት ማሰብ ይገባል። አዎ ለመልካም ስራ መሸቶም ረፍዶም አያውቅምና አቶ ዱባለ የሚያስፈልጋቸውን የህክምና እርዳታ ያገኙ ዘንድ ሁላችንም የበኩላችንን ማድረግ አለብን።

# ዓለም አቀፍ መድረኮችን ለቱሪዝም ዘርፉ መነቃቃት

**ዳግም ከበደ**

ኢትዮጵያ የብዝሃ ቱሪዝም መገኛ ነች። ለአገር ገፅታ ግንባታ፣ ለምጣኔ ሀብት መጎልበት፣ ለጋራ እሴት መገለጫ ከፍተኛ አበርክቶ ያላቸው የባህል፣ የተፈጥሮ፣ የታሪክ የመካነ ቅርስ እና ሌሎች ዘርፈ ብዙ የቱሪዝም ሀብቶችን በዚህች "ምድረ ቀደምት" የሚል ስያሜ በተሰጣት አገር ላይ እንደ ልብ ማግኘት ይቻላል፡፡ እነዚህን ሁሉ በረከቶች ትርጉም ወዳለው ጠቀሜታ መቀየር፣ ለቀሪው ዓለምም ሆነ ለአገር ውስጥ ጎብኚዎች ማስተዋወቅ፣ አገርና ትውልድን በሚጠቅም መልኩ ምጣኔ ሀብቱን እንዲደግፍ ፈር ማስያዝ ላይ ግን ብዙ ስራ እንደሚጠይቅ ባለሙያዎች ይናገራሉ። መረጃዎችና ጥናቶችም ኢትዮጵያ በተሰጣት የቱሪዝም በረከት ልክ ተጠቃሚ እንዳልሆነች ያመለክታሉ።

የአገራችን የቱሪዝም ሀብቶች በሚፈለገው ልክ ለምጣኔ ሀብታዊ፣ ማህበራዊና ሌሎች ጥቅሞች እንዳይውሉ ካደረጉት መካከል ቀዳሚ የሆነው ምክንያት ሀብቶቹ በዓለም መድረክ ላይ እንዲተዋወቁ፣ እውቅና እንዲያገኙና ተወዳዳሪ እንዲሆኑ የሚካሄደው የገበያና ፕሮሞሽን ስራ በቂ አለመሆኑን የዘርፉ ባለሙያዎች ይጠቅሳሉ። ዓለም አቀፍ መድረኮችን አቅም በፈቀደ መልኩ መጠቀምና ለዚያም ሀብቶቹን የሚታዩበትን እድል (visible) ማስፋት እንደሚያስፈልግ ይገለፃሉ።

የቱሪዝም ዘርፉን በቀዳሚነት የሚመራው የቱሪዝም ሚኒስቴር መስሪያ ቤት ባለፉት ጥቂት ዓመታት ይህንን ችግር በመለየት መፍትሄ ለመስጠት እየሰራ እንደሆነ ይገለፃል። በተለይ መንግሥት መስኩን ከዋና ዋና የኢኮኖሚ አመንጪ ምሰሶዎች አንዱ አድርጎ በመውሰድ በትኩረት ለመስራት መሰናዳቱን አስታውቆ እየሰራ ይገኛል። በዓለም አቀፍ መድረክ ላይ የቱሪዝም የመስህብ ሀብቶችን የማስተዋወቅ እና የቱሪስት ፍሰቱን ለመጨመር የሚደረጉ ጥረቶች መኖራቸውን የሚያሳዩ ጥረቶችም እንዲሁ ይስተዋላሉ።

ሰሞኑንም የቱሪዝም ሚኒስቴር አመራሮች በተለያዩ አህጉርና ዓለም አቀፍ የቱሪዝም ሁነቶች ላይ ተሳትፈዋል፤ በዚህም የኢትዮጵያን የቱሪዝም ሀብቶች አስተዋውቀዋል፤ ልምድ ተለዋውጠዋል፡፡ ከእነዚህ አመራሮች መካከል የሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ ሚኒስትር ዴኤታ ወይዘሮ ሰላማዊት ዳዊት ይገኙበታል። እርሳቸው በደቡብ አፍሪካ "የቱሪዝም ልምድ ልውውጥና ቀጣናዊ ትስስር"ን ማጠናከርን ታሳቢ ባደረገና 13 አገራትን ባሳተፈ መድረክ ላይ ተገኝተው የኢትዮጵያን ተሞክሮ ከማጋራታቸው ባሻገር ከደቡብ አፍሪካ ጋርም የጋራ ስምምነት ላይ ደርሰዋል።

በበርሊን የቱሪዝም ሚኒስትሯ አምባሳደር ናሲሴ ጫሊ የተሳተፉበት የአይቲቢ ኤግዚቢሽንና በሳውዲ አረቢያ ኢትዮጵያ በጮቄ ተራራና ሙሉ ኢኮ ሎጅ መልከዓ ምድር የዓለም ምርጥ የቱሪዝም መዳረሻ በሚል ሽልማት የተቀበለችበት መድረክን አስመልክተን ሚኒስትር ዴኤታዋ ሰላማዊት ዳዊትን አነጋግረን የሚከተለውን ዳሰሳ ይዘንላችሁ ቀርበናል።

ሚኒስትር ዴኤታዋ እንዳሉት፤ 13 አገራት የተሳተፉበት የደቡብ አፍሪካ ኬፕታውኑ መድረክ ዓላማ በዋናነት አገራት ያላቸውን የቱሪዝም አቅምና አፈፃፀም የሚያቀርቡበትና ልምድ የሚለዋወጡበት ነው፤ ችግሮች የሚፈቱበትን መንገድ በማቅረብም ለዚያ የተቀመጠውን መፍትሄ ሌሎች አገራትም እንዲወስዱት ታሳቢ ያደረገም ነው፡፡

በተለይ የኮቪድ ወረርሽኝን ተከትሎ ብዙ የአፍሪካ አገራት መጎዳታቸውን የሚናገሩት ሚኒስትር ዴኤታዋ፣ መድረኩ ሀገሮች ይህንን ችግር በምን መልኩ እንዳለፉና ምርጥ ተሞክሮዎችን የተለዋወጡበት እንደሆነም ገልፀዋል። በቱሪዝም ዘርፉ ያለው የኢኮኖሚ መነቃቃት ምን ደረጃ ላይ እንደሚገኝም የተወያዩበት መሆኑን ያስረዳሉ።

በመድረኩ ላይ ኢትዮጵያ ባለፉት ጥቂት ዓመታት በከተማም ሆነ በገጠር ያሳካቻቸውን የቱሪዝም ልማት ስራዎችና የቱሪስት መዳረሻ ቦታዎችን የማልማት (የገበታ ለሃገር፣ ገበታ ለሸገር፣ እና የገበታ ለትውልድ) ስኬት በመድረኩ ላይ እንደ ምርጥ ተሞክሮ ለተሳታፊ አገራት ማካፈሏን ተናግረዋል። በተለይ የልማት ስራዎችን የሚደግፍ መዋቅር ነዋይ ከግል ዘርፉ፣ ከማህበረሰቡ እንዲሁም አቅም ካላቸው አካላት የተሰባሰበበትን



**ኢትዮጵያ ሰሞኑን በጀርመን፣ ደቡብ አፍሪካ እና ሳውዲ አረቢያ በተካሄዱ የቱሪዝም መድረኮች ተሳትፋለች**

መንገድ፣ በማህበረሰብ አቀፍ ሎጅ መልከዓምድራቸውንና ያላቸውን የመስህብ ስራዎች በባህላዊ ሥርዓት ጠብቀው ለቱሪዝም መስህብነት ተመራጭ ያደረጉ እንደ ወንጪ ደንዲና ጮቄ ተራራ አይነት ስፍራዎችን እና ሌሎችም የዘርፉ ስኬቶችን እንደ ልምድ ማጋራት እንደተቻለ ገልፀዋል። መንግሥት የቱሪዝም ዘርፍን ለመጀመሪያ ጊዜ እንደ ዋና የምጣኔ ሀብት መስክ ቆጥሮ ልዩ ትኩረት እንደሰጠው ማስረዳታቸውንም አስረድተዋለ።

እንደ ሚኒስትር ዴኤታዋ ገለጻ፤ ኢትዮጵያ በቱሪዝም ዘርፏ በኩል መሻሻል ያለባቸውን ጉዳዮች በመድረኩ አንስታለች፡፡ ከተሳተፉት 13 አገራት የፀጥታና ሰላም ችግር ያለባቸው ቢኖሩም፣ የአገር ውስጥ ሆነ ዓለም አቀፍ ጎብኚዎችን የሚያስተናግዱ መሆናቸውና ዘርፉ እክል እንዳልገጠመው ከመድረኩ መገንዘባቸው ተችሏል።

ከዚህ አንፃር በኢትዮጵያ ውስጥ ቱሪዝሙን ተጠቅሞ እዚህም እዚያም የሚነሱ የፀጥታ ስጋቶችን መቀነስና ለጎብኚዎች ምቹ የሆነ ከባቢያዊ ሁኔታ መፍጠር የሚቻልበትን ልምድ ከአገራቱ ማግኘት የተቻለበት ሁኔታ ተፈጥሯል፡፡

"በልምድ ልውውጡ ላይ ምርጥ ተሞክሮን ከመለዋወጥና ከመማማር ባሻገር ከደቡብ አፍሪካ ጋር ተጨማሪ ውይይቶችንና ስምምነቶችን የማድረግ ፍላጎት ነበረን" የሚሉት ሚኒስትር ዴኤታዋ፤ በዋናነት በቱሪዝም ዘርፍ ከአገሪቱ ጋር በቅንጅት ለመስራት ፍላጎት እንዳለም ይገልፃሉ። ቀደም ሲል ጠቅላይ ሚኒስትር ዶክተር አብይ አሕመድ በደቡብ አፍሪካ በነበራቸው ይፋዊ ጉብኝት ላይም በቀዳሚነት ከተፈራረሙት የመግባቢያ ሰነድ ውስጥ "በቱሪዝም ዘርፍ በጋራና በትብብር እንሰራለን" የሚል ሃሳብ እንደሰፈረበት ጠቅሰው፣ ይህንን ወደ ተግባር በመለወጥ ስራ ላይ ከልምድ ልውውጥ መድረኩ ጎን ለጎን ውይይት መደረጉን ይናገራሉ።

በዚህም ሁለቱ አገራት እርስ በእርስ የሚማማሩበትና የተለያዩ ድጋፎችን የሚለዋወጡበት ማእቀፍ ወደ ስራ ለማስገባት እየተንቀሳቀሱ መሆናቸውን ገልጸው፣ መድረኩንም ለዚህ ተጨማሪ ዓላማ ለማዋል እንደተጠቀሙበት ተናግረዋል። በተለይ ሁለቱም አገራት የቱሪዝም መስህቦቻቸውን በጋራ የሚያስተዋውቁበት እድል ለመፍጠር እንደሚሰሩ፤ ደቡብ አፍሪካ በዓለም አቀፍ መድረክ እንዲሁም ባላት የመገናኛ ብዙሃን አቅም የኢትዮጵያን የቱሪዝም ሀብቶች ተደራሽ እንዲሆን ለማስቻል ከሀገሪቱ የቱሪዝም ዘርፍ ዳይሬክተር ጀነራል ጋር ውይይት ማድረጋቸውን አሳውቀዋል።

ከዳይሬክተር ጀነራሉ ጋር ከዚህ ቀደም በጠቅላይ ሚኒስትሩ ይፋዊ ጉብኝት የተደረሰውን የመግባቢያ ስምምነት መሬት ላይ ለማውረድ የቴክኒክ ኮሚቴ በጋራ አቋቁሞ ወደ ስራ ለመግባት መጋቢት 23 ጀምሮ የልኡክ ቡድን ወደ ኢትዮጵያ እንደሚመጣ ገልጸዋል።

"እንደ አገር ሁለት ዓላማዎችን ይዘን ነው በመድረኩ ላይ የተገኘነው" ያሉት ሚኒስቴር ዴኤታዋ የመጀመሪያው ልምድ መለዋወጥ ሲሆን ሁለተኛው፣ ከአዘጋጅ አገሯ ጋር የሁለትዮሽ ስምምነት መፈፀም መሆኑን ተናግረው ሁለቱንም ማሳካት እንደተቻለ ይናገራሉ።

"በቱሪዝም ዘርፍ ቀጣናዊ ትስስር መፍጠር በአገራቱ መካከል በሚኖረው ውድድር ላይ ምን አይነት ተፅእኖ ሊያሳድር ይችላል" የሚል ጥያቄ የዝግጅት ክፍላችን አንስቶ ሚኒስትር ዴኤታዋ ሲመልሱ፤ ሁሉም ሀገሮች በዘርፉ የተሰጣቸው ፀጋና የቱሪዝም ሀብት የተለያየ መሆኑን ተናግረዋል። የኢትዮጵያ ታሪካዊ ቅርሶች፣ መልከዓምድር፣ ባህላዊና አርኪዮሎጂካል ሀብቶች ከደቡብ አፍሪካም ይሁን ከሌሎች አገራት የተለየ መሆናቸውን ጠቅሰው፣ የገበያ ሽሚያም ሆነ በጋራ ለመስራት እንቅፋት የሚሆን ሁኔታ እንደሌለ ገልፀዋል። ሌሎች አገራት ኢትዮጵያ ውስጥ ያለውን ሃብት ለዜጎቻቸው ቢያስተዋውቁም ሆነ ተመሳሳዩን ኢትዮጵያ ብታደርግ የተሻለ ውጤት በመስኩ ላይ ከማስመዝገብ ውጪ ምንም አይነት ጉዳት እንደማይኖረው ይገልፃሉ።

በዘርፉ በተለይ ቀጣናዊና ትስስር ከጎረቤት አገሮች ጋር ማድረግ አያሌ ጠቀሜታዎች እንዳሉት የሚያነሱት ሚኒስትር ዴኤታዋ፤ ለምሳሌ ያህል ጅቡቲን ለመጎብኘት የሚመጣ የቀሪው ዓለም ቱሪስት እግረ መንገዱን አፋር ላይ ያሉትን የቱሪዝም መዳረሻዎች እንዲመለከት በጋራ ቢሰራና እድሉ ቢመቻች ለሁለቱም አገራት የተሻለ አማራጭና ገበያ የሚከፍት እንደሆነ ይናገራሉ። ይህንን መሰል ልምድ በኬንያም፣ በኤርትራም ሆነ በሌሎች የቀጣናው አገራት ማስፋትና በጋራ አህጉሪቱን አስተዋውቆ ከዚያ እድል ተጠቃሚ መሆን እንደሚያስፈልግ ጠቁመዋል።

በደቡብ አፍሪካ ከተካሄደው የቱሪዝም ምርጥ ተሞክሮ መድረክ ባሻገር የቱሪዝም ሚኒስቴር መስሪያ ቤት በዓለም አቀፍ ደረጃ እውቅና ባላቸው ሁለት ተጨማሪ መድረኮች ላይ መካፈሉን የሚናገሩት ሚኒስትር ዴኤታዋ፣ የመጀመሪያው በሚኒስትሯ አምባሳደር ናሲሴ ጫሊ አማካኝነት "አይ ቲቢ" አውደ ርእይ ሲሆን ሁለተኛው የጮቄ ተራራና ሙሉ ኢኮ ሎጅ "የዓለም ምርጥ የቱሪዝም መንደር" ተብሎ መሸለሙን አስመልክቶ በሳውዲአረቢያ የተካሄደ መድረክ መሆኑን ተናግረዋል።

ከዚህ በተጨማሪም ኢትዮጵያ ከ30 በላይ ባለድርሻ አካላትን (የቱር ኦፕሬተሮች፣ የተወሰኑ ክልሎችን፣ የኢትዮጵያ አየር መንገድን፣ ኢንተርናሽናል ሆቴሎችን) ይዛ በጀርመን በርሊን በተካሄደው የአይ ቲቢ ኤግዚቢሽን ተካፍላለች፡፡ መድረኩ በጀርመን በየዓመቱ የሚካሄድና የቱሪዝም መስህብ ስፍራዎችንና ምርቶችን ለማስተዋወቅ ዓላማ ያደረገ መሆኑን አስታውቀዋል። በርካታ ካምፓኒዎችና ዓለም አቀፍ የቱሪዝም ዘርፍ አንቀሳቃሾች የኢትዮጵያ አቅም ምን ደረጃ ላይ እንደሚገኝ በመድረኩ ከመመልከታቸውም ባሻገር አብረው የሚሰሩበት ስምምነት ላይ የተደረሰበት መልካም አጋጣሚ መፈጠሩንም ሚኒስትር ዴኤታዋ ይገልፃሉ።

በበርሊኑ አውደ ርእይ በሚኒስትሯ መሪነት የተሳተፈው ልኡክ በሰሜን ኢትዮጵያ የነበረውን ግጭትና የኮቪድ ተፅእኖዎችን ኢትዮጵያ እንደተሻገረቻቸውና ሁሉም መዳረሻዎች ለጎብኚዎች ክፍት መሆናቸውን ለማስተዋወቅ እድል ያገኙበት እንደነበር ሚኒስትር ዴኤታዋ ገልፀዋል። ቦታው ላይ በተንቀሳቃሽ ምስል፣ በቡና አፈላል ዝግጅት፣ በፅሁፍና በልዩ ልዩ የግንኙነት አግባቦች ኢትዮጵያን በማስተዋወቅ ስኬት የተገኘበትና ውጤታማ መድረክ እንደነበር አስረድተዋል።

እንደ ሚኒስትር ዴኤታዋ ገለጻ፤ የሳውዲ አረቢያው መድረክ የዓለም የቱሪዝም ድርጅት 'UNWTO' ያዘጋጀው ነው፡፡ መድረኩ በየዓመቱ የሚደረግ ሲሆን፣ ኢትዮጵያም አባል አገር እንደመሆኗ በመድረኩ ተሳትፋለች።

ድርጅቱ የዓለም ምርጥ የቱሪዝም መድረክ እንደሚያወዳድርና እንደሚሸልም ገልፀው፣ ኢትዮጵያ በተንቀሳቃሽ ምስል የጮቄ ተራራ መልከአምድርና ሙሉ የማህበረሰብ አቀፍ ኢኮ ሎጅን ጨምሮ ሶስት የቱሪዝም መዳረሻ መንደሮችን ዶክመንት በማዘጋጀት ከመድረኩ ቀደም ብሎ መላኳን ተናግረዋል። የጮቄ ተራራና ማህበረሰብ አቀፍ ሎጂ ሽልማቱን ማሸነፉን ጠቅሰው፣ ኢትዮጵያ በመድረኩ ላይ ሽልማቱን መቀበሏን ተናግረዋል። ከዚህ ጎን ለጎን ልኡኩን የወከሉት አመራሮች ከሳውዲ አረቢያ የቱሪዝም ሚኒስትር ዴኤታዎች ጋራ በጋራ ለመስራት በሚያስችሉ ጉዳዮች ጋር ግንኙነት በመፍጠር ምክክር መደረጉን ገልፀውልናል።

ሚኒስትር ዴኤታዋ ወይዘሮ ሰለማዊት ዳዊት ሶስቱን ዓለም አቀፍ መድረኮች ጨምሮ መሰል መድረኮችን አሟጦ መጠቀም አስፈላጊ መሆኑን ይናገራሉ። ይሁን እንጂ ሁሉም ጋ ለመገኘትና ኢትዮጵያን በዓለም አቀፍ መድረኮች ላይ በበጎ መልኩ ለማስተዋወቅ ከፍተኛ የመዋለንዋይ አቅም እንደሚጠይቅ ጠቅሰው፣ በተቻለ አቅም ያሉትን አጋጣሚዎች ሁሉ ለቱሪዝም ዘርፉ መነቃቃት ማዋል እንደሚያስፈልግ ገልጸዋል።

ስፖርት እና መዝናኛ

# ሳምንቱን በታሪክ

## የደጃዝማች ዑመር ሰመተር የጀግንነት ገድል

ዋለልኝ አየለ

«ከአገሬ አፈር የሚደባልቅ ቤልጅግ እና ጎራዴ ይዤ እንጂ ጫት ተሸክሜ የምመጣ እንዳይመስልህ!» የሚለው ንግግራቸው በቃል ጭምር ይነገርላቸዋል። ፋሽስቱን ጣሊያን መግቢያ መውጫ ካሳጡ የኢትዮጵያ የቁርጥ ቀን ጀግኖች አንዱ የሆኑት የምሥራቁ አርበኛ ደጃዝማች ዑመር ሰመተር በዚህ ሳምንት ይታወሳሉ፡፡

በዛሬው ሳምንቱን በታሪክ ዓምዳችን ከ79 ዓመታት በፊት በዚህ ሳምንት መጋቢት 6 ቀን 1936 ዓ.ም ሕይወታቸው ያለፈውን ደጃዝማች ዑመር ሰመተርን እናስታውሳለን።

በፋሺስት ኢጣሊያ ወረራ ወቅት ለኢትዮጵያ ሉዓላዊነት የተጋደሉትና ደማቅ የጀግንነት ታሪክ የፃፉት ጀግናው አርበኛና ግዛት አስተዳዳሪ ደጃዝማች ዑመር ሰመተር በ1871 ዓ.ም በኦጋዴን አካባቢ ካልካዩ በተባለ ሥፍራ ተወለዱ። ለአካለ መጠን ከደረሱም በኋላ የኤልቡር አካባቢ ገዢ በመሆን አገልግለዋል። ኢጣሊያ ዓድዋ ላይ የደረሰባትን ሽንፈት ለመበቀል የያዘችውን የረጅም ጊዜ ዓላማ ለማሳካት ባደረገችው ወረራ ወቅት በምስራቁ የኢትዮጵያ ክፍል ከደጃዝማች አፈወርቅ ወልደሰማያት ጋር ተሰለፉ። ኢጣሊያ ኢትዮጵያን ለመውረር የጫረችው የወልወል ጠብ የተከሰተው ደግሞ ዑመር ሰመተር በነበሩበት በምስራቁ የኢትዮጵያ ክፍል ነበር።

ኢጣሊያ በ1888 ዓ.ም ዓድዋ ላይ የደረሰባትን ሽንፈት ለመበቀልና ኢትዮጵያን የኢጣሊያ ምስራቅ አፍሪካ ቅኝ ግዛት አካል ለማድረግ ለ40 ዓመታት ያህል ስትዘጋጅና ጊዜ ስትጠብቅ ቆየች። እንደ አውሮፓውያኑ የዘመን ቀመር በ1922 ወደ ሥልጣን የመጣው ቤኒቶ ሙሶሊኒ፣ ኢጣሊያ ዓድዋ ላይ የተከናነበችውን የውርደት ማቅ እንደሚበቀልና ኢትዮጵያ የኢጣሊያ ቅኝ ግዛት አካል እንደምትሆን መዛት የጀመረው ገና በጠዋቱ ነበር።

ለዚህም እንዲያመቸው የኢጣሊያ መንግሥት ራስ ተፈሪ መኮንን ኢጣሊያን በጎበኙበት ወቅት «ቪቫ ኢትዮጵያ» እያለ ወዳጅ መስሎ ሸነገላቸው። እስከ አፍንጫው የታጠቀ በርካታ ጦር በኤርትራና በሌሎች የኢጣሊያ ምስራቅ አፍሪካ ቅኝ ግዛት አካባቢዎች ላይ ያከማች ጀመር። የጦሩን ውጤታማነት አስተማማኝ ለማድረግም ሀኪሞችን፣ ሰላዮችንና ሌሎች ሙያተኞችን አብሮ አጓጓዘ። ኢትዮጵያውያን የግዛት ባላባቶችን በጥቅም በመደለል ማስኮብለሉንና መረጃ መመንተፉንም ተያያዘው። በጨካኝነታቸው የታወቁትን እነ ኢሚሊዮ ዴ ቦኖ፣ ፒየትሮ ባዶሊዮ፣ ሩዶልፎ ግራዚያኒና ሌሎች የጦር አለቆችን ወደ ምስራቅ አፍሪካ ላከ፡፡

ጣሊያን ይህንን ዝግጅት ካጠናቀቀች በኋላም ኢትዮጵያን የምትወርበት አጋጣሚ መጠባበቅ ጀመረች። በዕለተ ረቡዕ፣ ኅዳር 26 ቀን 1927 ዓ.ም የኢጣሊያ ወታደሮች በኢትዮጵያ እና በእንግሊዝ ሱማሌላንድ (British Somaliland) መካከል ያለውን ወሰን ለመከለል የተላኩትን ሰዎች ይጠብቁ በነበሩት የኢትዮጵያ ወታደሮች ላይ ጥቃት ከፈቱባቸው። (ኢጣሊያ በአካባቢው ያለው የኢጣሊያ ሱማሌላንድ ግዛቷ ስለሆነ ወታደሮቿ በአካባቢው ነበሩ)

ውጊያ ተደረገና በሁለቱም ወገኖች በኩል ሰውነት ቆሰለ፤ አካል ጎደለ ... የሰው ሕይወት ጠፋ፡፡

ኢትዮጵያም ስሞታዋን ለኢጣሊያ መንግሥት ስታቀርብ፤ የኢጣሊያ መንግሥት ይባስ ብሎ የተበደለ መሆኑን በመግለፅ የሚከተሉትን «የመደራደሪያ ጥያቄዎች» አቀረበ፡፡

አንደኛ፤ የወቅቱ የሐረርጌ ገዢ የነበሩት ደጃዝማች ገብረማርያም ወልወል ድረስ ሄደው እዚያ የሚገኘውን የኢጣሊያ የጦር መሪ በኢትዮጵያ መንግሥት ስም ይቅርታ እንዲጠይቁ፣ አንድ የኢትዮጵያ የጦር ጓድ ለኢጣሊያ ሰንደቅ ዓላማ ሰላምታ እንዲሰጥ፣ በኢትዮጵያ በኩል ለተደረገው የማጥቃት እርምጃ ኃላፊ የሆኑት ባለሥልጣኖች ሁሉ ተይዘው የኢጣሊያን ሰንደቅ ዓላማ እጅ ነስተው እንዲሻሩና ተገቢውን ቅጣት በአስቸኳይ እንዲያገኙ፣

ሁለተኛ፤ የኢትዮጵያ መንግሥት ለቆሰሉት፣ አካላቸው ለጎደለውና ለሞቱት የኢጣሊያ ወታደሮች ካሣ የሚሆን 200 ሺህ ማርቴሬዛ (ጠገራ ብር) እንዲከፍል እንዲሁም

3ኛ፤ በኢጣሊያ ወታደሮች ላይ ጥቃት ፈፅመው



**ኢጣሊያ በ1888 ዓ.ም ዓድዋ ላይ የደረሰባትን ሽንፈት ለመበቀልና ኢትዮጵያን የኢጣሊያ ምስራቅ አፍሪካ ቅኝ ግዛት አካል ለማድረግ ለ40 ዓመታት ያህል ስትዘጋጅና ጊዜ ስትጠብቅ ቆየች**

ከባድ ጥፋት ያደረሱት ዑመር ሰመተር ተይዘው ለኢጣሊያ መንግሥት እንዲሰጡ ... በማለት የለየለት የትዕቢት ጥያቄ አቀረበ።

የኢትዮጵያ መንግሥትም የኢጣሊያን ሃሳብ ሳይቀበል ቀረ፤ ጉዳዩ በእርቅ እንዲያልቅ ለማድረግ ቢጥርም ሳይሳካ ቀረ። ከዚህ በኋላ ፋሺስት ኢጣሊያ ለ40 ዓመታት ያህል ስትዘጋጅበት የቆየችውን እቅድ እውን ለማድረግ በሁሉም አቅጣጫዎች ኢትዮጵያን መውረር ጀመረች።

በዓለም አቀፍ ሕግጋት ፈፅሞ የተከለከሉ የጦር መሳሪያዎችን (የጦር አውሮፕላን፣ የመርዝ ጋዝ፣ ...) ጭምር በመጠቀም በኢትዮጵያውያን ላይ እጅግ በጣም ከባድ የሆነ የጦር ወንጀል ፈፀመች፡፡

ኢጣሊያ የኢትዮጵያን ግዛት እወስዳለሁ ብላ ወልወል ላይ የጫረችው እሳት በሁለቱም ወገኖች ላይ ጉዳት አድርሶ ነበር። በኋላም እርቀ ሰላም አወርዳለሁ ብላ ቃል ስትገባም ድርድር ስታቀርብ የግጦሽ መሬት ከኢትዮጵያ ግዛት ተቆርሶ እንዲሰጣት ስትጠይቅ «በኢጣሊያ ወታደሮች ላይ በደል የፈፀመው ዑመር ሰመተር እጁ ተይዞ ተላልፎ ይሰጠኝ» ብላ ጠይቃ ነበር፡፡ ዑመር ሰመተርም ይህን ሲሰሙ «ከአገሬ አፈር የሚደባልቅ ቤልጅግና ጎራዴ ይዤ እንጂ ጫት ተሸክሜ የምመጣ እንዳይመስልህ» ብለው በመመለስ ፋሺስት ኢጣሊያ ኢትዮጵያን ከመውረር እንድትታቀብ ደጋግመው ያስጠነቅቁ ነበር፡፡

በወልወል የተጫረው እሳት በሰሜንም ቀጠለ፤ በመላው አገርም ተዳረሰ። ዑመር ሰመተር ከደጃዝማች አፈወርቅ ወልደሰማዕት ጋር በመሆን የፀረ ፋሺስት ትግሉን ተያያዙት። በተለይም የሰለጠነው የዑመር ሰመተር ጦር ገርለጉቤ ከተባለው ስፍራ ላይ መሽጎ ስለነበር እየተወረወረ ጠላትን መውጫ ቀዳዳ በማሳጣት ታላቅ ጀብዱ ፈፅሟል። ኤልቡር በተባለው ቦታ ላይ ዑመር ሰመተር በስድስት ባታሊዮን የጠላት ጦር ተከበቡ። የሰዎቻቸውን አቅምና የጦሩን ሁኔታ ተመልክተው ቦታ ለቀቁ፤ አንዳንድ ሰዎችም መሳሪያ አስረከቡ። ከአምስት ወራት በኋላ ዑመር ሰመተር ጦራቸውን አጠናክረው ሱማሌውን፣ አማራውን፣ ትግሬውን፣ ኦሮሞውን እንዲሁም ከሌላው የአገሪቱ ግዛት የተውጣጣውን ኅብረተሰብ አስከትለው በ1930 ዓ.ም ገደማ አንድ ሌሊት በጠላት ጦር ላይ አደጋ ጣሉ። ስድስቱም ባታሊዮን የጣሊያን ጦር የሞተው ሞቶ ሌላውም ተማረከ። መሳሪያዎቹንም ማረኩና ተመልሰው ሺላቦ ላይ ሰፈሩ።

አሁንም የኢጣሊያ ጦር ሺላቦ ድረስ እየመጣ ቢያስቸግር እንደገና ገጥመው ድል አደረጉት። ብዙ የጠላት ጦር አባላትንም ገደሉ። ዑመር ሰመተር ከደጋው የኢትዮጵያ ክፍል በሚላክላቸው የሰው ኃይል፣ መሳሪያና ስንቅ እየተጠናከሩ እንደገና ቆራሄ ላይ ከጠላት ጦር ጋር ገጥመው አመድ አደረጉት። በመጨረሻም ከጠላት ምሽግ ውስጥ ገብተው የጨበጣ ውጊያ በማካሄድ ታላቅና የማይረሳ ገድል ፈፅመዋል።

ከዚህ በኋላ ወደ ደገሃቡር ተመልሰው ከበላይ አዘዦቻቸው ጋር ተገናኙ። በዚህም ወቅት የጦሩ የአንዱ ክፍል አዛዥ የነበሩት ደጃዝማች ገብረማርያም የዑመርን ጀግንነት ተመልክተው በኦጋዴን አውራጃ ካሉት የአካባቢው ተወላጆች ወታደር መልምለው እንዲቀጥሩ ፈቀዱላቸው። በዚህም ጊዜ የፊታውራሪነት ማዕረግ ተሰጣቸው። ፊታውራሪ ዑመር ሰመተር ጠላትን በማንበርከክ በገርለጉቤ፣ በቆራሄ፣ በሃነሌ ... የሚያስደንቅ ጀብዱ ፈፀሙ። ደጃዝማች አፈወርቅ ከሞቱም በኋላ ወታደሩን እያረጋጉ ሲዋጉ ቆይተው በመጨረሻ እርሳቸውም በስድስት ጥይት ቆስለው ስለነበር ወደ ጂግጂጋ ተመለሱ። ፊታውራሪ ዑመር ሰመተር የደረሰባቸው ቁስል እጅግ ከባድ ስለነበር ለጦርነት መሰለፍ ከማይችሉበት ደረጃ ላይ ደረሱ። የጦር መሳሪያ የሚገኝበትን ዘዴ እየቀየሱ፣ ሕዝቡም ካለው የማረሻ በሬና ሌላም ቁሳቁስ እያዋጣ በመሸጥ ጥይትና ጠመንጃ እየገዛ ትልቅ ውጤት አስገኝቶ ነበር፡፡

በኋላም ቁስላቸው እጅግ እየበረታባቸው ስለሄደ ወደ ሃርጌሳ መሰደድ ግድ ሆነባቸው። ከሃርጌሳ ተነስተው ኬንያ ገቡ። ከኬንያ ወደ ለንደንም ተወስደው ነበር። ከዚያም የቀረውን የጦርነት ጊዜ በስደት ላይ ሆነው ካሳለፉ በኋላ ነፃነት ሲመለስ ወደ አገራቸው ገቡ። ስድስቱ ጥይት በአካላቸው ውስጥ እንዳለ ነበር ወደ አገራቸው የተመለሱት።

ነፃነት ከተመለሰ በኋላ አርበኛው ሁሉ እየፎከረና እያቅራራ ጀግንነቱን ሲያስመሰክር ፊታውራራ ዑመር ሰመተር በምድረ ኦጋዴን ከጦር የተረፉ ጀግኖች ናቸው ካሉበት በመብራት ያስፈለጓቸው። ቀጥሎም የደጃዝማችነት ማዕረግ ተሰጣቸውና የኦጋዴንና ጂግጂጋ ገዢ ሆኑ።

ይሁን እንጂ በአካላቸው ውስጥ ያሉት ጥይቶች እረፍት ነሳቸው፤ ቁስሉም እያመረቀዘ አስቸገራቸው። በሐረር ከተማ ሃኪሞች ባሉበት ቦታ ሁሉ እየተዘዋወሩ ቢታከሙም መዳን ግን አልቻሉም።

ደጃዝማች ዑመር ሰመተር ለአገራቸው ትልቅ ቁም ነገር ሰርተው መጋቢት 6 ቀን 1936 ዓ.ም፣ በተወለዱ በ65 ዓመታቸው አረፉ። ሥርዓተ ቀብራቸውም በሐረር ከተማ ውስጥ በወታደራዊ ክብር ተፈጽሟል።

ደጃዝማች ዑመር ሰመተር ከመሞታቸው በፊት እንዲህ ብለው ነበር። « ... የአገሬን ሕዝብ የፈጀው ጠላት በጀግኖች ክንድ ተረግጦ ሲወጣ በዓይኔ ተመልክቻለሁ። የመገዛት፣ የመዋረድና የመረገጥ እድል ምን እንደሆነ አይቻለሁ። እንደተራራ ንብ በየምሽጉ እየገቡ የሚነድፉ ኢትዮጵያውያን ዘር በመሆኔም ኮርቻለሁ። በታሪክ የሰማሁትን የዓድዋ ጀግኖች ጀብዱ ለማስመስከር ልጆቻቸው በኦጋዴን የጣሊያንን አንገት ሲቆርጡ አይቻለሁ። የዚህ ሕዝብ ልጅ በመሆኔ አሁንም እኮራለሁ። የማዝነው ግን መላው ሱማሌዎች ተባብረው የአንዲት ኢትዮጵያ ልጅ ሆነው በአንድ ሰንደቅ ዓላማ ስር ሲጠቃለሉ ሳላይ በመሞቴ ነው። በመቃብርም ውስጥ ምኞቴ ይህ ነው፡፡»

ደጃዝማች ዑመር ሰመተር የባሕል፣ የሃይማኖትና የቋንቋ ልዩነት ለአገር አንድነት መሰናክል መሆን እንደሌለባቸው ሲያስገነዝቡም « ... ቅኝ ገዢዎች በፈጠሩት ክፉ ሴራ አንዳንድ አገሮች እየተለያዩ ኖረዋል። የተለያዩትም በመጀመሪያ ከታሪክ ጋር ያልተያያዘ ድንበር በማበጀት፤ ቀጥለውም በሃይማኖትና በጎሳ እየተመካኘ ነው። ባሕል፣ ሃይማኖትና ቋንቋ አንዱን ወገን ከሌላው ሊለዩ የሚችሉ ምክንያቶች አይደሉም። በሕንድ በመቶ የሚቆጠሩ ሃይማኖቶችና ቋንቋዎች አሉ ሲባል ሰምቻለሁ፤ በሌሎቹም አገራት እንዲሁ። ይሁን እንጂ ሰዎች የተለያየ ቋንቋ በመናገራቸው ከመሰረታዊ ታሪክ ሊፈናቀሉ አይገባም። አሁንም ኢምፔሪያሊስቶች በምስራቅ አፍሪካ ቀንድ የሚሸርቡት ሴራ ለታሪክ የተጋለጠ ነው። ጠላትን ተባብረን ከአገራችን ያስወጣን ኢትዮጵያውያን ቅኝ ገዢዎች ቀብረውት የሄዱት ቦንብ ቀኑን ጠብቆ እየፈነዳ ወገን ከወገኑ ሊፋጅበት አይገባም። እኛ ሱማሌዎችም ከሌሎች ሱማሌዎች ጋር ተባብረን ከአንዲት ኢትዮጵያ ጋር ተቀላቅለን በሰላም መኖር አለብን።

ኦጋዴን በጦር ሜዳ፣ በሐረርም ጠቅላይ ግዛት በአስተዳዳሪነት ስላለሁ እንዳሁኑ የአልጋ ቁራኛ ሳልሆን ከሰሜን፣ ከምዕራብ፣ ከደቡብ እንዲሁም ከመሐል ኢትዮጵያ የመጡ የአገሪቱን ተወላጆች ተመልክቻለሁ። ከነደጃዝማች ነሲቡ እና ከነደጃዝማች አፈወርቅ ጋር ሆኜ ተዋግቻለሁ። ሌላውን ኢትዮጵያዊ ከኦጋዴን ሱማሌ ወይም ከሌላው ሱማሌ የሚለው አንዳችም ነገር ዐይቼ አላውቅም። ባሕል፣ ሃይማኖትና ቋንቋ ሌላ ጉዳይ ነው። ስለዚህ ምኞቴ በምስራቅ ክፍላችን ያሉ የተበታተኑ ሱማሌዎች አንድ ሆነው ኢትዮጵያዊነታቸውን ሲያስከብሩ ይታየኛል። በጠመንጃ ሰደፍ ያስወጣነው ጠላት መልኩን ለውጦ ከእናት አገር ሊለይ ታሪክ ሰራሽ ሳይሆን ሰው ሰራሽ ችግር እየፈጠረ ነው። ሕዝባችን ይህን ተረድቶ አንድነቱን ማጠናከር አለበት ...» ብለው ተናግረው ነበር፡፡

እነሆ እኚህን ጀግና ታሪክ ሲዘክራቸው ይኖራል።

# የዝነኞች ገጽ

# የኢትዮጵያ ሥነ- ጽሁፍ ዋርካ

**ሙሉጌታ ብርሃኑ**

ያሳለፍነው ሳምንት የካቲት 27 ቀን 2015 ዓ/ም ለኢትዮጵያ የሥነ-ጽሁፍም ሆነ የምርምር ዓለም ጥሩ ቀን አነበረችም። ሊነጋጋ ሲል ሰማዩ ይጠቁራል፤ ያቺ ሌሊት ግን የምርም የጠቆረችና ምህረት የለሽ ጨለማን ያዘለች ነበረች። ምክንያቱ ደግሞ ጉምቱውን የኢትዮጵያ ሥነ- ፅሁፍ ሰው መመለሻ በሌለው የሞት ሁዲድ ይዛ እብስ ማለቷ ነው።

ተባባሪ ፕሮፌሰር ዘሪሁን አስፋው፣ በኢትዮጵያ የሥነ-ጽሁፍና የምርምር ስራዎች ውስጥ ትውልድን ከመቅረጽ አንስቶ የነበራቸው ሚና ይህ ነው ተብሎ በቀላሉ የሚነገር አይደለም። ተባባሪ ፕሮፌሰር ዘሪሁን አስፋው ማን ነበሩ፤ ለሀገራቸውስ ምን አበረከቱ የሚለውን ጉዳይ በዛሬው የዝነኞች ገፅ ከብዙ በጥቂቱ እንቃኘው።


ጥቅምት 10 ቀን 1944 ዓ.ም የኢትዮጵያ ሰማይ የፈካበት ብሩህ እለት ነበረ። ለምን ካላችሁ የምናወራው ስለ አንድ ታላቅ ሰው ነውና እኚህ ሰው የተወለዱበት እለት ነበር። እኚህ ታላቅ የሥነ-ፅሁፍ ሰው ባይዘመርላቸውም በዝምታና በጠመዝማዛው ጎዳና እየተጓዙ በተለይ ለሥነ-ጽሁፉ ዓለም ዋርካ የሚያስብላቸውን እልፍ ተግባራት ከውነዋል። ከነበራቸው የልጅነት ታሪክ ስንጀምርም የመጀመሪያ እና የሁለተኛ ደረጃ ትምህርታቸውን ያጠናቀቁት በተወለዱባት የደሴ ከተማ ሲሆን፣ በወይዘሮ ስህን ትምህርት ቤት በመጀመር፣ በዚያው በደሴ በዕደ ማርያም ትምህርት ቤት አጠናቅቀዋል። ወይዘሮ ስህን ትምህርት ቤት በነበሩበት ወቅት ከነበራቸው የትምህርቱ ዓለም ብቃት ባሻገር ሙዚቃ የመጫወት ልዩ ተሰጥኦና ፍቅርም ነበራቸው። ከዚያ በመውጣትም የተወለዱባትን ቀዬ ለቀው ወደ አዲስ አበባ በመምጣት የሀገር ኩራት ለመሆን ያበቃቸውን የትምህርት ጉዞ ቀጠሉ። በዚህም በቀድሞው የቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ዩኒቨርሲቲ ውስጥ የከፍተኛ ትምህርታቸውን ተከታትለዋል። በአንድ ወቅትም የአርቲስት ተስፋዬ አበበ (ፋዘር) ተማሪ ነበሩ።

ዩኒቨርሲቲው በሚሰጠው ማህበረሰባዊ አገልግሎት ላይም ቀዳሚነታቸውን በማሳየት በኤርትራ ከረን ለአንድ ዓመት በማስተማር እንዲሁም በእድገት በህብረት ዘመቻ ደግሞ በዓድዋ አካባቢ ዘምተው የህብረተሰብ አገልግሎትን በተሳካ ሁኔታ ሰጥተዋል።

ከዩኒቨርሲቲው የመጀመሪያ ዲግሪያቸውን ከተቀበሉ በኋላም በስሩ ወደ ነበረው ወደ አለማያ ግብርና ኮሌጅ በማቅናት በረዳት ምሩቅነት ተቀጥረው ክህሎትና የስራ ደረጃቸውንም ከጊዜ ወደ ጊዜ እያሻሻሉ እስከ ዩኒቨርሲቲ መምህርነት ደረጃ በመድረስ በመምህርነትና በተከታታይ ትምህርት አስተባባሪነት ቀጠሉ። በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የአማርኛ ቋንቋና ፎክሎር ሥነ ጽሑፍ ትምህርት ክፍል ውስጥ ደግሞ በተለያዩ ማዕረጎችና ኃላፊነቶች ለማገልገል ችለዋል። ከብዙ የመማር ሂደት በኋላም ከትምህርት ቤቶችና ከሕይወት የቀሰሙትን እውቀት ለትውልዱ በማካፈል ለአርባ ዓመታት ያህል በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ሲያስተምሩና ትውልዱን ሲቀርጹም ቆይተዋል።

በእነዚህ አርባ ዓመታትም የሥነ-ጽሁፍ መምህር በመሆን በኢትዮጵያ ሥነ-ጽሁፍ ትልቅ ዋርካ ሆነው ከስራቸው ብዙዎችን አስጠልለው ጠቢባንን ማፍራት ችለዋል። በሥነ ፅሑፍ ሃያሲነታቸው አንቱታን ያተረፉት ተባባሪ ፕሮፌሰር ዘሪሁን ለ42 ዓመታት ባገለገሉበት በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የቋንቋና ሥነ ፅሑፍ ትምህርት ክፍል ውስጥም ኃላፊ በመሆን አገልግለዋል።

የመምህርነት ሙያ እንደ ድልድይ ሆኖ ትውልዱን ማሸጋገር ነው። ደስታና እርካታው የሚገኘውም በእነርሱ ድልድይነት ተሸጋግረው ከወደ ማዶው በሚመለከቷቸው ሰዎች ስኬት ነው። ረዳት ፕሮፌሰር ዘሪሁን አስፋው ለኢትዮጵያ የሥነ-ጽሁፍም ሆነ ለሌላ



**የመምህርነት ሙያ እንደ ድልድይ ሆኖ ትውልዱን ማሸጋገር ነው። ደስታና እርካታው የሚገኘውም በእነርሱ ድልድይነት ተሸጋግረው ከወደ ማዶው በሚመለከቷቸው ሰዎች ስኬት ነው**

ያበቋቸውን እንቁ ሰዎችን ቤቱ ይቁጠረው ከማለት ውጭ በቁጥር ለማስቀመጥ እጅግ በጣም አዳጋች ነው። የእሳቸው ስራ ሌሎችን ከማብቃት በተጨማሪ በተለያዩ የስነ-ጽሁፍ ጉዳዮች ላይ ጠለቅ ያለ ምርምር ማድረግም ነበር። ከምርምር ስራዎቻቸው መሃከል አንደኛው ከፖፑሌሽን ሚዲያ ሴንተር ጋር በመሆን የተለያዩ የሥነ ሕዝብ ጥናቶችን የሰሩት ተጠቃሽ ነው። ከዚህም በሻገር በትልቅ ሀያሲነታቸውም የታወቁ ነበሩ።

በሕይወት ዘመናቸው ትንሽ ትልቅ ሳይሉ ከጀማሪ ደራሲያን እስከ ትላልቅ ሀያሲያን እና ተማራማሪዎች ድረስ በማማከርና ልዩ ልዩ ሙያዊ ድጋፍን መስጠት ስለቻሉት ታላቅ ሰው ከእሳቸው ጋር በተለያዩ አጋጣሚዎች መገናኘት የቻሉ ሁሉ በልበ ሙሉነት ታላቅነታቸውን ይመሰክራሉ። ከእነዚህም መሃከል ከ1976 ዓ/ም ጀምሮ እንደሚያቋቸውና በተለያዩ ጉዳዮች ላይም አብረው እንደሰሩ የሚናገሩት ረዳት ፕሮፌሰር ደረጀ ገብሬ "ዘሪሁን በተገኙበት ሁሉ የተመሰገኑና ነገሮችን ጥበብ በተሞላበት መንገድ የሚከውኑ የስኬት ሰው ነበሩ" በማለት ይገልጿቸዋል።

ተባባሪ ፕሮፌሰር ዘሪሁን አስፋው ለትውልድ አሻራቸውን ለማኖር ከሰሯቸው ትላልቅ ስራዎች መሃከል አንደኛው 'የሥነጽሁፍ መሠረታውያን' የተሰኘው መጽሃፋቸው ሲሆን፣ ሌላኛው እውቅናን ያገኙበት መጽሃፍ ደግሞ 'ከበዓሉ ግርማ እስከ አዳም ረታ' የተባለው የሥነ ጽሑፍ ትምህርት አጋዥ መጽሃፍቶችን ጨምሮ አራት የተለያዩ መጽሃፍትን በመጻፍ ለአንባቢያን አድርሰዋል። በበሳል ሀያሲነታቸው ከሚሰሯቸው የአርትኦት ስራዎች በተጨማሪ የተለያዩ ጥናት እና ምርምሮችን በመሥራት ሀገርና ትውልድ ገንቢ ለሆኑ ዓላማዎች አውለዋል። ዋነኛው ዓላማቸውም በትውልዱ ውስጥ የእውቀትና የጥበብን ብርሃን ማስረጽ ነበር። በዚህም ከመጀመሪያ ዲግሪ ጀምሮ እስከ ዶክትሬት ዲግሪ ድረስ በርካታ ተማሪዎችን አስተምረው ለወግ ለማዕረግ አብቅተዋል።

ከማስተማርና ከማሰልጠን ጎን ለጎን በተለያዩ ጊዜያት 143 የመጀመሪያ ዲግሪ ተመራቂዎችን ፣ 80 የማስተርስ ዲግሪ እንዲሁ 20 የዶክቶሬት ዲግሪ ተማሪዎችን በምርምር ሥራዎቻቸው በማማከርና ድጋፍ በመስጠት አለኝታነትታቸውን አሳይተዋል። ይህን ሁሉ ሲያደርጉ ግን ያለ አንዳች ሳንቲም ከንጽሁ የበጎነት ስሜት በመነጨ መልካምነት ነበር። ከእነዚህም መሃከል በዛሬይቱ የኢትዮጵያ የሥነ-ጽሁፍና የምርምር ማህደር ውስጥ ስማቸው የሰፈሩ የእሳቸው ፍሬዎች በርካቶች ናቸው።

እሳቸው 'የኢትዮጵያ ሥነ-ጽሁፍ ዋርካ ናቸው' ሲባል በምክንያት ነው። ከእዚህ ዋርካ ስር ቁጭ ብለው የእውቀትና የጥበብን ሀሁ ከተማሩት መሃከል አንዷ የአሁኗ የኢትዮጵያ ደራሲያን ማህበር ሥራ አስኪያጅ በመሆን የምታገለግለውና በኢትዮጵያ የሥነ ጽሑፍ ታሪክ ውስጥ የመጀመርያዋ ሴት የአጭር ልብ ወለድ ጸሐፊት መሆን የቻለችው የዝና ወርቁ ናት። እሷም ስለ እውቀት አባቷ ቃል በቃል እንዲህ ትገልጻለች፣ "ጋሽ ዘሪሁን ትዕግስተኛ ፣ መካሪ ነበር። ኢትዮጵያ እጅግ ታላቅ የሥነ ጽሑፍ ምሁር ነው ያጣችው።"

ሌላኛው ከእሳቸው ጥላ ስር ረዥም የሆነ የጥበብ ብርሃንን አሻግሮ የተመለከተው ከያኒ አንዷለም አባተ በኀዘን ተክዞ "እኚህን ሰው ማጣት የተደገፍክበት ወንበር ድንገት ሾርተት ሲልብህ ያለውን ስሜት የሚፈጥር ነው" ሲል ስሜቱን ያጋራል።

በነበራቸው የሙያ ክህሎትና ሁለ ገብ እውቀት በተለያዩ ጊዜያት ያቀረቧቸው የምርምር ሥራዎች በውጭና በሀገር ውስጥ የምርምር መፅሔቶች ላይ ለመታተም በቅተዋል፡፡ የምርምር ስራዎቹ ከሀገር አልፈው ለዓለም ሁሉ ጠቃሚና አዲስ መንገድ ቀያሽ ናቸው። በብዙ ውጣ ውረዶች እያለፉ ለኢትዮጵያ ሀገራቸው ዘመን አይሽሬ የሆኑ ስራዎችን ማበርከት በመቻላቸውም በሥራ ዘመናቸው የተለያዩ ሽልማቶችን ተቀዳጅተዋል። በሕይወት ዘመናቸው ብዙ ደክመው ብዙ የሰሩ ቢሆንም እሳቸው ግን ገና ምን ሰራሁ የሚሉ እንጂ ይሄን ሰራሁ ብለው የማኮሩ አልነበሩም። በሚዲያዎች እንኳን ቀርበው እምብዛም የማይታዩ ሙያ በልብ ስለመሆናቸው የሚያውቋቸው ይናገራሉ።

ተባባሪ ፕሮፌሰር ዘሪሁን ከህልፈተ ሕይወታቸው ጥቂት ቀናት ቀደም ብሎ በአንድ ትልቅ ስራ ላይ ተጠምደው ነበር። የታላቁ ደራሲ ሀዲስ አለማየሁ መጽሃፍ የሆነውን 'ፍቅር እስከ መቃብር'ን የኢትዮጵያ ብሮድካስቲንግ ኮርፖሬሽ ከሰው መሆን ፊልም ፕሮዳክሽን ጋር በመተባበር መፅሐፉን ወደ ቴሌቪዥን ድራማ ለመቀየር በሚሰራው ስራ ተባባሪ ፕሮፌሰር ዘሪሁን ሙያዊ ድጋፋቸውን በመለገስ ላይ ነበሩ። በመጽሃፉ ዙሪያም ጠለቅ ያለ የምርምር ስራ በማካሄድ ላይ ነበሩ።

የአጭር ልብወለድ ንድፍና ተግባራዊነት ላይ የሚያተኩር መፅሐፍ አጠናቀው ለሕትመት ለማብቃት ዝግጅት በማድረግ ላይም ነበሩ። በብዙ ድካም የዘሩትን የእውቀት አዝመራ እሸቱንም ሳይቀምሱ ያቺ ለሊት ደርሳ ወደ ሞት ብትወስዳቸውም። የሚሰሩት ሁሌም ለትውልዱ ነውና ትውልዱም ከሚያምረው የእውቀት አዝመራ እየቀጠፈ መብላቱና እሳቸውን ማመስገኑ የማይቀር ነው። ትልልቅ ሰዎች ሁሌም በትልቅ ስራቸው ውስጥ በህያውነት ተቀርጸው ይኖራሉ።

ከጥበቡ ዓለም ማህበረሰብ ብቻ ሳይሆን ጥሩ የሆነ የቤተሰብ መሰረት መገንባት የቻሉት ተባባሪ ፕሮፌሰር ዘሪሁን አስፋው የአንድ ሴት ልጅና የሶስት ወንዶች አባትም ነበሩ። አስደንጋጭ የሆነው ድንገተኛ ህልፈተ ሕይወታቸው ለቤተሰቡ እጅጉን አስደንጋጭ ነበር። ያቺ መጥፎ ለሊት ከመድረሷ ሰዓታትን ቀደም ብሎ ረዳት ፕሮፌሰር ዘሪሁን በሞት ሳይሆን በጥበብና እውቀት ባህር ውስጥ እየዋኙ በስራ ተወጥረው ነበር። በዚያች ሌሊት አድፍጦ የሚጠብቃቸውን የሞትንም ሴራ አልተረዱም ነበርና በብሩህ ተስፋ አሻግረው ነገን እየተመለከቱ ግብራቸውን ይከውናሉ። ነገን ለማየት ቢጓጉም፣ ነገን ለማየት ሳይችሉ ቀሩ። እናም በዚያች ሌሊት የካቲት 27 ቀን 2015 ዓ.ም የነብስና ስጋቸው አብሮነት አከተመና እስትንፋሳቸው ጸጥ አለች። በተወለዱ በ71 አመታቸውም ስራዎቻቸውን አስረክበውን ከዚህች ዓለም ድካም በሞት ተለዩን። ነብሳቸውን በአጸደ ገነት ያኑርልን።

# ዓለም አቀፍ

## ባይደን በፕሬዚዳንት ፑቲን ላይ ለወጣው የእስር ትዕዛዝ ድጋፋቸውን ሰጡ

የአሜሪካ ፕሬዚዳንት ጆ ባይደን ዓለም አቀፉ የወንጀል ፍርድ ቤት በሩሲያ አቻቸው ፕሬዚዳንት ቭላድሚር ፑቲን ላወጣው የእስር ማዘዣ ድጋፋቸውን ሰጡ።

ዓለም አቀፉ ፍርድ ቤት ፕሬዚዳንት ፑቲንን በዩክሬን የጦር ወንጀል በመፈጸም የከሰሳቸው ሲሆን ፕሬዚዳንት ባይደንም የሩሲያው መሪ "በግልጽ" ፈጽመውታል ብለዋል።

ሩሲያ በዩክሬን ወረራ ከፈጸመች በኋላ ሕጻናትን ከዩክሬን ወደ ሩሲያ በሕገወጥ መንገድ አፈናቅላለች የሚልም ክስ ቀርቦባታል። ሞስኮ ይህንን ውንጀላ ውድቅ አድርጋ የእስር ትዕዛዙንም 'አሳፋሪ' ስትል ወቅሳለች።

ሩሲያ የአይሲሲ ፈራሚም ሆነ አባል ባለመሆኗ ፍርድ ቤቱ በአገሪቱ ላይ ምንም ዓይነት ሥልጣን የለውም። ዓለም አቀፉ ፍርድ ቤት የአንድ አገር መንግሥት ካልተባበረው ተጠርጣሪዎችን የማሰር ሥልጣንም ስለሌለው እርምጃው ሊያመጣ የሚችለው አዲስ ነገር የለምም እየተባለ ነው።

ሆኖም የእስር ትዕዛዙን ፕሬዚዳንቱ በተለያየ መንገዶች



ሊጎዳቸው እንደሚችልም ተጠቅሷል፤ ለምሳሌም ያህል የዓለም አቀፍ ጉዞዎችን ማድረግ አለመቻል አንዱ ነው። ፍርድ ቤቱን ካቋቋሙትና ፈራሚና አባል ከሆኑት 123 አገራት ውስጥ አንዱን ከረገጡ ሊታሰሩ ይችላሉ።

ፕሬዚዳንት ፑቲን በዓለም አቀፉ የወንጀል ፍርድ ቤት የእስር ትዕዛዝ የወጣባቸው ሶስተኛው መሪ ናቸው። ፕሬዚዳንት ባይደን ፍርድ ቤቱ በአሜሪካ ውስጥ ምንም አይነት ሥልጣን ባይኖረውም የእስር ማዘዣው መውጣቱ ጠንካራ መልዕክት እንደሚያስተላልፍ ተናግረዋል።

አስተዳደራቸው ቀደም ሲል በዩክሬን በቀጠለው ጦርነት ሩሲያ የጦር ወንጀሎችን መፈጸሟን በይፋ ያወጀ ሲሆን ምክትል ፕሬዚዳንት ካማላ ሃሪስ ከጥቂት ወራት በፊት ተሳታፊዎች "ተጠያቂ ይሆናሉ" ብለዋል።

የተባበሩት መንግሥታት ድርጅት በዚህ ሳምንት መጀመሪያ ላይ ባወጣው ሪፖርት ሩሲያ ዩክሬናውያን ህጻናትን በቁጥጥሯ ስር ካሉ አካባቢዎች ማፈናቀሏን አስታውቆ ይህም የጦር ወንጀል መሆኑን አረጋግጧል።

ዓለም አቀፉ የወንጀል ፍርድ ቤት ፕሬዚዳንት ፑቲን ህጻናትን በማፈናቀል እጃቸው አለበት በሚል ክስ የመሰረተው በድርጊቱ በቀጥታ በመሳተፍ እንዲሁም ከሌሎች ጋር እንደፈጸሙት የሚያሳምን በቂ ምክንያት እንዳለው አመልክቷል።

በተጨማሪም የሩሲያው መሪ ህጻናቱን ከዩክሬን የሚያፈናቅሉ ሌሎች አካላትንም ለማስቆም ያላቸውን ሥልጣናቸውን ሳይጠቀሙ እንደቀሩ ነው ፍርድ ቤቱ ያሳወቀው።

የሩሲያ የህጻናት መብት ኮሚሽነር ማሪያ ሎቮቫ-ቤሎቫም በተመሳሳይ ወንጀል በዓለም አቀፉ የወንጀል ፍርድ ቤት ተፈላጊ ሰው ሆነዋል።

የአይሲሲ አቃቤ ሕግ ካሪም ካን የእስር ቤት ትዕዛዙ "በማስረጃዎች፣ በምርመራ እና በሁለቱ ባለሥልጣናት በተነገሩ መግለጫዎች ላይ የተመሰረቱ ናቸው ብሏል። ፍርድ ቤቱ መጀመሪያ ላይ የእስር ማዘዣውን በሚስጥርነት ሊይዘው አስቦ የነበረ ቢሆንም ተጨማሪ ወንጀሎች እንዳይፈጸሙ እና እንዲቆሙ ለማድረግ በሚል ለሕዝብ ይፋ ለማድረግ ወስኗል።

"ህጻናት እንደ የጦር ምርኮ ተደርገው ሊወሰዱ አይችሉም፣ ሊፈናቀሉ አይችሉም" በማለት አቃቤ ሕጉ ለቢቢሲ ተናግረዋል። "ይህ ዓይነቱ ወንጀል መሆኑን ለመረዳት አንድ ሰው ጠበቃ መሆን አያስፈልገውም። በጣም አጸያፊ እንደሆነ መታወቅ አለበት" በማለት አክለዋል ሲል ቢቢሲ ዘግቧል።

## ሰሜን ኮሪያ ወደ 800 ሺህ የሚጠጉ ዜጎቿ አሜሪካን ለመዋጋት መመዝገባቸውን አስታወቀች

የሀገሪቱ ወታደር ቤት ለመቀላቀል ፈቃደኛ ከሆኑት አብዛኞቹ ተማሪዎች እና ሰራተኞች ናቸው ተብሏል፡፡

ሰሜን ኮሪያ፤ ወደ 800 ሺህ የሚጠጉ ዜጎቿ "አሜሪካን ለመዋጋት" በፈቃደኝነት ለውትድርና መመዝገባቸውን አስታወቀች፡፡

የሀገሪቱ ወታደር ቤት ለመቀላቀል ፈቃደኛ ከሆኑት አብዛኞቹ ተማሪዎች እና ሰራተኞች መሆናቸውም የሀገሪቱ ሮዶንግ ሲንሙን ጋዜጣ ዘግቧል።

የሰሜን ኮሪያ ይህን ዜና ይፋ ያደረገችው ዋሽንግተን እና የሴኡል በአይነቱ ልዩ የሆነውን ወታደራዊ ልምምድ በማድረግ ላይ ባሉበት በአሁኑ ወቅት መሆኑ ነው፡፡

ፒዮንጊያንግ ከአሜሪካ እና ደቡብ ኮሪያ የገባችው ውጥረት ቀጣናውን እንዳያተራምሰው ተሰግቷል። በተለይም ሰሜን ኮሪያ በተለያዩ ጊዜያት የምታስወነጭፋቸው የሚሳይል ሙከራዎች ውጥረቱን እንዳያባብሰው የሚል የበርካቶች ስጋት ሆኗል፡፡

ሰሜን ኮሪያ፤ ሐሙስ እለት የሁዋሶንግ-17 አህጉር አቋራጭ ሚሳይል (አይሲቢኤም) ወደ ጃፓን ባህር ማስወንጨፏ ይታወሳል፡፡

ሀገሪቱ ከፒዮንግያንግ አውሮፕላን ማረፊያ ያስወነጨፈችው ሚሳይል የጋራ ልምምድ በማካሄድ ላይ ላሉት ዋሽንግተን እና ሴኡል ጠንካራ ምላሽ ለመስጠት ያለመ እንደሆነም ነበር የገለጸችው፡፡

ሚሳይሉን የማስወንጨፍ መርሃ-ግብር ላይ የተገኙት የሰሜን ኮሪያው መሪ ኪም አሜሪካ እና ደቡብ ኮሪያ የሚያካሂዱትቂጋራ ወታደራዊ ልምምድ በኮሪያ ልሳነ ምድር ያለውን ውጥረት የሚያባብስ ነው ሲሉ ከሰዋል፡፡

ያም ሆኖ የጠላትን ጥቃት ለመከላከል ሁሌም ዝግጁ መሆን ያስፈልጋል ሲሉ ተደምጠዋል ፕሬዝዳንቱ። "ጠላቶችን እንዲበረግጉ በማድረግ እና ጦርነትን በመግታት እንዲሁም ሕዝባችን ሰላማዊ ሕይወት ኖሮት ለሶሻሊስት ግንባታ የሚያደርገውን ትግል በአስተማማኝ ሁኔታ ዋስትና በመስጠት የኒውክሌር ጦርነትን መከላከል ያስፈልጋል" ሲሉም



ተናግረዋል።

የሰሜን ኮሪያ የባሊስቲክ ሚሳኤሎች በዋሽንግተን፣ ሴኡል እና ቶኪዮ የተወገዙ ከመሆናቸው በተጨማሪ በተመድ የጸጥታው ምክር ቤት ጥቅም ላይ እንዳይውሉ የተከለከሉ መሆናቸው ይታወቃል፡፡

"ሁዋሶንግ-17" የሚል ሲያሜ የተሰጠው ሚሳይል አሜሪካን መምታት የሚችል አህጉር አቋራጭ ባሊስቲክ ሚሳኤል መሆኑ ይነገራል። ሚሳይሉ 1,000 ኪሜ (621 ማይል) ርቀት የመምዘግዘግ አቅም እንዳለውም ይነገራል ሲል የዘገበው አል አይን ኒውስ ነው፡፡

## ዋሊፍ ትራንስፖርት አ.ማ

### 4ተኛ መደበኛ እና 3ተኛድንገተኛ ጠቅላላ ጉባኤ ጥሪ

ዋሊፍ ትራንሰፖረት አ.ማ መስራች ባለ አክስዮኖች 2ተኛ መደበኛ ጠቅላላ ጉበኤ መጋቢት 23 ቀን 2015 ዓ.ም በፊንፊኔ ኢሊሊ ኢንተርናሽናል ሆቴል ከ2:30 ጀምሮ ያደርጋል።በዚሁ መሰረት የዳይሬክተሮች ቦረድ በአክብሮት ጥሪዉን ስናስተላልፍ በዊክልናም ሆነ በአካል መስራች ባለ አክስዮኑ ስበሰባ ላይ ለመሳተፍ ስትመጡ ህጋዊ ዉክልና እና የታደሰ የቀበሌ መታወቂያ ወይም መንጃ ፍቃድ ይዛችዉ እንድትገኙ እናሳዉቃለን።

የመደበኛ ስብሰባ አጀንዳዎች

1. የ ማህነሩን 2008-2014 ዓ.ም የስራ ሪፖርት መስማት ተወያይቶ ማፅደቅ
2. የማህበሩን 2008-2014ዓ.ም የዉጪ ኦዲተሮች ሪፖርት በመስማት ተወያይቶበት ማፅደቅ
3. የዳይረክተሮች ቦርድ አበል እና የጥቅማ ጥቅሞችን መወሰን

የ ድንገተኛ ስስብሰባ አጀንዳዎች

1. የማህበሩ መነሻ ካፒታል መቀነስ
2. የማህበሩን መመሥረቻ ፅሑፍ ማሻሸል
3. በማህበሩ የመኔጨዉን አክስዮን ለአዲስ እና ነባር ኣባላት በሽያጭ በማስተላለፍ የማህበሩን ካፒታል ማሳደግ
4. አዳዲስ ባለ አክስዮኖችን የመቀበልና የማስመዝገብ ተጨማሪ ስልጣን ለቦርድ ውክልና መስጠት

**የዳይሬክተሮች ቦርድ**

## የሐራጅ ሽያጭ ማስታወቂያ

የፍባለመብት እነ ግርማ ካሳ እና በፍ/ባለዕዳ ኦርኪድ ቢዝነስ ግሩፕ ሀ/የተ/የግ/ማ መካከል ስላለው የፍርድ አፈጻጸም ጉዳይ የፌደራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በመ/ቁጥር 94155፣94178 በ29/3/2015 ዓ.ም እና በ27/4/2015 ዓ.ም በዋለው ችሎት በሰጠው ትዕዛዝ መሠረት በኮ/ቀ/ክ/ከተማ የሚገኝ የሠ.ቁ ኮድ 3-56179 አ.አ ሆኖ ተጠቃቀሽ መዝገቦች ያሉበት መሆኑ ታውቆ የሐራጅ ሽያጭ መነሻ ዋጋ ብር 850,000(ስምንት መቶ ሃምሳ ሺ ብር) ሆኖ የሥም ማዛወሪያ ገዥ የሚከፍል መሆኑ ታውቆ ሚያዚያ 2 ቀን 2015 ዓ/ም በሐራጅ ይሸጣል። የተጫራቾች ምዝገባ በ9:30 ሰዓት ተጀምሮ የቀረቡ ተጫራቾች ተመዝግበው እንደተጠናቀቀ 'ወዲያዉኑ ጨረታው የሚካሄድ ይሆናል።

የሐራጁ ሽያጭ የሚካሄደው በፌደራል ፍርድ ቤቶች የፍርድ አፈጻጸም ዳይሬክቶሬት የጨረታ አዳራሽ ውስጥ ሲሆን፣ ንብረቱን ተጫርተው ለመግዛት የሚፈልጉ ተጫራቾች ከጨረታው ቀደም ብሎ ባሉት አራት የሥራ ቀናቶች ውስጥ ባለመብቱ ለማስጎብኘት በሚመርጧቸው ሶስት የስራ ቀናት በፌ/ፍ/ቤቶች ፍርድ አፈፃፀም ዳይሬክቶሬት ሐራጅ ክፍል ድረስ ከጠዋቱ በ3:30 ብቻ በመገኘትና ባለመብቱ በሚያቀርበው ትራንስፓርት ንብረቱን ለመጐብኘት የሚችሉ ሲሆን፤ እያንዳንዱ ተጫራች በሚጫረትበት ወቅት የንብረቱን ግምት 1/4 ኛውን በባንክ በተረጋገጠ c.P.O ማስያዝ ይኖርበታል። ከ1/4ኛ አስበልጦም ሆነ አሳንሶ የሚመጣ ተጫራች በጨረታው አይካፈልም። በጨረታው አሸናፊ የሆነው ግለሰብ አሸናፊ የሆነበትን ገንዘብ በአጠቃላይ ጨረታውን ከአሸነፈበት ቀን ጀምሮ በ15 ቀናት ውስጥ ገቢ ማድረግ አለበት።

በተጨማሪ ተጫራቾች ካፒታል ጌይን እና ታክስ ስምን ይዛወርልኝ የሚልን ጥያቄ፣ ሐራጁ ጉድቶኛል የሚሉ ጥያቄዎችን ዳይሬክቶሬት የማያስተናግድና በችሎት የሚጠየቅ መሆኑን እንገልፃለን።

**በኢ.ፌ.ዲ.ሪ ጠቅላይ ፍ/ቤት የፌዴራል ፍ/ቤቶች የፍርድ አፈፃፀም ዳይሬክቶሬት**

## አማራ ክልል

አቶ/ወ/ሮ ወ/ሪት ደሴ ቤዛ ደመቀ
ባሉበት
ከሳሽ ባህሪው ካሳ አለሙ
ተከሳሽ ደሴ ቤዛ ደመቀ መካከል ስላለው የገንዘብ ክስ ክርክር ጉዳይ መከሰስዎን አውቀው ክሱን በመዝገብ ቤት በኩል ወስደው መልስዎን ለቀን 19/07/2015 ዓ.ም ለሆነው ቀጠሮ በ3፡00 ሰዓት ባ/ዳርና አካ/ከፍ/ፍ/ቤት እንዲቀርብ ፍ/ቤቱ አዟል።

**በአማራ ብ/ክ/መ/ጠቅላይ ፍ/ቤት የባህር ዳር አካባቢዋ ከፍተኛ ፍ/ቤት**
**የፍትሐብሔር ዳኝነት አገልግሎት አሰጣጥ ቡድን**

---

በከሳሽ ዐ/ህግ እና በተከሳሽ አለባቸዉ አይተን አለነ መካከል ባለዉ የወንጀል ክርክር ተከሳሽ በተከሰሰበት አካለመጠን ያልደረሰን ልጅ መጥለፍ ወንጀል ለመጋቢት 18 ቀን 2015 ዓ.ም ከጠዋቱ 3፡00 ሰዓት በደቡብ አቸፈር ወረዳ ፍርድ ቤት እንዲቀርብ የማይቀርብ ከሆነ ጉዳዩ በሌለበት የሚታይ መሆኑን እንዲያውቁ ፍርድ ቤቱ አዟል።

**በአብክመ ጠቅላይ ፍ/ቤት በባ/ዳር አካ/ከፍ/ፍ/ቤት/የደ/አቸ/ወ/ፍ/ቤት**
**የወንጀል ዳኝነት አገ/አሰ/ቡ/ች/ፀሀፊ**

---

ከሳሽ እነ ፍስሃ ቢሻው
ተከሳሾች 1ኛ አፍሮ ጽዮን ኮንስትራክሽን ድርጅት
2ኛ ደ/ታቦር ዩኒቨርሲቲ
መካከል ስላለው የአሰሪና ሰራተኛ ክስ ተከሳሾች የፍርድ ቤት መጥሪያ ተልኮላቸው በቀጠሮው ቀን ሊቀርብ ስላልቻሉበዚህ ማስታወቂያ ጥሪ ተደርጎላቸው ለቀጠሮው ለ27/07/2015 ዓ.ም. በ2፡30 ሰዓት ደ/ጎን/ዞን/ከፍ/ፍ/ቤት ድረስ እንዲቀርቡ ባይቀርቡ ግን ጉዳዩ ተከሳሾች በሌሉበት የሚታይ መሆኑን እንዲያውቁ ፍ/ቤቱ አዟል።

**በአብክመ ጠቅላይ ፍ/ቤት በደ/ጎን/አስ/ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት**
**የፍታብሔር ዳኝነት አገልግሎት አሰጣጥ ዋና የስራ ሂደት**

## ለሶስተኛ ጊዜ የወጣ ማስታወቂያ

አፍሪካ ጫማ ፋብሪካ ኃ. የተ. የግል ማህበር አባላቱ መጋቢት 1 ቀን 2008 ዓ.ም. ባደረጉት ስብሰባ እንዲዘጋ ወስነዋል። እኔንም የማህበሩ አጣሪ አድርገው ሾመውኛል። ስለዚህ የማህበሩን መዘጋት ተቃዋሚ ወይም ዕዳ ፈላጊ ካለ ማስታወቂያው በጋዜጣ ከወጣበት ቀን ጀምሮ ባሉት ተከታታይ 30 የሥራ ቀናት ውስጥ ቂርቆስ ክፍለ ከተማ ቀበሌ 01/19 ፔድስ ሕንፃ የቢሮ ቁጥር 402 ወይም በስልክ ቁጥሮች፡- 011 552 62 00 /011 553 66 86 በሥራ ሰዓት ማመልከት የምትችሉ መሆናችሁን አሳውቃለሁ።

**አብርሃም ብርሃኑ አድማሱ**
**በመፍረስ ሳይ ያለው የአፍሪካ ጫማ ፋብሪካ ኃ. የተ. የግል ማህበር አጣሪ**

# ስፖርት





## ወርቅ አነፍናፊዋ የረጅም ርቀት ተወርዋሪ ኮከብ

**አለማየሁ ግዛው**

በአትሌቲክስ ሕይወቷ ለመቁጠር የሚታክቱ ሜዳሊያዎችን በተለያዩ ዓለም አቀፍ የውድድር መድረኮች ማጥለቅ ችላለች። ይህም የረጅም ርቀት የምንጊዜም ጀግና አትሌት አሰኝቷታል። በተለያዩ አገር አቀፍና ዓለም አቀፍ ውድድሮች እጅን በአፍ የሚያስከድኑ ድሎችን በመቀዳጀት ለበርካታ አትሌቶች ለማሳካት ቀርቶ ለማሰብ የሚከብዱ ገድሎችን ቀለል አድርጋ መስራት ተክናበታለች። አልሸነፍ ባይነትና ጠንካራ የጀግንነት ስሜቷ ጥበብ ከተሞላው የአሯሯጥ ስልቷ ጋር ተደምሮ እንኳን የአገሯ ዜጎች የዓለም ሕዝብም አድናቆት እንዲቸራት አድርጓል። ወርቅ አነፍናፊዋ የረጅም ርቀት ቀወርዋሪ ኮከብ ጥሩነሽ ዲባባ ቀነኒ።

አትሌቲክስን ባህሉ ካደረገ ቤተሰብ የፈለቀችው ኮከብ የታላላቆቿን በተለይም የአክስቷ ደራርቱ ቱሉና የታላቅ እህቷን እጅጋየሁ ዲባባ ፋና ተከትላ ወደ አትሌቲክሱ ዓለም ከገባች በኋላ ተነግሮ የማያልቅ ታሪክ ፅፋለች።

ጥሩነሽ ገና በለጋ እድሜዋ አትሌት የመሆን ዕድል የነበራት ቢመስልም የሩጫ ሕይወቷ ምን ያህል አስደናቂ ታሪክ የሚፃፍበት እንደሚሆን ቀደም ብለው የተነበዩ ጥቂቶች ነበሩ። ያም ሆኖ በአትሌቲክስ ታሪክ በትንሽ ዕድሜ የዓለም ቻምፒዮን የሆነች ሴት፣ በትንሽ ዕድሜዋ በኢትዮጵያ ኦሊምፒክ የሜዳሊያ ተሸላሚ ሴት፣ በኦሊምፒክ 5 ሺና 10ሺ ሜትር የመጀመርያዋ ሴት አትሌት ከመሆን በተጨማሪ ስድስት የኦሊምፒክ ሜዳሌዎች፣ አምስት የዓለም ቻምፒዮና የወርቅ ሜዳሊያዎችንና ሌሎች በርካታ ድሎችን ከዓለም ክብረወሰኖች ጋር ለማሳካት በቅታለች። ይህች በበርካቶች ዘንድ ተወዳጅ የሆነች ኮከብ ስለእሷ መስማትና ማንበብ የሚፈልጉ አያሌ ቢሆኑም እሷ ግን ውድድሮችን ስታደርግ እንጂ ብዙ ጊዜ ወደ



አትሌት ጥሩነሽ ዲባባ

መገናኛ ብዙሃን ወጥታ የምትታይ አይደለችም። በቅርቡ ግን ከሰላምታ መፅሄት ጋር ባደረገችው ቃለምልልስ በአትሌቲክስ ሕይወቷ ዙሪያ የተለያዩ አስተያየቶችን ሰንዝራለች።

እንደሷ ሁሉ በርካታ እንቁ ኦሊምፒያኖች የፈለቁባትን የአትሌቶች ምድር በቆጂን በተመለከተ ጥሩነሽ ዓመታትን መለስ ብላ የአትሌቲክስ ሕይወቷን ጅማሬ ስታስታውስ "በቆጂ ከፍታ ላይ የምትገኝ ትንሽ ከተማ ነች። ትንሽ ቀዝቃዛም ነች!" ትላለች። ይህም በስልጠና ወቅት አትሌቶችን የሚረዳ እንደነበር ታስታውሳለች። አሰልጣኞችም መልክአምድሩ የሚቸረውን ምቹ ሁኔታ ተጠቅመው የሩጫ ጥበብና ቴክኒካዊ እንቅስቃሴን በማከል ብዙ ኮከብ አትሌቶችን ሊዲያፈሩ እንደቻሉ ትናገራለች።

ጥሩነሽ መሮጥ የጀመረችው ገና የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤት እያለች ሲሆን ጎበዝ አትሌት የመሆኗ ነገር ግልጽ ሆኖ መታየት የጀመረውም በዚያ ወቅት ነበር። የመጀመርያ ዓለም አቀፍ ውድድር ያደረገችው እአአ በ2001 ነበር። ውድድሩን ስታካሄድ የ15 ዓመት ልጅ የነበረች ሲሆን አምስተኛ በመሆን ነበር ያጠናቀቀችው። ወደ አገር አቋራች ውድድሮች ለመግባት ዕድሉን ያገኘችውም ብዙም ሳይቆይ ነበር። ይህም ወደ ታላቅ አትሌትነት ለማቅናት ማርሽ ቀያሪ አጋጣሚ ሆኗታል። ምንም እንኳን አንፀባራዊ አትሌትነት ህይወቷ በትራክ (መም) ውድድሮች ላይ የበዛ ቢሆንም እአአ ከ2003-2008 ዓመት ድረስ በአገር አቋራጭና በተለያዩ የዓለም ቻምፒዮና ውድድሮች አምስት የወርቅ ሜዳለያዎችን በማስመዝገብ ሁለገብ የሆነ ድንቅ ችሎታዋን ማሳየት ችላለች፡፡

እአአ 2003 በፓሪስ በተካሄደው የዓለም አትሌቲክስ ቻምፒዮና የረጅም ርቀት ስኬቷን አንድ ብላ የጀመረችው ጥሩነሽ፣ ገና በ18 ዓመቷ በ5 ሺ ሜትር የወርቅ ሜዳሊያ በማሸነፍ በአትሌቲክስ ታሪክ ትንሿ ሴት የዓለም ቻምፒዮን መሆን ችላለች፡፡

ያንን የበኩር ድሏን ስታስታውስም "በሕይወቴ ከተደሰትኩባቸው ወቅቶች አንዱ ነበር፣ በሙቀት ውስጥ ነው ያሳለፍኩት ከዚያም በመጨረሻው ውድድር ላይ ነበርኩ፤ እና ሳሸንፍ ማመን አቃተኝ፣ ለመሮጥ አንድ ተጨማሪ ዙር ይቀራል ብዬ አሰብኩኝ! አሸንፋለሁ ብዬ አላሰብኩም ነበር፣ ምክንያቱም ከመላው ዓለም የተሳተፉ ትልልቅ አትሌቶች ነበሩ፤ ህልም እያለምኩ መስሎ ተሰማኝ" ትላለች፡፡

ከመጀመሪያ ዓለም አቀፍ ድሏ ከጥቂት ወራት በኋላ ወደ አገር ውስጥ ውድድሮች ተመልሳ በታላቁ ሩጫ 10 ኪሎ ሜትር የጎዳና ላይ ውድድር መሳተፍ እንደቻለችም ኮከቧ ታስታውሳለች።

ከድሎቿ ሁሉ እጅግ አንፀባራቂ የሆነውና አሁንም ድረስ በታሪክ ብቸኛ ሆኖ የሚጠቀሰው የቤጂንግ 2008 ኦሊምፒክ የ 10 እና 5ሺ ሜትር ጥምር የወርቅ ሜዳሊያ ስኬቷ ነው። ለእሷ ግን የተለየ ቦታ ያለው ምናልባትም በፓሪሱ የመጀመሪያ ዓለም አቀፍ ድሏ ምክንያት ይሆናል የ5ሺ ሜትር ስኬቶቿ በልቧ ውስጥ ልዩ ቦታ አላቸው። "5 ሺ ሜትርን ለመሮጥ በጣም የምወደው ርቀት ነው፣ ሁልጊዜ ብዙ ፉክክር አለ፣ ስለዚህ በዚህ ርቀት ውድድሮችን ባሸነፍኩ ቁጥር በጣም ደስ ይለኛል" ትላለች።

ተወርዋሪዋ ኮከብ በጎዳና ላይ ውድድሮችም የዋዛ አይደለችም። እአአ በ2012 በእንግሊዝ በተካሄደው ተወዳጁና ታላቁ የግማሽ ማራቶን የመጀመርያ ውድድሯን አድርጋ በድንቅ ብቃት ማሸነፍ ችላለች። ከጥቂት ዓመታት በኋላ ጥሩነሽ ፊቷን ወደ ማራቶን አዙራም በለንደንና በርሊንና በዓለም አቀፍ እውቅና በተሰጣቸው ውድድሮች ድንቅ ብቃቷን አሳይታለች። በ2017 በብዙ አትሌቶች ትልቅ ቦታ የሚሰጠውን የቺካጎ ማራቶንን በማሸነፍም ይህንኑ አስመስክራለች።

ባለፉት ጥቂት ዓመታት ከወሊድ ጋር በተያያዘ ከውድድር ርቃ የቆየችው ጥሩነሽ በቅርቡ ወደ ውድድር ብትመለስም ዘመን አይሽሬ ታሪኮችን በሰራችባቸው የመም ውድድሮች ሳይሆን በማራቶን ነው።

ከሩጫ ውጪ ከቤተሰቧ ጋር በማሳለፍ የበለጠ ደስታን እንደምታገኝ የምትናገረው ጥሩነሽ፣ የሩጫ ፍቅሯ ግን እንደቀድሞ ጠንካራ መሆኑንም ትገልጻለች። "ሩጫ በደሜ ውስጥ ነው፣ እናም ለስልጠና በወጣሁበት ጊዜ ሁሉ አሁንም ቀድሞ የነበረኝ አይነት ስሜት ይሰማኛል። ሁልጊዜ ልቤ እዚያው ሩጫ ላይ ነው" ስትልም አትሌቲክስ በሕይወቷ ውስጥ ያለውን ቦታ ታብራራለች።




## ብቸኛ ስለሆነው የእንስሳት ሙዚየም ምን ያህል እናውቃለን?

**ሠላማዊት ውቤ**

ልጆች እንደምን ሰነበታችሁ! ሳምንቱ እንዴት አለፈ? አሁን የትምህርት ወቅት እንደመሆኑ በጥናት እንዳሳለፋችሁት እንገምታለን። ባለፈው ሳምንት በኢትዮጵያ ብቸኛው ወደሆነውና በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ሥር የሚገኘውን የእንስሳት የተፈጥሮ ቅርስ መዘክር ጎብኝተን በመዘክሩ ስለሚገኙ የወፍ ዝርያዎች አስነብበናችሁ እንደነበር ታስታውሳላችሁ አይደል። ዛሬ ደግሞ ቀጣዩን ክፍል ይዘን ቀርበናል፡፡

ልጆች! እነዚህ እንስሳት እናንተ ተማሪዎች በክፍል ውስጥ በንድፈ ሃሳብ ደረጃ የተማራችሁትን በተግባር እያያችሁ የምታረጋግጡባቸው እንደመሆናቸው ሕይወት የላቸውም። በመዘክሩ የአደን ሠራተኞች ታድነው የሚመጡ ያረጁ፤ ወይም በተለያየ አደጋ የሞቱና ጫካ ውስጥ ወድቀው የተገኙ እንስሳት ናቸው። በመሆኑም አስጎብኛችን ወይዘሮ አምሳለ ተፈራ እንደነገሩን እነዚህ እንስሳት ወደ መዘክሩ ከመጡ በኋላ የእናንተን የተማሪዎችንና የሌሎች ጎብኚዎችን ትኩረት እንዲስቡ ተደርገው በሦስት መንገድ ይዘጋጃሉ።

በመዘክሩ ከሚገኙ አብዛኞቹ እንስሳት የሚዘጋጁት የውስጥ አካላቸው ይወጣና ሌላ ሰው ሠራሽ አካል ይገባላቸዋል። ከተፈጥሮ ዓይናቸው ጋር ፍፁም ተመሳሳይ የሆነና ከጠርሙስ የተሰራ ሰው ሠራሽ ዓይንም ይገጠምላቸዋል። ቆዳቸውና ቀንዳቸው ግን የራሳቸው የእንሰሶቹ ነው። ይሔም ሕይወት ያላቸው ያስመስላቸዋል። እንደ ጢንዚዛ ያሉት ደግሞ ሙሉ አካላቸው እንዳለ የራሳቸው ሆኖ በኬሚካል በመድረቅ ነው ለጉብኝት የሚቀርቡት። እንደ እባብ፤ ዘንዶና እንቁራሪት ያሉት ደግሞ ሙሉ አካላቸው እንዳለ ሆኖ በኬሚካል በማንበር ወይም በመዘፍዘፍ ነው ለዕይታ የሚቀርቡት። ልጆች ስለዚህ ሁሉም ሕይወት ያላቸው ይመስላሉ። ነገር ግን ሕይወት የላቸውምና ስትጎበኙ አትፍሯቸው። ቀርቦ በእጅ መንካት ግን አይቻልም፤ እሽ ልጆች!

ልጆች በመጀመርያ የምናስጎበኛችሁ የጽሑፍ፤ የስዕልና የፎቶ መረጃ ያለበት ክፍል ሲሆን ሁለተኛው የጀርባ አጥንት የሌላቸው እንስሳት ስብስብ ያለበት ነው። ሆኖም ልጆች እዚህ ክፍል ዋልያም አለ። ነገር ግን ዋልያ እዚህ ክፍል ውስጥ ተካትቶ የተቀመጠው በአገራችን የሚገኝ ብርቅየ ስለሆነ የጎብኚዎችን ትኩረት እንዲስብ ተብሎ መሆኑን አስጎብኛችን ነግረውናል። ሦስተኛው ክፍል ውስጥ የሚገኙት እንደ እንቁራሪት ፤ ጉርጥ ያሉና በውሃ ውስጥም ሆነ በመሬት የሚኖሩ እንስሳት ናቸው፤ ልጆች እዚሁ ክፍል ውስጥ በአንድ ጎን እንደ እባብ፤ ዘንዶና ሌሎች በደረታቸው የሚሳቡ እንስሳቶች አሉ። አራተኛው ክፍል አጥቢ እንስሳቶች የሚገኙበት ነው። ልጆች አምስተኛውም የአጥቢዎች ክፍል ሲሆን ቀንዳቸው ፤ ቆዳቸውና ከአንገታቸው በላይ ያለው የሰውነታቸው ክፍል ብቻ የሚገኝበት ነው። እነዚህም በሁለት በኩል ሲሆን የተቀመጡት በአንደኛው ጎን ተሰድረው የተቀመጡት ሥጋ በል እንስሳት ናቸው። በሌላው በኩል ያሉት ደግሞ ሣርና ቅጠላ ቅጠል የሚበሉ እንስሳት እንደሆኑም አስጎብኛችን ነግረውናል። ልጆች ታዲያ በዚህ ክፍል ውስጥ ትልቅ ቆዳ አለ። ቆዳው የወንድ አንበሳ ሲሆን ከላይ ጎፈር እንዳለውም አይተናል። ትልቅ የሆነው የወንድ አንበሳ እንደሆነም ነግረውናል። ከታች ያሉት ቆዳዎች ደግሞ የጅብና የቀበሮ እንዲሁም የሚዳቆና የአንባራይሌ እንደሆኑ አስረድተውናል። ከጅብ ዝርያ ተራ ጅብ የሚባለው ፤ የትም ቦታ የሚገኝ እንደሆነ ኃይለኛና ሰው ሳይቀር የሚበላው ጅብ ይሄው ተራ ጅብ የሚባለው እንደሆነም አስረድተውናል። በመጠን ይሄ ጅብ ግዙፍም ነው። ቆላማ ቦታ ላይ የሚገኘው ጅብ በላተኛ ቢሆንም እንደ ተራው ጅብ ኃይለኛ አይደለም።

በዚሁ ክፍል በሌላው ጎን የድመት ዝርያ የሆኑ እንስሳት ቆዳዎችም ይገኛሉ። ቆዳዎቹ የአቦ ሸማኔ፤ የነበርና የአነር ናቸው። ታዲያ አስጎብኛችን ቆዳቸው በዚህ ክፍል ውስጥ ከሚገኘው አጥቢና የድመት ዝርያ ያላቸው እንስሳት መካከል አቦ ሸማኔ ምድር ላይ ካሉት አጥቢ እንስሳቶች ፈጣኑ ሯጭ መሆኑን ነግረውናል። እሳቸው እንዳሉን አቦሸማኔ በሰዓት እስከ 120 ኪሎ ሜትር ይሮጣል፡፡

ልጆች አስጎብኛችን ስለነዚህ የድመት ዝርያ እንስሳት አንዳቸው ከሌላው የሚለያዩበትንም ነግረውናል። እንደነገሩን ታዲያ አቦ ሸማኔ ፊቱ ላይ ጥቋቁር መስመር ሲኖረው ነብር ግን የለውም። በተጨማሪም አቦ ሸማኔ ድፍን ጥቁር ነጠብጣብ ሲኖረው ነብር ደግሞ እንደ አበባ ክብ ነጠብጣቦች ናቸው ያሉት። በመሆኑም ሁለቱም በነጠብጣባቸው በእጅጉ ይለያሉ። የዝንጀሮና ጦጣ፤ የአይጥ ቆዳዎችም በክፍሉ ውስጥ አሉ። የሌሊት ወፎች ቆዳም ክንፍ ስላላቸውና ስለሚበሩ እንጂ አጥቢዎች በመሆናቸው በዚሁ ክፍል ውስጥ ተካትቶ ይገኛል። አነር ደግሞ ዳር ዳሩ ጠቃጠቆ መካከሉ ሰረዝ ጅራቱ ደግሞ አጭር ነው።

አምስተኛው ክፍል አጥቢ እንስሳቶች የሚገኙበትና ከአንገት በላይ የእንስሳት አካል ሲሆን በዓለማችን ግዙፉ የምድራችን እንስሳ የሆነው የዝሆን የራስ ቅል አለ። ልጆች ታዲያ አስጎብኛችን እንደገለፁልን ትልቅ የሚባለው የአንዱ ዝሆን ሙሉ የሰውነት አካል እስከ 6ሺህ ኪሎ ግራም ይመዝናል። ቅልጥሙ እንዲሁም የእግሩ መርገጫ ጫማውም ከራስ ቅሉ ጋር አብሮ ተቀምጧል። በተጨማሪም ውሃ የሚጠጣበትና ምግብ ወደ አፉ የሚያደርስበት ኩንቢውም ያውም ደግሞ የታችኛውን መንጋጋ ሳይጨምር በዚሁ ሥፍራ ተቀምጦ የሚገኝ ሲሆን እንስሳው ግዙፍ በመሆኑ ሰፊ ቦታ መውሰዱንም አስተውለናል። በዚሁ ክፍል ውስጥ የሰጎን እንቁላሎችም



ፎቶ- ኢዮብ ተፈሪ

ይገኛሉ። እንቁላሎቹ ትልልቅ ሲሆኑ ስዕል እየተሳለባቸው ለገበያ የሚቀርቡ መሆናቸውን አስጎብኛችን ገልፀውልናል፡፡

የአንበሳ፤ የጉማሬ፤ የዝሆንና የከርከሮ ጥርሶችም በዚሁ ክፍል ውስጥ ይገኛሉ። ጥርሶቹ ረጃጅም አንዳንዶቹም ሹል ናቸው። በተለይ በጎንና በጎን የሚወጡት ሁለቱ የዝሆን ጥርሶቹ በጣም ረጃጅም ናቸው። ልጆች! ይሄ የዝሆን ጥርስ በከፍተኛ ገንዘብ የሚሸጥ ውድ ሲሆን በአብዛኛው ዝሆን የሚታደነው ለዚህ ለጥርሱ ሲባል ነው። ጥርሱ ለጌጣጌጥና ለተለያዩ ነገሮች መሥርያ ይውላል።

ሌላው ውሃና መሬት ላይ የሚኖር ከዝሆን ቀጥሎ ያለ ግዙፍ እንስሳ የጉማሬ የራስ ቅል እዚህ ክፍል ይገኛል። የታችኛው መንጋጋ ከነጥርሱ ሲገኝ ትልልቅ በመሆኑ ከዝሆን የማይተናነስ ስፍራ ይዟል። በተለይ የውሻ ክራንቻ የሚባለው ጥርሱ እያደገ፤ እያደገ በመምጣት መጨረሻ ላይ ከዳርና ከዳር ያሉትን ረጃጅም የዝሆን ጥርሶችን ሊያክል እስኪደርስ ያድጋል። ልጆች! እኛ እንደጎበኘናቸው እናንተም ከአባባና ከእማማ ጋር ሆናችሁ ወደ መዘክሩ በመሄድ እነዚህን እንስሳት ጎብኝዋቸው እንድትጎበኟቸው እጋብዛለን ።